ወደ ገላቲያ ሰዎች

መግቢያ

ገላትያ አሁን ቱርክ ተብላ በምትጠራዋ አገር ማዕከላዊ ስፍራ የምትገኝ የቀድሞው የሮማ መንግሥት አንዱ ክፍለ ሐገር ነበረች። ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች የጻፈው ይህ መልእክት ለአንዲት ቤተክርስቲያን ሳይሆን፥ ለብዙ አብያተክርስቲያናት ነበር። እነዚህም አብያተክርስቲያናት በተለያዩ ዓመታት ቀደም ብለው ጳውሎስ ራሱ የመሠረታቸው ናቸው። በዚህ መልእክቱ ላይ ስማቸውን በዝርዝር ስላልጠቀሰ ለየትኞቹ እንደጻፈ አይታወቅም። በተጨማሪም ይህን መልእክት የጻፈበት ትክክለኛ ዓመት ባይታወቅም አንዳንድ ሊቃውንት በ54–56 ዓ.ም. ውስጥ ተጽፎአል ሲሉ፥ ሌሎች ደግሞ በ48–49 ዓ.ም. እንደተጻፈ ይናገራሉ።

ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የጻፈበት ምክንያት በመልእክቱ ውስጥ በግልጥ ተጠቅሶ ይገኛል። እነዚህን የአሕዛብ አብያተክርስቲያናት እንደ መሠረተ፤ አንዳንድ አይሁድ ክርስቲያኖች መጥተው የጳውሎስን ትምህርት መቃወም ጀመሩ። ጳውሎስ ያስተምር የነበረው፥ ሰው በእግዚአብሔር ፀጋና በእምነት አማካይነት እንደሚድን ነበር (ኤፌ. 2፥8)። እነዚህ አይሁድ ክርስቲያኖች ግን አንድ ሰው ለመዳን የአይሁድን ሕግ በተጨማሪ መፈጸም እንደሚገባው አስተማሩ። የእነዚህ አይሁድ ክርስቲያኖች ትምህርት ከተንሰራፋ የጳውሎስ የጸጋ ወንጌል ከንቱ ሆነ ማለት ነው። ስለዚህ ገና ሕፃን የሆኑት የገላትያ ክርስቲያኖች በአይሁድ ክርስቲያኖች ትምህርት ምክንያት ከእውነተኛው የመዳን መንገድ እንዳይስቱ ለማድረግ የስህተት ትምህርቱን የሚቃወም መልእክት መጻፍ ነበረበት። የገላትያ ሰዎች ደኅንነትን በሕግ ሥራዎች ለማግኘት ጥረት ማድረግ ከጀመሩ የተቀበሉትን ጸጋ በማጣት አደጋ ላይ ሊወደቁ ይችላሉ።

በቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚታወቀው ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች የጻፈው መልእክት የላቀ ዋጋ ሲሰጠው ቆይቷል። ማርቲን ሉተር ይህን መልእክት ካጠና በኋላ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የምታስተላልፈውን ስህተት ማስተዋል ጀመረ፤ የተሐድሶ እንቅስቃሴውንም ጀመረ። ለሉተር የበራው የቃሉ ብርሃን፥ ሰው ደኅንነትን የሚያገኘው ከቤተክርስቲያን ወይም ሕግን በመከተል ሳይሆን በእምነት የእግዚአብሔርን ጸጋ በመቀበል መሆኑ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ደኅንነትን በራሳቸው ሥራና ጥረት ለማግኘት ይፈልጋሉ። ስለዚህም ሃይማኖታዊ ወጎችንና ሥርዓቶችን በመፈጸም እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ይሞክራሉ። በገዛ ብርታታቸው ቅዱስ ለመሆን ይጥራሉ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ድካማቸው ከንቱ ነው። ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኘው በጸጋ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ከታላቅ ፍቅሩና ከብዙ ምሕረቱ የተነሣ ለኃጢአተኛ ሰዎች የሰማይን በር ከፍቶላቸዋል። በክርስቶስ በማመን በዚህ በር ማለፍ ይቻላል፤ ይህ ለገላትያ ክርስቲያኖች የተጻፈ ዋና መልእክት ነው። ስለ ጳውሎስ ሕይወት ለማወቅ የሮሜ መልእክትን መግቢያ ይመለከቷል።

አስተዋጽኦ

ሀ. መግቢያ (1፥1–10)።
   1. ሰላምታ (1፥1–5)።
   2. መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት (1፥6–10)።

ለ. ጳውሎስ ሐዋርያነቱን ለማረጋገጥ ያቀረበው ምላሽ (1፥11–2፥21)።
   1. ጳውሎስ ወንጌልን የተቀበለው በቀጥታ ከእግዚአብሔር መሆኑ (1፥11–24)።
   2. ጳውሎስ ከሌሎች ሐዋርያት ጋር ያለው ግንኙነት (2፥1–14)።
   3. የአይሁድ ሕግ ውድቀት (2፥15–21)።

ሐ. ጳውሎስ ስለ ወንጌል ያቀረበው መከላከያ (3፥1–4፥31)።
   1. ጽድቅ በእምነት መገኘቱ (3፥1–14)።
   2. ሕግና የኪዳን ተስፋ (3፥15–29)።
   3. ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች ያቀረበው ጥያቄ (4፥1–31)።

መ. ለቅድስና ሕይወት የቀረበ ጥሪ (5፥1–6፥18)።
   1. ከጸጋው መራቅ የሚያስከትለው አደጋ (5፥1–12)።
   2. በመንፈስ የሆነ ሕይወት (5፥13–26)።
   3. ሁለት ተግባራዊ ምክሮች (6፥1–10)።
   4. ማጠቃለያ (6፥11–18)

ምዕራፍ 1

ሰላምታ (1፥1–5)

1 ጳውሎስ በእግዚአብሔርና በኢየሱስ ክርስቶስ *ሐዋርያ* እንዲሆን በቀጥታ የተሾመ ሰው ነበር። ይህን ኀላፊነት በሌሎች ሰዎች አማካይነት አልተቀበለም። በአዲስ ኪዳን ሐዋርያ ማለት ወንጌልን ለመስበክና ቤተክርስቲያንን ለመመሥረት ከክርስቶስ ልዩ የሆነ ሥልጣን የተቀበለ ሰው ነው። በአዲስ ኪዳን የነበሩ ብዙዎቹ ሐዋርያት የክርስቶስን ትንሣኤ በዓይናቸው የተመለከቱ ናቸው። ጳውሎስም በደማስቆ የነበሩ ክርስቲያኖችን ለማሳደድ ሲጓዝ ኢየሱስን አይቷል (የሐዋ. 9፥3–6፤ 26፥12–15፤ 1ቆሮ. 15፥8 ይመለከቷል)። የዚያን ጊዜ አይሁድ ላልሆኑ ሐዋርያ እንዲሆን ከኢየሱስ የሐዋርያነትን ሹመት ተቀብሏል (የሐዋ. 9፥15፤ 26፥16–18)። ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች፥ ለእኛም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ሙሉ ሥልጣን ይህን መልእክት ጽፎአል። ስለዚህ የገላትያ ሰዎች የጳውሎስን ደብዳቤ ልብ ሊሉ ይገባቸዋል፤ እኛም እንዲሁ (ሮሜ 1፥1፤ ኤፌ. 1፥1 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

ጳውሎስ የተጠራው በኢየሱስና በእግዚአብሔር አብ እንደሆነ አስተውሏል። ክርስቶስና አብ አንድ አምላክ ናቸው። ሁልጊዜ በአንድነት ይሠራሉ። በአንዳንድ ቁጥሮች ኢየሱስ ብቻ፥ በሌሎች ደግሞ እግዚአብሔር አብ ብቻ ቢጠቀሱም ሁልጊዜ ሥራቸውን በአንድነት እንደሚሠሩ ማስተዋል ይኖርብናል። ዛሬ እኛ ክርስቲያኖች እንደ ጳውሎስ ክርስቶስን ልናገለግል ተጠርተናል። እንደ ጳውሎስ የተለየ ሥልጣን ባይኖረንም፥ ደቀ መዛሙርት እንድንሆንና ከክርስቶስ ጋር እንድንወርስ ተመርጠናል። የተለዩ ሐዋርያት ብቻ የእግዚአብሔርን ሥራ እንደሚሠሩ አንጠብቅ። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የምንሠራለትን ሥራ ሰጥቶናል። ይህንን ሥራ እንድንሠራም በመንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልገውን ጸጋና ኃይል ሰጥቶናል። ኢየሱስ ራሱ «. . . *በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና*» ብሏል (ዮሐ. 14፥12)።

2 በዚህ ቁጥር ለየትኞቹ የገላትያ አብያተክርስቲያናት እንደጻፈ አይታወቅም፤ አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ጳውሎስ የጻፈው በደቡብ ገላትያ ወደሚገኙ የጲስዲያ፥ አንጾኪያ፥ ኢቆንዮን፥ ልስጥራና ደርቤን የሚባሉ ከተሞች እንደሆነ ይናገራሉ (የሐዋ. 13፥14፤ 14፥1፤ 6፤21–22፤ 16፥1–2 ይመለከቷል)። ጳውሎስ እነዚህን ከተሞች ሁሉ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ተልእኮው የጎበኛቸው ናቸው።

3 ጳውሎስ መልእክቱን የሚያነቡ ሰዎች *ጸጋንና ሰላምን* እንዲያገኙ ይጸልያል፤ ጸጋና ሰላም ዋና ዋና የሆኑ የወንጌል አዕማድ ናቸው። በመጀመሪያ ጸጋ ከዚያም ሰላም፤ ጸጋ ሁልጊዜ የመጀመሪያ ነው። ማንኛውም ነገር ምንጩ ጸጋ ነው። የተጠራነው በጸጋ ነው። በጸጋ ኃጢአታችን ይቅር ተባለ፥ በጸጋ ዳንን፥ በጸጋ ጸደቅን፥ ቅድስናንም አገኘን፤ በፀጋ ከእግዚአብሔር ጋር የመሆን *ሰላም* አለን። ከጸጋ ውጭ የክርስቶስ ወንጌል የለም። በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት ክርስቶስ ወደ ምድር መጣ፤ *ስለ ኃጢአታችንም ስርየት ራሱን ሰጠ* (ቁ. 4)። ጸጋ ብድራት ያይደለ ወሰን የሌለው የእግዚአብሔር የፍቅርና የምሕረት ነጻ ስጦታ ነው። ስለዚህ ጸጋ፥.ክብርን ለእግዚአብሔር መስጠትና ማመስገን አንተው (ሮሜ 1፥7፤ ኤፌ. 1፥2፤6 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

እንዲሁም ጸጋና ሰላም *ከእግዚአብሔር አብና ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ* እንደሚመጡ እናስተውል። እግዚአብሔርና፡ ክርስቶስ አንድ ናቸው (ዮሐ. 10፥30 እና ማብራሪያውን፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአስተምህሮ ዳሰሳው የተጻፈውን ይመለከቷል)።

4–5 ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ራሱን ሰጠ፤ የእርሱ መሥዋዕትነት ለደኅንነታችን ሙሉና በቂ ነው። ለደኅንነታችን እኛ የምናደርገው ነገር የለም፤ ነገር ግን እምነታችን በክርስቶስ ላይ መሆን ይኖርበታል።

ክርስቶስ ከዚህ ክፉ ዓለም አዳነን፥ ይህ ዓለም የሰይጣን መንግሥት ነው፤ ሰይጣንም የዚህ ዓለም ገዢ ነው (ዮሐ. 16፥11)። ክርስቶስ እኛን ከዚህ ዓለም አላወጣንም፤ ነገር ግን ከዚህ ክፉ ዓለም አዳነን (ዮሐ. 17፥15)።

ሌላ ወንጌል የለም (1፥6–10)

6–7 ጳውሎስ በገላትያ ክርስቲያኖች ባሕርይ እጅግ መደነቁን ያሳያል። የገላትያ ሰዎች ከቅርብ ጊዜ በፊት የጸጋ ወንጌልን ተቀብለው ነበር፤ አሁን ደግሞ በፍጥነት ከዚህ ወንጌል ፊታቸውን መመለስ ጀመሩ።

ከኢየሩሳሌም የመጡ አንዳንድ አይሁድ ክርስቲያኖች የገላትያ ክርስቲያኖችን ሌላ ወንጌልን እንዲከተሉ ጥረት ያደርጉ ነበር። ይህ «ወንጌል» ደኅንነት በጸጋ ሳይሆን በሥራ እንደሚገኝ የሚናገር ሲሆን፥ የገላትያ ክርስቲያኖችን ግራ አጋብቶአቸዋል (ቁ. 7)። ጳውሎስ ግን የእነርሱ «ወንጌል» እውነተኛ ወንጌል እንዳልሆነ በመናገር እውነተኛው ወንጌል ደኅንነት በጸጋ ብቻ እንደሚገኝ የሚገልጽ መሆኑንም ተናገረ።

እነዚህ የገላትያ ክርስቲያኖች የሚያደርጉት የሚያሳዝንና የሚያስፈራ ነገር ነው። በጳውሎስ ስብከት የእግዚአብሔርን ነጻና ወሰን የለሽ ጸጋ ተቀብለዋል። አሁን ግን ጳውሎስንና የጠራቸውን እግዚአብሔርን ዘነጉ። የእግዚአ ብሔርን ጸጋ ተቃወሙ፥ አቃለሉትም።

ጳውሎስ *የክርስቶስን ወንጌል ለማጣመም ለሚሞክሩት ሐሰተኛ መምህራን* ነው የተቃውሞ ደብዳቤ የጻፈው። የእነዚህ መምህራን ትምህርት ክርስቶስ ብቻ አያድንም የሚል ነው። ስለዚህ ለመዳን የአይሁድን ሕግ መፈጸም አስፈላጊ ነው፤ እንዲህ ያለው ትምህርት የክርስቶስን ጸጋ ከንቱ የሚያደርግ ነው። ጸጋ ከወንጌል ከተለየ ወንጌል መሆኑ ይቀራል። ጳውሎስም ከዚህ የተነሣ መንፈሳዊ ልጆቹ ከእውነተኛው ወንጌል እንዲርቁ አይፈልግም።

ልናስተውል የሚገባን፤ ጳውሎስ እዚህ ቦታ የጻፈው የአይሁድን ሕግ መጠበቅ ለመዳን አስፈላጊ ነው፤ የሚለውን የስህተት ትምህርት ለሚያስተምሩ አንዳንድ አይሁድ ክርስቲያኖች ነው። በዚህ ዘመንም ቤተክርስቲያናትን ሊያናውጥ የሚችል የስህተት ትምህርት ሊኖር እንደሚችል ይህ መልእክት ምሳሌ ይሆንልናል። በየትኛውም አገር እንገኝ ለመዳን አንዳንድ ሕግጋትን ወይም ሃይማኖታዊ ወጎችንና ልማዶችን መፈጸም እንዳለብን የሚያስተምሩ አሉ። ይህ እጅግ አደገኛ የሆነ የስህተት ትምህርት ነው። እውነተኛው ግን ሰው የሚድነው በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው የሚለው ነው። ይህ የክርስቶስ ወንጌል መሠረት ነው።

8–9 ከዚህ የምንማረው የእግዚአብሔር ሥራ፥ የእግዚአብሔር ወንጌል እንዴት ትልቅና አስፈላጊ እንደሆነ ነው። የእግዚአብሔርን ወንጌል በማንኛውም መንገድ በየትኛውም አቅጣጫ ልንቀይረው አይገባንም። ሰባኪ ወይም አስተማሪ፥ መልአክ እንኳ ቢሆን የእግዚአብሔርን ቃል የመለወጥ ሥልጣን የለውም። የእግዚአብሔርን ቃል መስበክና ማስተማር ከባድና አስፈሪ የሆነ ኀላፊነት ነው። እኛም በታማኝነት ልንሰብከውና ልናስተምረው ይገባናል፤ ምክንያቱም ወንጌልን መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈበት ዓላማ በመጻረር ከሰበክን በእግዚአብሔር የተረገምን እንሆናለን። ቃሉን የሚሰሙት ከአንዱ እውነተኛ ወንጌል ጋር ሊጣበቁና ከሐሰተኛ መምህራን ራሳቸውን ሊጠብቁ ይገባል።

10 በገላትያ የነበሩት የጳውሎስ ተቃዋሚዎች ጳውሎስ የሚጥረው ሰዎችን ደስ ለማሰኘት ብቻ ነው ብለው ከሰውታል። ጳውሎስ የአይሁድ ሕግን መከተል አያስፈልግም ብሎ የሚያስተምረው፤ ከአሕዛብ ወገን የሆኑትን የገላትያ ሰዎች ደስ ለማሰኘትና ደኅንነትን በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያደርገው ጥረት ነው ይላሉ።

ጳውሎስ ግን ሰዎችን ደስ ለማሰኘት እንደማይሞክር ተናግሯል (1ጢሞ. 2፥6)። በዚህ መልክቱ ጳውሎስ የገላትያ ክርስቲያኖችን በብርቱ ገሥጾአቸዋል። ሰዎችን ደስ እያሰኙ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን በጣም የሚያስቸግር ነገር እንደ ሆነ ጳውሎስ በዚህ ቦታ ተናግሯል። ሌሎች ሰዎች ምንም ቢያስቡ የክርስቶስ አገልጋይ የሆኑ ወንጌልን በታማኝነት ሊሰብኩ ይገባል (1ተሰ. 2፥4)። የሰባኪ ዋነኛ ዓላማ ክርስቶስን ማክበርና ሰዎችን ወደ ደኅንነት መንገድ መምራት ነው (1ቆሮ. 9፥19፥22–23)።

የጳውሎስ በእግዚአብሔር መጠራት (1፥11–24)

11–12 በእነዚህ ቁጥሮች ጳውሎስ እውነተኛ ሐዋርያ እንደ ሆነ ለገላትያ ሰዎች ይናገራል። የሚሰብከው እውነተኛ ወንጌል ሲሆን ይህንንም የተቀበለው በቀጥታ *ከኢየሱስ ክርስቶስ በራእይ* ነው (ቁ. 12)። ጳውሎስ ይህን ራእይ በመጀመሪያ የተቀበለው ከሞት የተነሣው ኢየሱስ በደማስቆ መንገድ ሲገለጥለት ነው (የሐዋ. 9፥3–5)።

የክርስቶስ ወንጌል በሰዎች የተፈጠረ ልብ ወለድ አይደለም፤ ከአይሁድ እምነትና ከክርስትና እምነት በስተቀር በዓለም ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሃይማኖት ከሰዎች ፍልስፍናና ሐሳብ የተወለዱ ናቸው። የክርስቶስ ወንጌል ግን እግዚአብሔር ራሱ ያደረገው የምሥራች ነው። ስለ እግዚአብሔርና ደኅንነት ስለሚገኝበት መንገድ በቂና የመጨረሻው ፍጹም እውነት ነው።

ክርስቲያኖች በመጀመሪያ ወንጌልን የተቀበልነው ሌሎች ሰዎች ወንጌልን ሲሰብኩ ሰምተን ወይም መጽሐፍ ቅዱስን አንብበን ነው። አንዳንድ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በቀጥታ ከክርስቶስ በሆነ ትምህርት ወንጌልን እንቀበላለን። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በቀጥታ ትምህርትን ስንቀበል ከቅዱስ ቃሉ የተለየ ወይም አዲስ መልእክት አይመጣም፤ መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ መልእክት ነው ያለው።[1] ጳውሎስ ግን ወንጌልን የተቀበለው አዲስ ኪዳን ከመጻፉ በፊት በቀጥታ ከክርስቶስ ነው። ጳውሎስ ወንጌልን ከሌላ ሰው የተቀበለ ቢሆን ኖሮ ከዚያ ሰው «ያነሰ» ይሆን ነበር ማለትም «ተማሪ ሐዋርያ» ይሆን ነበር። ጳውሎስ እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት (እንደ ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ያዕቆብ) በጌታ የተመረጠ ሐዋርያ ነው (ቁጥር 9)። እርሱ እውነተኛ ሐዋርያና የሚሰብከውም ወንጌል እውነተኛውን ወንጌል ነው። ስለዚህ የገላትያ ክርስቲያኖች ይህን ሊጠራጠሩ አይገባም።

የጳውሎስን መልእክት የምናጠና እኛም አንጠራጠረው። ዛሬ በዓለም ላይ ብዙ ተጠራጣሪዎችና የማያምኑ አሉ። «ሰው እውነትን ሊያውቅ አይችልም» እንዲሁም «ሁሉም ሃይማኖቶች መልካምና የሚጠቅሙ ናቸው፤ ስለዚህ ሁሉም ወደ መንግሥተ ሰማያት ይመራሉ» ይላሉ። እነዚህ ሰዎች ተሳስተዋል፤ የክርስቶስ ወንጌል ብቻውን እውነት የሆነ ወንጌል ነው። ኢየሱስ *«እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም»* በማለት ተናግሯል (ዮሐ. 14፥6)።

13–14 ጳውሎስ በሕይወቱ የተከናወነውን ታላቅ ለውጥ ለገላትያ ክርስቲያኖች ያስታውሳቸዋል። በመጀመሪያ እጅግ በከፋ ሁኔታ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ያሳድድ ነበር (የሐዋ. 8፥3፤ 9፥1–2፤ 22፥4)። የአይሁድ ሃይማኖት የሆነውን *ይሁዲነት*[2] በጥብቅና ለሃይማኖቱ በመቅናት ይከተል ነበር (የሐዋ. 22፥3፤ ፊል. 3፥4–6)። በአይሁድ እምነት አንድ ሰው ሊድን የሚችለው የአይሁድን ሕግጋት ሲፈጽም ብቻ እንደ ሆነ ያስተምራል፤ ጳውሎስም እንዲሁ ያምን ነበር። አሁን ግን የጳውሎስ ዋና መልእክት ሰው በጸጋ በክርስቶስ በማመን ብቻ ይድናል የሚል ነው። እጅግ በከፋ ሁኔታ ያሳድዳቸው የነበሩት ሰዎችም የዚህ ክርስቶስ ተከታዮች ናቸው። በጳውሎስ ሕይወት እንዲህ ያለውን ለውጥ ሊያመጣ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

15 ጳውሎስ ከመወለዱ በፊት ሐዋሪያው እንዲሆንለት እግዚአብሔር መርጦት ነበር። እግዚ አብሔር እያንዳንዳችንን ከመወለዳችን አስቀድሞ መርጦናል (መዝ. 139፥13–16)። ይልቁንም *ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ* እግዚአብሔር መርጦናል (ኤፌ. 1፥4)። እግዚአብሔር እኛን የመረጠን እንደ ጸጋው እንጂ እንደ ሥራችን ወይም ጠቃሚነታችን አይቶ አይደለም። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ *በጸጋው የጠራኝ* ይላል (1ቆሮ. 15፥9–10 ይመለከቷል)። ጥሪያችንን በእኛ ማንነት ያገኘነው ሳይሆን ከመወለዳችን በፊት እግዚአብሔር ስለጠራን ነው።

እግዚአብሔር የጠራን ለምን ጉዳይ ነው? በመጀመሪያ እንድንድን ጠራን፥ ሁለተኛ ከመዳናችን ጋር የእርሱ ልጆች እንድንሆን (ኤፌ. 1፥5)፥ ማለትም ከክርስቶስ ጋር አብረን የምንወርስ እንድንሆን ጠራን (ሮሜ 8፥17)። ሦስተኛ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን ሥራ ወይም ተግባር እንድንፈጽም ጠራን (ኤፌ. 2፥10)። የጳውሎስ የተለየ አገልግሎት ወንጌልን ለአሕዛብ መስበክ ነበር (ቁጥር. 16)።

16 እግዚአብሔር ልጁን *በእኔ*[3] ለመግለጥ ወደደ ሲል፥ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ጽፎአል። ክርስቶስ «ለእኛ» መገለጡ ብቻ በቂ አይደለም፤ «በእኛም» መገለጥ አለበት። የክርስቶስ መንፈስ በውስጣችን ማደር አለበት። አለዚያ እምነታችን ደካማ ሕይወታችንም መፈሳዊ ኃይል የሌለው ይሆናል።

17 ጳውሎስ የሕይወት ለውጥ ካገኘ በኋላ ለሦስት ዓመታት እንደ ጴጥሮስና የጌታ ወንድም ከሆነው ያዕቆብ ካሉት ሐዋርያት ጋር አልተገናኘም። ከሌላም ሰው ምንም ዓይነት ትምህርት አልተቀበለም። እርሱ በቀጥታ ከእግዚአብሔርና ከክርስቶስ የተማረ ነበር።

ከሕይወቱ ለውጥ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ ወደ ዓረብ አገር ሄዶ ነበር። ነገር ግን እዚያ ምን ያደርግ እንደነበር የሚታወቅ ነገር የለም። ምናልባት እግዚአብሔር ለጠራው ሥራ የሚያዘ ጋጀውን፤ ጸሎትና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በማጥናት ጊዜውን ያሳልፍ ይሆናል።

የሕይወት ለውጥ አግኝቶ በዓረብ አገር ካደረገው ቆይታ በኋላ በመጀመሪያ ወደ *ደማስቆ* ተመለሰ። ከዚያም ሦስት ዓመታት በደማስቆ[4] ከቆየ በኋላ ወደ *ኢየሩሳሌም*[5] ወጣ (ቁ. 18)።

ከዚህ የምንመለከተው ጳውሎስ የሚዘጋጅበት ጊዜ አስፈላጎት እንደ ነበር ነው። ይህም ለሁላችን የሚያስፈልግ ነው። በአንድ ጊዜ የበሰሉ ክርስቲያኖች አንሆንም። እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ሊያዘጋጀን ይፈልጋል፤ ይህ ደግሞ ጊዜን የሚጠይቅ ነው። በብሉይ ኪዳን የአይሁድ ታላቅ መሪ የነበረውን ሙሴን ለማዘጋጀት አርባ ዓመታትን ወሰዱል። ሙሴ እድሜው ሰማንያ ዓመት እስኪሞላ ድረስ እግዚአብሔር ወደ ጠራው ሥራ አልተሰማራም (ዘጸ. 7፥7፤ የሐዋ. 7፥23፤30)። ስለዚህ በቅጽበት ለአገልግሎት እንበቃለን ብለን አናስብ።

የተጠራነው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ለአገልግሎት የምንዘጋጀውም በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። እያንዳንዳችን በየእለቱ ሳያቋርጥ እንዘጋጃለን፤ ይህም እስከምንሞት ድረስ የሚቀጥል ነው፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ጥልቀትና ክብር በይበልጥ ይገባናል።

ሁሉ በጸጋ ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ ከዋክብትና ዓለማት በምህዋራቸው ይጠበቃሉ። በሙቀት ብዛት እንዳንቀልጥ ወይም በቅዝቃዜ ምክንያት በረዶ እንዳንሆን በመሬትና በፀሐይ መካከል ያለው ርቀት በእግዚአብሔር ጸጋ የተጠበቀ ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ እንተነፍሳለን፥ እንበላለን፥ እንስቃለን ደግሞም እንኖራለን። እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም የሰው ደካማ ጉልበት አያስፈልገውም። እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅርም ለእርሱ በምናደርገው

---

[1] *መንፈስ ቅዱስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሁልጊዜ ይስማማል፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በመንፈስ ቅዱስ ብርሃን/ግልጠት/ ነውና። ለተጨማሪ ማብራሪያ የአጠቃላይ ማብራሪያውን «መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንዴት ወደ እኛ ደረሰ?» የሚለውን ይመለከቷል።*

[2] *ይሁዲነት የአይሁድ ሕዝብ የሚከተለው ሃይማኖትና የኑሮ ዘይቤ ነው።* ክርስቶስ ከመምጣቱ ሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ እግዚአብሔር አብርሃምን የአይሁድ ሕዝብ አባት እንዲሆን ጠራው። እግዚአብሔር አይሁድን የተለዩ ሕዝቦቹ እንዲሆኑ መረጠ። የአይሁድ ሕግ የሚባለውን የራሱን ሕግ ሰጣቸው። የአይሁድ ቅዱሳን መጻሕፍት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ። ብሉይ ኪዳን የአይሁድን ታሪክ ይዘግባል፤ የአይሁድን ሕግና የአይሁድ ነቢያትን መጽሐፍ ይዟል (በአስተምህሮ ዳሰሳው የብሉይ ኪዳን ማጠቃለያን ይመለከቷል)።

[3] *በእኔ* በሚለው ቃል ምትክ ሌሎች ትርጉሞች «ለእኔ» በማለት ጽፈዋል። ሆኖም በግሪክ ቋንቋ ቃሉ *በእኔ* ይላል። ጳውሎስ በትክክል የጻፈው ይህንኑ ነው።

[4] *ደማስቆ የመካከለኛ ምሥራቅ ሶሪያ ዋና ከተማ ነች።*

[5] *ኢየሩሳሌም የእስራኤል ደቡባዊ ክፍለ አገር የነበረችው የይሁዳ ዋና ከተማ ነበረች። ኢየሩሳሌም ለአይሁድ ዋና ከተማ፥ ቅዱስ ከተማ፥ እንዲሁም ለሃይማኖታዊ (ለመንፈሳዊ) ሕይወታቸው ማዕከል ነበረች። እስከ አሁንም ድረስ እንዲሁ ናት። ዛሬ ኢየሩሳሌም በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ዋና ከተማ ነች።*

ሥራ ላይ የተመሠረተ አይደለም። እርሱ የሚወደን በእኛነታችን ነው፤ ይህም የእርሱ ልጆች በመሆናችን ነው። የእርሱ ልጆች የሆንውም በጸጋው በኩል ነው። ስለዚህ ወንድሞችና እህቶች ሕይወታችንን በሙሉ፤ ክብር ለሆነው ጸጋ ለመኖር እንፈልግ (ኤፌ. 1፥6)።

18 ጳውሎስ የሕይወት ለውጥ ካገኘ ከሦስት ዓመት በኋላ ከጴጥሮስ[6] ጋር ተገናኘ። ጳውሎስ ሐዋርያነትን ከጴጥሮስ አልተማረም። ጳውሎስና ጴጥሮስ በሐዋርያነት ሥልጣን እኩል ነበሩ። ታዲያ ጳውሎስ ይህን መጻፍ ለምን አስፈለገው? ምክንያቱ በገላትያ የነበሩት የጳውሎስ ተቃዋሚዎች ጴጥሮስ እውነተኛ፥ ጳውሎስ ግን ሐሰተኛ ሐዋርያ እንደ ሆኑ ይናገሩ ስለ ነበር ነው።

ጳውሎስ ከጴጥሮስ ጋር ለመገናኘት ያደረገው የመጀመሪያ ጉዞ በሐዋርያት ሥራ 9፥26–30 ላይ ተገልጾአል።

19–20 በዚህ ቦታ የተጠቀሱት ሌሎች ሐዋርያት (የአስቆሮቱ ይሁዳን ሳይጨምር) አሥራ ሁለቱ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ናቸው። ነገር ግን ከአሥራ ሁለቱ በተጨማሪ ሌሎች ሐዋርያት ነበሩ፤ ከእነርሱም የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ ይገኝበታል (1ቆሮ. 15፥7)። ጳውሎስ ይህን መልእክት ለገላትያ ክርስቲያኖች በሚጽፍበት ጊዜ ያዕቆብ በኢየሩሳሌም የነበረችው «እናት ቤተ ክርስቲያን» ዋና መሪ ነበር (የሐዋ. 21፥18፤ ገላ. 2፥9)። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ እንደሚለው በዚያን የጉብኝት ጊዜ ከያዕቆብ በስተቀር ከማንም ሐዋርያት ጋር አልተገናኘም።

21 ጳውሎስ በኢየሩሳሌም የቆየው ለዐሥራ አምስት ቀናት ብቻ ነበር (ቁ. 18)። በይሁዳ ዙሪያ ባሉት ስፍራዎች አልሰበከም። ነገር ግን ይህን አካባቢ ትቶ ከአይሁድ ወገን ውጪ ለሆኑት ወንጌልን ለመስበክ ወደ ሶሪያና ኪልቅያ[7] ሄደ።

22–24 በእስራኤል ደቡባዊ ክፍል በይሁዳ ያሉት አብያተክርስቲያናት ጳውሎስን (ወይም ሳውልን) የሚያስታውሱት በአሳዳጅነቱ ነው። ስለ ክፉ ሥራው በሙሉ ሰምተው ነበር። ጳውሎስ በይሁዳ ወንጌልን ስላልሰበከ የይሁዳ ክርስቲያኖች የተለወጠውንና የክርስቶስ ሐዋርያ የሆነውን የጳውሎስን አዲስ ሕይወት የማየት እድል አልገጠማቸውም፤ ቢሆንም፥ ጳውሎስ በሶሪያና በኪልቅያ የሰበከውን ስለሰሙ ስለ እርሱ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። ነገር ግን ጳውሎስ እንዲያውም ያላሳደዳቸው የገላትያ ክርስቲያኖች ከእርሱ ራቁ ከመጀመሪያ አንሥቶ እንደ አባት ይወዳቸው የነበሩት የገላትያ ሰዎች እርሱን ተቃወሙ።

ምዕራፍ 2

የጳውሎስ በሐዋርያት ተቀባይነት ማግኘቱ (2፥1–10)

1 አብዛኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት በዚህ ቁጥር የተጠቀሰው ወደ ኢየሩሳሌም የተደረገው ጉዞ በሐዋርያት ሥራ 15፥1–29 ከተጠቀሰው ጉዞ ጋር አንድ ነው ይላሉ።[8] በዚህ ጉዞ ከጳውሎስ ጋር ከተጓዙት ሰዎች አንዱ *በርናባስ* ነበር፤ ይህ ሰው በጳውሎስ የመጀመሪያ የተልእኮ ጉዞው ላይ የቅርብ አጋሩ ነበር (የሐዋ. 9፥27፤ 11፥22–26፤ 13፥2–3)። ሌላኛው አጋር ደግሞ በ2ቆሮ. 7፥6–7፥13 እና 8፥16–17፥23 ላይ የተጠቀሰው ወጣቱ ቲቶ ነበር። በኋላም በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰውን «የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ለቲቶ» ጻፈለት።

ወደ ኢየሩሳሌም የተደረው ጉዞ ዓላማ በግልጽ ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ 15፥1–2 ላይ ተገልጾአል፤ ጳውሎስ በነበረበት ዘመን ቀድሞ የአይሁድ እምነት ተከታዮች በነበሩት ክርስቲያኖችና ወደ ክርስትና በመጡት አሕዛብ መካከል ከፍተኛ የሆነ አለመግባባት ተነሥቶ ነበር። የአይሁድ ክርስቲያኖች ወደ ክርስትና የመጡት አሕዛብ የአይሁድን ሕግ መፈጸም አለባቸው የሚል ክርክር ነበራቸው (የሐዋ. 15፥1፤5)። ጳውሎስ ግን ከአሕዛብ ለሆኑት አማኞች በመወገን የአይሁድ ክርስቲያኖችን ትምህርት በብርቱ ተቃውሟል። የእርሱ ክርክር ከአሕዛብ ወገን ወደ ክርስትና የመጡ ሰዎች የአይሁድን ሕግ የመፈጸም ግዴታ የለባቸውም የሚል ነበር። ስለዚህ ከኢየሩሳሌምና ከአካባቢዋ ወደ ገላትያ የሄዱት የአይሁድ ክርስቲያኖች የገላትያ ክርስ ቲያኖች የሙሴን ሕግ መፈጸም እንዳለባቸው ማስተማር ስለ ጀመሩ ይህን የተሳሳተ ትምህ ርታቸውን ለመቃወም በኢየሩሳሌም ወደምትገኘው ቤተክርስቲያን መሪዎች ለመሄድ ወሰነ።

2 ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው *ከተገለጠለት ራእይ የተነሣ* ነበር። ይህም ራእይ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንዳለበት መንፈስ ቅዱስ የገለጠለት ነው። ጳውሎስ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ዋና ዋና በሆኑ ጉዳዮች ላይ መንፈስ ቅዱስ በሚገለጥለት ልዩ ራእይ እየተመራ ይሄድ ነበር (የሐዋ. 16፥6–10፤ 22፥17–18፤ 27፥23–26)። በኢየሩሳሌም መሪዎች ፊትም በአሕዛብ መካከል ስለሚሰበከው ወንጌል አስታወቀ። ይህ ወንጌል ምን ነበር? ሰው የሚድነው የአይሁድን ሕግ በመጠበቅ ሳይሆን፥ በጸጋ እንደ ሆነ የሚናገረው በእምነት የሚገኝ የክርስቶስ የጸጋ ወንጌል ነበር። በኢየሩሳሌም የሚገኙት የአይሁድ[9] ክርስቲያኖች መሪዎች የጳውሎስን ትምህርት ባይቀበሉ የዚያን ጊዜ በእርግጥ የጳውሎስ ስብከት ከንቱ ይሆን ነበር። እስካሁን ሩጫውን በከንቱ የሚሮጥ ሰው ይሆን ነበር። ጳውሎስ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህን የተናገረው ለብቻቸው ነበር። በከተማው ካሉት ከአይሁድ ክርስቲያኖች መካከል አለመግባባትና ብጥብጥ እንዲነሣ ጳውሎስ አልፈለገም።

3 ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር ያደረገው ስብሰባ የተሰካ ነበር። ከነበሩት ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ አሕዛብ ክርስቲ ያኖች እንደ አይሁድ ሕግ *መገረዝ* አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚል ሐሳብ ነበር። የአይሁድ ክርስቲያኖች የግድ አስፈላጊ ነው ሲሉ፥ ጳውሎስ ደግሞ አስፈላጊ አይደለም ይል ነበር። በመጨረሻም የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች በጳውሎስ ትምህርት ተስማሙ። ይህንንም ማስረጃ በማድረግ ቲቶ እንዲገረዝ የግድ አላሉትም። (ቲቶ *የግሪክ*[10] ሰው እንጂ አይሁዳዊ አልነበረም) ቲቶ ባይገረዝም እንደ ክርስቲያን ወንድም ተቀብለውታል።

ዛሬ ለእኛ ይህ ትንሽ ነገር መስሎ ሊታየን ይችላል፤ ነገር ግን በክርስትና ሃይማኖት ታሪክ በኢየሩሳሌም የተደረገው ይህ ስብሰባ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ስብሰባ ነበር። ምክንያቱም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው የሚድነው የትኛውንም ሕግ በመጠበቅ ወይም ሰው ሰራሽ የሆነ ወግን በመፈጸም ሳይሆን በጸጋና በእምነት አማካይነት ብቻ እንደ ሆነ በአጠቃላይ በቤተክርስቲያን ገሀድ ወጥቷል። ይህ የክርስቲያኖች ወንጌል ነው፤ የክርስትና እምነትን በዓለም ውስጥ ካሉ ሌሎች ሃይማኖቶችም የሚለየው ይህ ነው። በሌሎች ሃይማኖቶች ትምህርት ሰው ለመዳን አንዳንድ ግዴታዎችን፥ ወጎችንና ሥርዓቶችን መፈጸም ይገባዋል። እነዚህ ሃይማኖቶች የተመሠረቱት አንድ ሰው በሚያደርገው ጥረት በሚያገኘው ዋጋ ላይ ነው። የክርስትና እምነት ግን ከዚህ ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው። እንደ ክርስቶስ ወንጌል ከሆነ ማንም በሥራው ደኅንነትን ማግኘት አይችልም። ደኅንነት በጌታ ኢየሱስ

---

6 ጴጥሮስ በሚለው ስም ፈንታ አንዳንድ ትርጉሞች «ኬፋ» ይላሉ። ኬፋ በግሪክ ቋንቋ ጴጥሮስ ማለት ነው።

7 ኪልቅያ፥ የአሁኗ ደቡብ ቱርክ ስትሆን፥ በደቡብ ሶርያ የምትገኝ የሮም ግዛት ነበረች።

8 አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ከዚህ አመለካከት ጋር አይስማሙም። በዚህ ቁጥር የተጠቀሰው ጉዞ በየሐዋ. 11፥29–30 ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ይናገራሉ።

9 እያንዳንዱ አይሁዳዊ ወንድ በተወለደ በስምንተኛ ቀን መገረዝ ይጠበቅባቸዋል ዘፍ. 17፥9–14። ጳውሎስ በነበረበት ዘመን መገረዝ አይሁድ መሆንን የሚያረጋግጥ ውጪያዊ ማስረጃ ነበር። ለተጨማሪ ማብራሪያ በቃላት መዘርዝር ግርዘት የሚለውን ይመለከቷል።

10 የግሪክ ሰዎች በደቡባዊ አውሮፓ በምትገኝ አገር የሚኖሩ ናቸው። በአዲስ ኪዳን ዘመን ግሪክ የሮም ግዛት አንድ ክፍል ነበረች። የግሪክ ሰዎች አይሁዶች አልነበሩም። የዳበረ ባሕልም ነበራቸው። በዚህ ዘመን በመካከለኛው ምሥራቅ የነበሩ አብዛኛዎቹ ምሁራን የግሪክ ቋንቋ ይናገሩ ነበር። አዲስ ኪዳንም በመጀመሪያ የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ነበር።

ክርስቶስ በማመን የሚገኝ የእግዚአብሔር ጸጋ ነፃ ስጦታ ነው።

4 ደኅንነትን ለማግኘት የአይሁድን ሕግ· መፈጸም የግድ ነው ብለው የሚያስተምሩትን፤ ጳውሎስ *ሐሰተኛ ወንድሞች* በማለት ይጠራ ቸዋል። እነርሱ እውነተኛ ክርስቲያኖች አልነበሩም። ጳውሎስም ስለ እነርሱ እንደ ሰላዮች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው ገብተዋል ሲል ጽፎአል። *የበግ ለምድ እንደ ለበሱ ተኩላዎች* (ማቴ. 7፥15) የሰይጣን አገልጋዮች ነበሩ። ከሰይጣን ግዛት ያመለጡትን አዳዲስ ክርስቲያኖች የሰይጣን *ባሪያዎች* እንዲሆኑ ያስገድዱቸው ነበር። የአዲስ ክርስቲያኖችን ነፃነት በመግፈፍ እንደ ገና የሕግ እስረኛ ሊያደርጓቸው ይሞክራሉ። ሰይጣን ደኅንነታችንን ሊወስድብን እንደማይችል ያውቃል (ዮሐ. 10፥27–29)። ስለዚህ ይህን ነፃነታችንንና ደስታችንን ሊወስድብን ይጥራል።

ሐሰተኛ ወንድሞችን ወይም ሐሰተኛ ነቢያትንና አስተማሪዎችን እንዴት ልናውቅ እንችላለን? ሁለት የማወቂያ መንገዶች አሉ። የመጀመሪያው በሚናገሩት ልናውቃቸው እንች ላለን (1ዮሐ. 4፥1–3)። ክርስቶስ የእግዚአ ብሔር ልጅ እንደ ሆነና በሥጋ ወደ ምድር እንደመጣ የሚያምን ማንኛውም ሰው እውነተኛ ወንድም ነው (ሮሜ 10፥9 ይመለከቷል)። ሁለተኛው መንገድ፥ በሚሠሩት ሥራ በፍሬአቸው ሐሰተኛ ወንድሞችን እናውቃቸዋለን (ማቴ. 7፥16–18)።

እውነተኛ ወንድሞች በተሳሳተ ትምህርት ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉን? አዎን፤ የኢየሱስ ዋነኛ ደቀ መዝሙር የነበረው ጴጥሮስ እንዲሁም በርናባስ በእነዚሁ የአይሁድ መምህራን ትምህርት ስህተት ውስጥ ገብተዋል (ቁ. 11–13)። ቢሆንም በአንድ ወቅት ጴጥሮስና በርናባስ ተሳስተው የነበሩ ቢሆንም ሐሰተኛ ወንድሞች አልሆኑም።

በዚህ ጉዳይ ልንወስደው የሚገባን ጥንቃቄ ወደ ስህተት የሄደውን ወንድማችንን መመለስ ግዴታችን ቢሆንም ሐሰተኛ ወንድም ብለን ለመጥራት መቸኮል የለብንም። ሐሰተኛ ወንድሞች ብለን የምንጠራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር የመጣ እግዚአብሔር እንደሆነ የሚቃወሙትን ነው።

በቤተክርስቲያን ውስጥ በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር ሌላውን ወገን ሐሰተኛ ወንድሞች ብለው ለመጥራት የሚቸኩሉና የተዘጋጁ አንዳንድ ሰዎች አሉ። በዚህ መንገድ በወንድሞቻችን ላይ ልንፈርድ አይገባንም (ማቴ. 7፥1) የሰውን ልብ የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነውና (ማቴ. 13፥24–30 ይመለከቷል)።

5 ከአይሁድ ወገን የነበሩ ወንድሞችን የስህተት ትምህርት በመቃወም ጳውሎስ ጸንቶ ቆሟል። በገላትያ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን በክርስቲያኖች ዘመን ሁሉ እውነቱ ተጠብቆ እንዲቆይ ጳውሎስ ለወንጌል እውነት ተሟግቷል።

6 ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም በሄደ ጊዜ ዋነኞች የሆኑት የቤተክርስቲያን መሪዎች በእርሱ መልእክት ላይ አንዳችም ነገር አልጨመሩም ነበር። ጳውሎስ የተሰጠውን ሥልጣን ተቀብለዋል። ከአሕዛብ ወገን የመጡ ክርስቲያኖች የአይሁድን ሕግ የግድ መጠበቅ አለባቸው አላሉም።

በኢየሩሳሌም የነበሩትን የቤተክርስቲያን መሪዎችንና ሐዋርያትን ጳውሎስ ከእርሱ በላይ አድርጎ አልቆጠራቸውም። ጳውሎስ የሐዋርያነቱን ሥልጣን የተቀበለው ከእነዚህ ሰዎች ሳይሆን በቀጥታ ከእግዚአብሔር ነበር። በሰዎች ዓይን ዋና መስለው ቢታዩም ይህ ለጳውሎስ ምንም አልመሰለውም። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያየው በዓለም ውስጥ ያላቸውን ስፍራ ሳይሆን በውስጣቸው ያለውን መንፈሳዊ ሁኔታ ነው።

ጳውሎስ በዚህ ቦታ ያስተማረው መሪዎቻችንን እንዳንታዘዝ ወይም እንዳና ከብራቸው ሳይሆን፥ እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት እርሱም መሪና ሐዋርያ እንደ ሆነ ማሳየቱ ነበር። ስለዚህ የእነርሱን ውሳኔ ለመከተል ግዴታ አልነበረበትም። ይሁን እንጂ፥ ዋነኞች ያልሆንን ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን ያሉትን መሪዎች ልንታዘዝ ይገባናል። እነርሱን ብቻ ሳይሆን አሠሪዎቻችንንና የመንግሥት ባለ ሥልጣናትንም መታዘዝ ይኖርብናል (ሮሜ 13፥1–2፤ 1ጴጥ. 5፥5)።

7–8 ጴጥሮስና ሌሎቹ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለወንጌል ሥራ አደራ እንደተሰጣቸው ጳውሎስም እንዲሁ ተሰጥቶታል። በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት *ለአይሁድ*[11] ወንጌልን እንደሰበኩ፥ ጳውሎስ *ለአሕዛብ*[12] ወንጌልን እንዲሰብክ ተሹሟል። ስለዚህ እግዚአብሔር በሌሎቹ ሐዋርያት እንደሠራ በጳውሎስም ይሠራ ነበር። ጳውሎስና ሌሎች ሐዋርያት የሰበኩት አንድ ወንጌል እንጂ ሁለት ወንጌላት አልነበሩም።

9 የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በደስታ የጳውሎስንና የበርናባስን ሐዋርያነት ተቀብለው ለመስማማታቸው *ቀኝ እጃቸውን ሰጧቸው*።[13] ጳውሎስም *የተሰጠኝን ጸጋ አውቀው* ይላል፤ ይህም የሐዋርያነት ጸጋ ነበር (ኤፌ. 3፥7–8)። የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ዋና መሪዎች ያዕቆብ፥ ጴጥሮስ (ኬፋ) እና ዮሐንስ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ የቤተክርስቲያን አዕማድ ይላቸዋል። ዮሐንስ የኢየሱስ ተወዳጅ ደቀ መዝሙር በመባል የሚታወቅ ሲሆን የዮሐንስን ወንጌልና በስሙ የተጻፉትን ሦስት የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ጽፎአል።

እነዚህ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች ጳውሎስና በርናባስ ለአሕዛብ፥ እነርሱ ደግሞ ለአይሁድ ወንጌልን ሊሰብኩ ተስማ ምተዋል። ይህ ጥሩ ቅንጅት ነበር። አንዳንድ ክርስቲያኖች ለአንድ ሥራ ይጠራሉ፤ ሌሎች ደግሞ ለሌላ ሥራ በእግዚአብሔር ይጠራሉ። እግዚአብሔር ወደሚልከን ቦታ ለመሄድ ዝግጁ መሆን ይገባናል።

10 የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች ጳውሎስን አንድ ነገር እንዲያደርግ ለመኑት፤ ይህም ድኾችን እንዲያስብ። መሪዎቹ ይህን ሲሉ በኢየሩሳሌም ያሉትን ችግረኛ ክርስቲያኖች ማለታ ቸው ነበር። በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በአንዳንድ ስፍራ ጳውሎስ በአሕዛብ ክርስቲያኖች ዘንድ እየዞረ በኢየሩሳሌም ለነበሩ ችግረኛ ክርስቲያኖች ገንዘብ እንዳሰባሰበ ተጠቅሷል (የሐዋ. 11፥29–30፤ ሮሜ 15፥25–26)።

ጳውሎስ ጴጥሮስን ተቃወመው (2፥11–14)

11 *ጴጥሮስ ወደ አንጾኪያ*[14] *በመጣ ጊዜ ፊት ለፊት ተቃወምሁት።* በዚህ ክፍል በጳውሎስና በጴጥሮስ መካከል ስለ ተነሣው ከፍተኛ አለመግባባት እናነባለን። ጳውሎስ ፊት ለፊት መናገሩን እንጂ አለማማቱን እናስተውል። እኛም እንዲሁ ከወንድሞችና እህቶች ጋር በሚፈጠረው አለመስማማት ፊት ለፊት እንወቃቀስ። ወንድማ ችንንና እህታችንን በማማት ኃጢአት ውስጥ አንውደቅ። ጴጥሮስ ተሳስቶ ነበር። ስህተት እንዳደረገ ራሱ እንኳ ተቀብሏል። ስህተቱም ለራሱም ለሌሎችም የተገለጠ ነበር።

12 በጳውሎስና በጴጥሮስ መካከል የነበረው አለመግባባት በመሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ላይ ሳይሆን፥ ከባህርይ የተነሣ ነበር። ከአሕዛብ ወገን የመጡ ክርስቲያኖች የአይሁድን ወግና ሥርዓት የግድ መፈጸም የለባቸውም በሚለው ሐሳብ ጴጥሮስ ተስማምቷል። ከአይሁድ ወገን የሆነው ጴጥሮስ እንኳ የአይሁድን ወግ አይጠብቅም። በእርግጥ ኑሮው እንደ አሕዛብ ነበር (ቁ. 14)።

የጴጥሮስ ስህተት ምንድን ነበር? በቀላሉ በአንጾኪያ ካሉ አህዛብ ክርስቲያኖች ጋር መብላትን ስለተወ ነበር። ይህን ለምን አደረገ? ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ የመጡ አንዳንድ የአይሁድ «ወንድሞች» አይሁዳዊ ከአሕዛብ (ከአረማዊ) ጋር ለምግብ በአንድነት መቀመጥ የለበትም ስላሉ ነው። እነዚህ ሰዎች *ከተገረዙት ወገን* የሆኑ አይሁዳውያን ነበሩ። እነርሱም ለመዳን መገረዝ አስፈላጊ ነው ብለው ያስተምራሉ። ስለዚህ ጴጥሮስ እነዚህን ሰዎች በመፍራት ልክ ከአሕዛብ ክርስቲያኖች ጋር በማእድ ኅብረት *እንደማያደርግ ሰው ራቀ*።

---

11 አይሁድ በሚለው ቃል ፈንታ አንዳንድ ትርጉሞች «የተገረዙ» ይላሉ። ይህም በመጀመሪያው የግሪክ መጽሐፍ እንደተጻፈው ሲሆን በትርጉም አንድ ናቸው።

12 አሕዛብ የሚለው ቃል በመጀመሪያ የግሪክ መጽሐፍ «ያልተገረዙ» የሚል ሲሆን በትርጉም አንድ ናቸው።

13 ቀኝ እጅን መስጠት (መጨበጥ) በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ የኅብረት ምልክት ነው። በጳውሎስ ዘመንም እንዲሁ ነበር።

14 አንጾኪያ በሰሜን ሶሪያ ዋነኛ ከተማ ነች። በአንጾኪያ የቤተክርስቲያን መመሥረት በሐዋሪያት ሥራ 11፥19–26 ላይ ተዘግቦ ይገኛል።

በአይሁድ አመለካከት አረማውያን የረከሱ እንደሆኑ ይቆጠራሉ። ስለዚህ አይሁዶች ከአረማዊ ጋር መመገብ እንደ እነርሱ የረከሰ ያደርጋል ብለው ያምናሉ። አይሁዶች ወደ ክርስትና ከመጡ በኋላ እንኳ እንዲህ ያለው የተሳሳተ አመለካከት ከአእምሮአቸው ቶሎ አይወገድም። ጴጥሮስ ራሱን ከአረማውያን ክርስቲያኖች ማግለሉ ትክክል እንዳይደለ ያውቃል። ወደ ክርስትና የገቡ አይሁዶችና አረማውያን በእግዚአብሔር ፊት እኩል እንደ ሆኑ፥ በክርስቶስ አንድ እንደ ሆኑ ያውቃል (የሐዋ. 10፥27–28፤ 15፥7–9፤ ገላ. 3፥28፤ ቆላ. 3፥11 ይመለከቷል)። ነገር ግን ጴጥሮስ የጥንቱ ፍርሃቱና ወግ አሸንፎት ስህተት ላይ ጣለው። እኛም ከሌላው ክርስቲያን ጋር በብሔሩ ወይም በቆዳ ቀለም ምክንያት ኅብረት ላለመፍጠር ወይም ላለመመገብ ብንፈልግ በክርስቶስ ላይ ኃጢአት እንደ ሠራን እንወቅ።

13 በአንጾኪያ የነበሩ ክርስቲያን አይሁዶች ከጴጥሮስ *ግብዝነት* ጋር ተባበሩ። ይህ ግብዝነት የተባለበት ምክንያት እነዚህ ሰዎች በአንደበታቸው አይሁድና አረማዊ በክርስቶስ አንድ ናቸው እያሉ በተግባር ግን ክርስቲያን የሆኑትን አረማውያን የበታችና ርኩስ አድርገው ይቆጥሯቸው ነበር።

ከዚህ ሁኔታ እኛም በተለያዩ መንገዶች ወደ ተሳሳተ ነገር በቀላሉ እንዴት እንደምንነዳ እናስተውል። ታላላቅ መሪዎች የሚባሉት ጴጥሮስና በርናባስ እንኳ ስህተት ውስጥ ወድቀዋል። መሪዎች ሲሳሳቱ ሌሎችን ወደ ስህተት ይዘው ይገባሉ። መሪዎች በተለይም ለአዳዲስ ክርስቲያኖች መልካም ምሳሌዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል (ማር. 9፥42)።

14 በሐዋርያት *ሥራ* 15፥13–14፥19 እንደተገለጸው በኢየሩሳሌም የነበሩት መሪዎች ወደ ክርስትና የገቡ አረማውያን የአይሁድን ሕግ የግድ መከተል እንደሌለባቸው ተስማምተዋል። አይሁድና አሕዛብ በክርስቶስ በማመን በጸጋ እንደሚድኑ ይህ የወንጌል እውነት ነው። ጴጥሮስም ከእውነት ጋር ተስማምቷል (የሐዋ. 15፥7–11)። በተጨማሪም እንደ አረማዊ ኖሯል። አሁን ግን ከአረማዊ ወገን ከመጡ ክርስቲያኖች ጋር ለመብላት አልፈቀደም፤ ምክንያቱም አረማውያን «ያልነጹ/ርኩስ» ስለሚባሉ ነው። ከጴጥሮስ ባሕርይ እንደሚታየው «የአይሁድን ሕግ ካልተከተላችሁ ከእናንተ ጋር አልበላም» ብሎ ለአረማውያን በድርጊቱ መናገሩ ነው። በዚህ መንገድ ወደ ክርስትና የገቡ አረማውያን የአይሁድን ወግ እንዲከተሉ ማስገደዱ ነበር።

የአይሁድ ሕግ ብቁ አለመሆን (2፥15–21)

15–16 ጳውሎስ ንግግሩን በመቀጠል ለጴጥሮስና በገላትያ ለነበሩት አይሁድ ክርስቲያኖች «እኛ አይሁድ ነን፤ ኃጢአተኞች የሆኑ አረማውያን አይደለንም» ይላል። በአይሁድ አመለካከት አሕዛብ ሁሉ የአይሁድን ሕግ ስለማይከተሉ ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ ይቆጠራሉ። ጳውሎስም የሚናገረው በአይሁድ አመለካከት ነው። «ነገር ግን እኛ ክርስቲያኖች የሆንን አይሁድ እንኳ፤ ሰው ሕግን በመጠበቅ እንደ ማይድን እናውቃለን» ይላል። አይሁድና አሕዛብ ጻድቅ ተብለው ሊጠሩ የሚችሉት በኢየሱስ ክርስቶስ ካመኑ ብቻ ነው (የሐዋ. ⁄ 15፥11)። ጳውሎስ ከመጀመሪያውኑ ለገላትያ ሰዎች ያስተማረው እውነተኛው ወንጌል ይህ ነው። *ታዲያ* የገላትያ ክርስቲያኖች በኢየሱስ በማመን ብቻ ከጸደቁ በኋላ አሁንም ለመጽደቅ የአይሁድ ሕግን መፈጸም ያስፈልጋል ወደሚለው ትምህርት እንዴት ዘወር አሉ? ይህ ሊሆን አይገባም!

አንድ ሰው ለደኅንነት የሚያስፈልገው ምን እንደ ሆነ ሁላችን ⁝ጠንቅቀን ልናውቅ ይገባናል። በመጀመሪያ መልካም የሆነ ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር ጸጋ የሚመጣ እንደ ሆነ ማወቅ። ከእግዚአብሔር ጸጋ ማለትም ከፍቅሩ የተነሣ ክርስቶስ ሰዎችን ለማዳን ወደ ምድር መጣ (ዮሐ. 3፥16)። አይሁድ ይሁን አረማዊ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ነው (ሮሜ 3፥9–10)፤ ስለዚህ ሁሉም ሰው የኃጢአት ቅጣት ከሆነው ከዘላለም ሞት የሚያድነው አዳኝ ያስፈልገዋል (ሮሜ 6፥23)፤ ምሕረት የማይገባን ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ (ሮሜ 5፥618)። ክርስቶስ የኃጢአታችንን ቅጣት ስለተቀበለልን በእርሱ *ያመንን* እኛ በእግዚአብሔር ዓይን ጻድቃን ሆነን እንጂ እንደ ተፈረደበት ሰው አንቆምም (ሮሜ 3፥23–24)። ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ ውጤት ነው።

ታዲያ ሰው ለመዳን ምን ማድረግ አለበት? በክርስቶስ ማመን አለበት። የእግዚአ ብሔርን ጸጋ መቀበል ይኖርበታል። እግዚአብሔር ይህን ስጦታ ለመስጠት እጁን ዘርግቷል፤ እኛም ስጦታውን መቀበል ይኖርብናል። እምነት እጅን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ የመቀበል ሁኔታ ነው። ለዚህም ነው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ሲጽፍ *«ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም»* ያለው (ኤፌ. 2፥8)። የእኛ እምነትና የእግዚአብሔር ጸጋ ለደኅንነታችን አስፈላጊ ናቸው።

በክርስቶስ ስናምን የእርሱን ጽድቅ እንቀበላለን። ምንም ጥፋት እንደሌለብን ጻድቅ ተብለን እንጠራለን (ሮሜ 5፥1–2)። ስለዚህ በኃጢአታችን እግዚአብሔር አይቆጣንም። ይልቁኑ ይቅርታ ሰጥቶን ልጆቹ ያደርገናል። በክርስቶስ ባመንን ጊዜ ጻድቃን ሆነን ደኅንነታችንን እናገኛለን (ሮሜ 5፥9–10)። ደኅንነትን በማግኘታችንም የዘላለም ሕይወትን እንቀበላለን።

ስለዚህ ለመዳን በመጀመሪያ ጻድቃን መባል አለብን። ለመጽደቅ በክርስቶስ ማመን ይኖርብናል። በክርስቶስ ለማመን ደግሞ በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ጸጋ መቀበል አለብን። እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ጠርቶናል (ኤፌ. 1፥4)። ደኅንነታችን፥ ጽድቃችን፥ እምነታችንና መጠራታችን ሁሉ እጅግ ጥልቅ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጸጋ የሚመነጩ ናቸው። (ከአስተምህሮ ዳሰሳው የደኅንነት መንገድ የሚለውን ይመለከቷል)። ሕግጋትን ወይም ሰው ሠራሽ ወጎችን በመፈጸም ደኅንነትን ለማግኘት እንሞክር። በሠራነው *ሥራ* ጽድቅን መቀበል አንችልም። እንዲያውም በሥራችን ጽድቅን ለማግኘት መጣር የክርስቶስን ጸጋ መቃወም ነው (ሮሜ 3፥20–28)።

በቁ. 16 መጨረሻ ላይ ጳውሎስ ሕግን በመጠበቅ ማንም አይጸድቅም ሲል ተናግሯል። ይህ ለምን ሆነ? ምክንያቱም ማንም ሕግን እፈጽማለሁ የሚል አንዲቷን ግን ባይጠብቅ ሁሉን እንደ ተላለፈ ይቆጠራል (ያዕ. 2፥10)። ከትእዛዛት ሁሉ ልንጠብቀው የማንችለው አትመኝ የሚለውን ነው (ዘጸ. 20፥17)። ከዐሥርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያዎቹን ዘጠኙን መጠበቅ እንችል ይሆናል፤ ዐሥረኛውን ግን ሁልጊዜ መጠበቅ አይቻለንም፤ አትመኝ ማለት ክፉ ምኞት አይኑርህ ማለት ነው። ይህን ትእዛዝ በፍጹምነት የጠበቀ ማንም አይኖርም። ስለዚህ የአይሁድን ሕግ ወይም ሌሎች ሕግጋትንም በመጠበቅ ማንም አይጸድቅም (ሮሜ 7፥6–11)።

17 በዚህም ስፍራ ጳውሎስ ለአይሁድ አማኞች ይናገራል። የአይሁድ ክርስቲያኖችን ሥጋት ውስጥ የከተታቸው የአይሁድ ሃይማኖትን ወግ ባይከተሉ ኃጢአታቸው የከፋ እንደሚሆን በማሰባቸው ነው። ይህ እውነት ከሆነ፥ በክርስቶስ ማመን ወደ ባሰ ኃጢአተኛነት ይመራል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ክርስቶስ ኃጢአትን ይጨምራል ማለት ነው። በጳውሎስ አባባል ግን ተቃራኒው እውነት ነው። በክርስቶስ በማመን ብቻ መጽደቅ አለመፈለጋቸው በእግዚአብሔር ፊት ይልቁን ኃጢአተኞች ያደርጋቸዋል። ቅዱስና ንጹሕ የመሆኛው ብቸኛ መንገድ እምነትን በክርስቶስ ማድረግና የእርሱን ጽድቅ መቀበል ነው።

18 በሕግ መመካት እጅግ ኃጢአተኛ ያደርጋል። ጳውሎስ የፈረሰውን መልሶ የመገንባት ሐሳብ የለውም። «አያስፈልግም» ብሎ የተወውን ሕግና ወግ እንደ ገና አያነሣም። እንዲህ ካደረገ ግን «የጸጋ ሕግን» ዋጋ ማሳጣቱ ነው። ይህም ሰዎች ሁሉ የሚጸድቁበትን የክርስቶስን ሥራና መሥዋዕትነት መቃወም ነው። የክርስቶስን ጽድቅ ትቶ ብቃት በሌለው ሕግ ለመጽደቅ መጣር በእግዚአብሔር ፊት እንደ ሕግ ተላላፊ ያስቆጥራል፤ ምክንያቱም ሕግን በመጠበቅ ማንም ሊጸድቅ ስለማይችል (ቁ. 16)።

19 ሕጉ በሰው ላይ ከመፍረድ በስተቀር ለኃጢአተኛ አዲስ ሕይወትን መስጠት አይችልም። ሕጉ በጳውሎስ ላይ የሞት ፍርድ ፈርዶበት ነበር። ጳውሎስ «በሕግ በኩል ለሕግ ሞቼ ነበር» ይላል። ነገር ግን ሲሞት ነፃ ይወጣል። ዳኛ ፍርድ ከሰጠ በኋላ በጉዳዩ ላይ *ሥራ* አይኖረውም። በወንጀለኛው ላይ ያለው ሥልጣኑ ያከትማል፤ ወንጀለኛው ቅጣቱን

በመፈጸም ከዳኛው «ነፃ» ይሆናል፤ በተመሳሳይ መንገድ ጳውሎስ ለሕግ ስለ ሞተ ከሕግ ነፃ ሆኗል። ሕጉ በጳውሎስ ላይ የሞት ፍርድ ከፈረደበት በኋላ ምንም ሊያደርገው አይችልም፤ ጳውሎስ በሞቱ ከጌታው ነፃ እንደ ወጣ አንድ ባሪያ ነው። ስለዚህ አሁን ከቀድሞ ጌታው ከሕግ ነፃ በመሆኑ ክርስቶስን ለማገልገል፥ ለእግዚአብሔርም ለመኖር ነፃነት አለው (ሮሜ 7፥4፤ 6–7፤ 8፥1–2 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ክርስቶስ በውስጡ ስለሚኖር ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ለመኖር ነፃ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ለመኖር ኃይልም አለው (ቁ. 20)።

20 *ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ።* እዚህ ስፍራ ጳውሎስ የሚሰጠው ምስክርነት ምንኛ ጥልቅና አስደናቂ ነው! አንድ ሰው አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ከመቀበሉ በፊት መሞት ይገባዋል፤ ይህም አሮጌው ማንነቱ በመስቀል ላይ መሞት አለበት (ሮሜ 6፥6)። ከክርስቶስ ጋር መሰቀል የኃጢአተኛው ማንነታችን መሞት ማለት ነው። የዚያን ጊዜ የክርስቶስ ሕይወትና ባሕርይ በውስጣችን ይሞላል። የእርሱ መንፈስ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ውስጣችን ይገባል፤ በመንፈስ ቅዱስም የቅድስናና የጽድቅ ሕይወት ለመኖር ኃይልን እናገኛለን። በሕይወት የሚኖረው የቀድሞው እኛነታችን ሳይሆን፥ ክርስቶስ ነው፤ የቀድሞው ኃጢአተኛ ማንነታችን ሞቷል። ከኃጢአተኛ ተፈጥሮ ነፃ ወጥተናል (ሮሜ 6፥3–8 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

ጳውሎስ *«እኔ አልኖርም ነገር ግን ክርስቶስ በእኔ ይኖራል»* ይላል። ስለ ራሳችን እንደዚህ መናገር እንችላለን? እስቲ ሁላችን ራሳችንን እነዚህን ጥያቄዎች እንጠይቅ፤ በእኔ ውስጥ የሚኖረው ማነው? የድሮው ማንነቴ ወይስ ክርስቶስ? እንደ ጳውሎስ ክርስቶስ በእኔ ይኖራል ማለት እንችላለን?

የክርስቲያን ሕይወት እውነተኛ ትርጉም ክርስቶስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ መኖሩ ነው። በገዛ ፈቃዳችን ሕይወታችንን መኖር የለብንም። በእምነት ክርስቶስ በውስጣችን እንዲኖር እንፈቅዳለን፤ ኢየሱስ፥ *«በእኔ ኑሩ፤ እኔም በእናንተ እኖራለሁ»* ብሏል (ዮሐ. 15፥4–5)። ኢየሱስ በእኛ ውስጥ ስለሚኖር እንደ ኢየሱስ መኖር እንችላለን። የዚያን ጊዜ ሌሎች ሰዎች ክርስቶስን በእኛ ውስጥ አይተው እነርሱም ክርስቲያኖች ለመሆን ይፈልጋሉ። ጳውሎስ *«አሁን በሥጋ[15] የምኖርበት ኑሮ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው»* ይላል። የእግዚአብሔር ልጅ የተባለው ደኅንነትንና የዘላለም ሕይወትን እንድንቀበል ስለ ኃጢአታችን ለመሞት ወደ ምድር የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማር. 10፥45 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

21 ጳውሎስ *«የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም»* ይላል፤ ይህም ማለት እንደ ገና ደኅንነትን ሕግ በመፈጸም ለማግኘት አልሞክርም ማለት ነው። ሰው በክርስቶስ በማመን ሳይሆን ሕግን በመፈጸም የሚድን ከሆነ በእርግጥ ክርስቶስ የሞተው በከንቱ ነው!

ምዕራፍ 3

እምነት ወይስ ሕግን መጠበቅ (3፥1–14)

1 የማያስተውሉት የገላትያ ክርስቲያኖች አዚም ተደርጎባቸው ነበር። አስቀድሞ ጳውሎስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ እነርሱ መሞቱን በማመናቸው እንደ ዳኑ በግልጽ አስተምሯቸው ነበር። በዓይናቸውም ፊት *ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ በግልጽ ተሥሎ ነበር* (1ቆሮ. 1፥23፥24፤ 2፥2)። *ታዲያ* አሁን በገዛ ሥራቸው ላይ መደገፋቸው ለምንድን ነው?

2 ጳውሎስ የገላትያ ሰዎችን አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው። ይህም «መንፈስ ቅዱስን እንዴት ተቀበላችሁ?» ክርስቲያን የሆናችሁት እንዴት ነው? የሚል ነበር። የገላትያ ክርስቲያኖች በግልጽ እንደሚያውቁት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት ከጳውሎስ የሰሙትን የወንጌል መልእክት በማመናቸው ነበር። በመጀመሪያ እንሰማለን ከዚያም እናምናለን፤ ቀጥሎም መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን (የሐዋ. 2፥38፤ ሮሜ 10፥14፤ ኤፌ. 1፥13)።

3 በመጀመሪያ የገላትያ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን በእምነት ተቀበሉ። በክርስቶስም አዲስ ህይወት አገኙ። ስለዚህ ጳውሎስ «ታዲያ አሁን በሰው ጥረት ግባችሁን ለመምታት ለምን ትሞክራላችሁ?»[16] ሲል ይጠይቃቸዋል። ይህም የገላትያ ክርስቲያኖች በራሳቸው ጥረት፥ በራሳቸው ሥራ ለምን ቅዱሳን ለመሆን ይሞክራሉ? ማለት ነው። ሰው ሊቀደስ (ሊጸድቅ) የሚችለው በእምነት ብቻ እንደ ሆነ ተምረዋል። አሁን እነዚህ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ትተው በሰው ድካም ላይ መደገፍ እየጀመሩ ነው። ለእግዚአብሔርም በሥራቸው ምን ያህል ጻድቃን እንደ ሆኑ ለማሳየት እየሞከሩ ነው። ሆኖም በእግዚአብሔር ፊት ማንም በሥራው ጻድቅ ሊሆን አይችልም (ገላ. 2፥16)።

4 የገላትያ ክርስቲያኖች በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት መከራ ተቀብለዋል፤ አሁን ይህን እምነት ከተው መከራ መቀበላቸው ከንቱ ሆነ ማለት ነው። ስለዚህ ነው ጳውሎስ *እንደዚህ ያለ መከራ በከንቱ ተቀበላችሁን?* ያለው፤ ጳውሎስ ይህን መናገሩ በእርግጥ መከራ መቀበላቸው በከንቱ እንዳልነበረ ለመግለጽ ነው።

5 እዚህ ስፍራም ጳውሎስ በቁ. 2 ላይ የጠየቀውን ጥያቄ ይደግማል። የገላትያ ሰዎች እግዚአብሔር መንፈሱን የሰጣቸውና በመካከ ላቸው ተአምራትን ያደረገው የሕግን ሥራ በመፈጸማቸው ሳይሆን በእምነታቸው ምክንያት እንደ ሆነ ያውቃሉ። ቀድሞውኑ የሚያውቁትን ጳውሎስ ያስታውሳቸዋል። ከእግዚአብሔር በረከትን ከተቀበሉና በመካከላቸው የእርሱን የጸጋውን ብርቱ ሥራዎች ከተመለከቱ በኋላ የገላትያ ክርስቲያኖች አሁን እንዴት የእግዚአብሔርን ጸጋ ትተው በሕግ ላይ እምነታቸውን ጣሉ?

6 የአይሁዳውያን አባት የሆነው አብርሃም ለሰው ሁሉ የሚሆን ምሳሌ ነው። እርሱ ጻድቅ የተባለው በሥራ ሳይሆን በእምነት ነው። ጳውሎስ ይህን የጠቀሰው ከዘፍ. 15፥6 ላይ ነው። የአብርሃም እምነት *ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት* (ሮሜ 4፥1–3 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

በገላትያ የነበሩ አይሁድ አስተማሪዎች ጻድቅ ተብሎ ለመጠራት መገረዝና የአይሁድን ሕግ መፈጸም ይገባል ብለው ያስተምሩ ነበር። ደግሞም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ለመባል በሥጋ የአብርሃም ልጅ መሆን ያስፈልጋል ብለው ያምኑ ነበር። ይህም ለመጽደቅ አይሁድ መሆን ያስፈልጋል ማለታቸው ነው። ጳውሎስ ከአይሁዳውያን ቅዱሳት መጻሕፍት (ብሉይ ኪዳን) በመጥቀስ አንድ ሰው በእምነት ብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ ጻድቅ ሊባል እንደሚችል ያሳያል።

7 እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ ያደረጉ ሁሉ የአብርሃም መንፈሳዊ ልጆች ናቸው። ከአረማውያን ወገን የሆኑ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለልጆቹ ቃል የገባውን በረከት በእምነት ይወርሳሉ። ስለዚህ እውነተኛ የአብርሃም ልጆች በሥጋ ከእርሱ የተወለዱ (አይሁዳውያን) ሳይሆኑ፥ በክርስቶስ ያመኑት ናቸው (ሮሜ 4፥11፡13፡16 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

8 ጳውሎስ ከዘፍጥረት መጽሐፍ በመጥቀስ እግዚአብሔር ለአብርሃም በእርሱ በኩል ሕዝቦች ሁሉ እንደሚባረኩ ቃል እንደ ገባለት ያሳያል (ዘፍ. 12፥3፤ 18፥18፤ 22፥17–18)። ሕዝቦች ሁሉ ሲል አይሁድ ብቻ ሳይሆኑ አሕዛብንም ያጠቃልላል። አይሁዳውያን ለአብርሃም የተገባውን የበረከት ተስፋን እነርሱ ብቻ እንደሚወርሱ ያምናሉ ምክንያቱም በሥጋ የአብርሃም ልጆች ስለሆኑ። ነገር ግን ማንም ቃል ከተገባለት በሥጋ በመወለዱ መንፈሳዊ በረከትን

---

15 እዚህ ስፍራ «ሥጋ» የሚለው ቃል ቁሳዊ አካልን ያመለክታል። በአዲስ ኪዳን በሌላ ክፍል «ሥጋ» የሚለው ቃል የሰውን ኃጢአት ተፈጥሮ የሚያመለክት ነው (ሮሜ 8፥3–13፤ ገላ. 5፥16–19፤ ለተጨማሪ ማብራሪያ ከቃላት መፍቻው ሥጋ የሚለውን ይመለከቷል)።

16 በሰው ጥረት ግባችሁን ለመምታት ትሞክራላችሁ የሚለው ዐረፍተ ነገር በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች «በሥጋ ትፈጽማላችሁ» ይላል፤ ይህ ከግሪኩ በቀጥታ ቃል በቃል የተተረጎመ ነው። ትርጉማቸው ግን አንድ ነው። በዚህ ቁጥር «ሥጋ» የሚለው ቃል ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችንን ያመለክታል። ለተጨማሪ ማብራሪያ የገላትያ 2፥20 የግርጌ ማስታወሻ፥ በቃላት መፍቻው ሥጋ የሚለውን ይመለከቷል።

ሊወርስ አይችልም። ስለዚህ በክርስቶስ *ያመኑ* በእምነት እነዚህን በረከቶች ሁሉ ይወርሳሉ።

9 በዚህ ቦታ ጳውሎስ የቁ. 7 ሐሳብን በድጋሚ ያቀርባል። አብርሃም ጻድቅ የተባለው ሳይገረዝ ነው። አብርሃም *በመጀመሪያ* በእግዚአብሔር ሲያምን ገና አልተገረዘም ነበር (ሮሜ 49፥11)። ደግሞም አብርሃም ሕግን በመፈጸም አልጸደቀም። ምክንያቱም በሕይወት በነበረበት ጊዜ ገና ሕግ አልተሰጠም ነበር (ሮሜ 4፥13)። ሕጉ የመጣው በሙሴ ዘመን ከ430 ዓመታት በኋላ ነበር (ቁ. 17)። ስለዚህ አብርሃም ጻድቅ የተባለው በእምነት ብቻ ነው። እኛም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ተብለን የምንጠራው በክርስቶስ በማመን ነው (የሐዋ. 13፥38–39፤ ሮሜ 5፥1)።

10 በሕጉ ያሉትን ትእዛዛት በሙሉ ካልታዘዝን ሕጉ ይፈርድብናል (ያዕ. 2፥10)። ስለዚህ በሕጉ ላይ ከተደገፍን *ከእርግማን በታች* እንሆናለን፤ ይህም ከሞት ፍርድ በታች መሆን ማለት ነው። የሞት ፍርድን እንቀበላለን። ለምን? ምክንያቱም ማንም ትእዛዛትን በሙሉ አንዱንም ሳይጥስ የሚፈጽም የለም። በዚህ ቦታ ጳውሎስ ከዘዳ. 27፥26 ይጠቅሳል።

11 *ማንም* ሕግን በመፈጸም አይጸደቅም፤ ምክንያቱም ማንም ሁሉንም መጠበቅ ስለማይችል። ጳውሎስ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ከዕንባቆም መጽሐፍ በመጥቀስ *ጻድቅ ሰው ግን በእምነት ሕይወትን ያገኛል* እንጂ በሕግ አይደለም ይላል (ዕን. 2፥4፤ ሮሜ 1፥17)።

12 ጳውሎስ ከዘሌ. 18፥5 ይጠቅሳል። *ሕግን የሚፈጽም ሁሉ (በሕግ) በሕይወት ይኖራል* (ሮሜ 10፥5)። ሰው ሕግን በፍፁምነት ቢታዘዝ በሕይወት ይኖራል ይህ ግን የማይቻል ነው። ካልታዘዘ ግን ከፍርድ በታች ይሆናል፤ ስለዚህ ሕግ የተመሠረተው በእምነት ላይ ሳይሆን በሰው *ሥራ* ላይ ነው።

13 እዚህ ስፍራ የተጠቀሰው *የሕግ እርግማን* የሞት ፍርድ ነው። ክርስቶስ የእኛን የሞት ፍርድ በራሱ ላይ በማድረግ *እኛን ዋጀን*። ይህ ፍርድ ከእኛ ስለ ተወሰደ በእግዚአብሔር ዓይን በደል የሌለብንና ጻድቃን ሆነናል። እግዚአብሔር፥ «ሰው ስለ ኃጢአቱ መቀጣት ይገባዋል። ማንን ልቅጣ?» ሲል ኢየሱስ በእኛ ቦታ ቆሞ «በእነርሱ ፈንታ እኔን ቅጣኝ፤ እነርሱ በነፃ ይለቀቁ» አለ (ማር. 10፥45 ይመለከቷል)።

ክርስቶስ ከሕግ እርግማን ዋጀን። ይህን ሌላ አገላለጽ በመጠቀም በተሻለ ሁኔታ መረዳት እንችላለን። ቀድሞ እንደ ባሪያዎች በእስራት ነበርን። ጌታችንም የአይሁድ ሕግ ነበር። ነፃነትን ለማግኘት ለጌታችን ዋጋ በመክፈል ነፃ የሚያወጣን ያስፈልግ ነበር። ኢየሱስ ይህን ዋጋ ከፈለልን። የከፈለው ዋጋ ደግሞ ደሙ ነው፥ የገዛ ሕይወቱን። ስለዚህ አሁን ከሕግ ሥልጣን በታች አይደለንም፤ እኛ የክርስቶስ ነን። እርሱ ዋጋ ከፍሎ የራሱ አድርጎናል (1ቆሮ. 6፥19–20፤ 7፥23፤ 1ጴጥ. 1፥18–19)።

ጳውሎስ ከዘዳግም 21፥23 ይጠቅሳል። ይህ ክርስቶስ በመስቀል *(በእንጨት)* ላይ እንደሚሞት የተነገረ ትንቢት ነው። በሞቱ *ስለ እኛ የተረገመ* ሆነ። የዘዳግም መጽሐፍ በተፃፈበት ዘመን ሞት የተፈረደባቸው ወንጀለኞች መረገማቸውን ለማሳየት በእንጨት ላይ ይሰቀሉ ነበር። ክርስቶስ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ፤ ይህም ቀድሞ ከነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ጋር ተመሳሳይነት አለው።[17]

14 ከሕግ እርግማን የተነሣ (ቁ. 13)፤ በዘፍ. 12፥3 ለአብርሃም የተሰጠው የበረከት ተስፋ በብሉይ ኪዳን ዘመን አልተፈጸመም፤ ነገር ግን ክርስቶስ መጥቶ እርግማንን አስወገደ። ስለዚህ አሁን የክርስቶስ አካል በመስቀል ላይ መሥዋዕት ስለሆነ በእርሱ በማመን ለአብርሃም የተገባለትን የበረከት ተስፋ መቀበል እንችላለን። በክርስቶስ በማመን የአብርሃም ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች ሆነናል (ሮሜ 8፥16)። ይህም ብቻ ሳይሆን በሰማይ ለእኛ ከተቀመጠልን የበረከት ውርስ ለቅምሻ የተላከውን የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ተቀበልን (2ቆሮ. 1፥21–22፤ 5፥5፤ ኤፌ. 1፥13–14)። ከዚህ ቁጥር እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለልጅ ልጆቹ የሰጠውን ተስፋ ማየት እንችላለን። ይህም ተስፋ ደኅንነት ነው። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በክርስቶስ የሚገኝ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት፤ በክርስቶስ እንዳመንን የሚጀምርና የማያልቅ አዲስ ሕይወት ነው።

ሕጉና ተስፋ (3፥15–20)

15 እግዚአብሔር ለአብርሃም የተሰጠውን ተስፋ ለማብራራት ጳውሎስ የእለት ከእለት ያለውን ኑሮ እንደ ምሳሌ ይጠቀማል። ሰዎች የተለያዩ ዓይነት *ቃል ኪዳኖች* እርስ በርሳቸው ይገባባሉ። *ቃል ኪዳን* አንዴ ከተገባቡ *የጸና* ይሆናል። ስለዚህም በቀላሉ የሚለወጥ አይሆንም።

16 በተመሳሳይ መልኩ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር *ቃል ኪዳን* አደረገ። እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ እርግጠኛ የሆነ *ቃል* ገባለት። ተስፋውም የአብርሃም ልጆች ደኅንነትንና መንፈስ ቅዱስን እንደሚቀበሉ ነው። ስለዚህ ዘሩ የተባለው ክርስቶስና እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ ያደረጉትን ሁሉ ያጠቃልላል። ክርስቶስ በኩር ነው፤ የአዲሱ መንፈሳዊ ቤተሰብ ወይም ሕዝብ የመጀመሪያ ፍሬ ነው (ሮሜ 8፥29፤ 1ቆሮ. 15፥20)። የተስፋ *ቃል* የተሰጠው አብርሃም *ዘሮች* ማለትም ለአብርሃም የሥጋ ልጆች አይደለም፤ ነገር ግን ለክርስቶስ ብቻ እና በክርስቶስ ላመኑት ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን «. . . *የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ*» አለው (ዘፍ. 22፥18)። ስለዚህ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ በክርስቶስ ተፈጽሟል።

17 በዚህ ቦታ ላይ ጳውሎስ ለማስተላለፍ የፈለገውን ፍሬ ሐሳብ ይሰጣል። እግዚአብሔር ለአብርሃም የደኅንነትን ተስፋ ገና ሕጉ ሳይታወቅ ከ430 ዓመታት በፊት ሰጠው (ዘጸ. 12፥40)። *ታዲያ* በገላትያ ያሉ እነዚህ አይሁድ አስተማሪዎች እንዴት ደኅንነትን ለማግኘት ሕግን መፈጸም አስፈላጊ ነው ይላሉ? የደኅንነት ተስፋ በምንም ዓይነት መንገድ በሕግ ላይ የተደገፈ አይደለም። እንዲሁም የሕጉ መምጣት በተሰጠው ተስፋ ላይ ምንም ተጽእኖ ሊያሳድር አይችልም።

18 *ውርሱን* (ደኅንነትን) ለማግኘት ሕጉ የሚያስፈልግ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ከንቱ ይሆን ነበር። ሕጉ ለደኅንነት አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው *ቃል ኪዳን* ይለወጥ ነበር፤ እንዲያውም ይሻር ነበር። ይህ ሊሆን ግን አይችልም (ቁ. 15)። የእግዚአብሔር ተስፋ ሊሻር አይችልም። ጳውሎስ የሚያስ ተላልፈው መልእክት፤ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለመንፈሳዊ ልጆቹ የሰጠው ውርስ (ደኅንነት) በኋላ በሚመጣው ሕግ በኩል ሳይሆን፤ ከእግዚአብሔር ጸጋ መንጭቶ በእምነት በምንቀበለው *ተስፋ* በኩል ነው (ሮሜ 4፥14፥16 ይመለከቷል)። ደኅንነት ለሰው የተሰጠው በጸጋ ብቻ ነው። የአይሁድን ሕግ ወይም ሌላ ሕግን በመፈጸም በሥራችን ደኅንነትን ልናገኝ አንችልም።

19 ስለዚህ የሕግ ዓላማ ምኑ ላይ ነበር? የሚለው ጥያቄ መነሣቱ የማይቀር ነው። ሕጉ የመጣው በመተላለፍ ምክንያት ነው። ሕጉ በእግዚአብሔር የተሰጠው፤ ኃጢአትን ለመግለጥና፥ ኃጢአትን ወደ ብርሃን ለማውጣት ነው (ሮሜ 5፥20 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ሕጉ ከመሰጠቱ አስቀድሞ ሰዎች ያላስተዋሉት እንደ ምኞት ያሉ ኃጢአቶች ነበር። እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ የገዛ ኃጢአታቸውን እንዲያዩና ኃጢአተኞች መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ሕግን ሰጠ (ሮሜ 3፥20፤ 7፥7 ይመለከቷል)።

ሕጉ በግልጽ የሚያሳየው ሰው ራሱን እንደማያድን ወይም ጻድቅ ማድረግ እንደማይችል ነው። ሕጉ የሚያሳየው ሁሉም ሰው አዳኙ ክርስቶስ እንደሚያስፈልገው ነው። በሌላ አገላለጽ፥ ሕጉ ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል፤ ደግሞም እንደሚመጣ ተስፋ የተገባለት *ዘሩ (ክርስቶስ) እስኪመጣ ድረስ* በሥራ ላይ እንደሚቆይ ያመለክታል። ክርስቶስ ከመጣ በኋላ ግን ሕጉ ምንም አስፈላጊነት የለውም። ይህም ቢሆን በሌላ በኩል ሕጉ አስፈላጊ ሆኖ ማገልገሉን ይቀጥላል፤ ኃጢአት ምን እንደ ሆነ ያሳየናል። ኢየሱስ ራሱ አብዛኛውን

---

[17] በሮማውያን ግዛት ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን ወንጀለኞች የሚቀጡት በመስቀል ላይ በማንጠልጠል (በመስቀል) ነበር።

ትምህርቱን ከአይሁድ ሕግ በመነሣት አስተምሯል (ማቴ. 5፥21-22፥ 27-28፥ 38-39፥ 43-44 ይመለከቷል)።

ሕጉ ከተስፋው ያነሰ ነው። ሕጉ ጊዜያዊ ነበር፤ ያገለገለውም ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ብቻ ነበር። አሁን ክርስቶስ ከሕግ *እርግማን* አድኖናል።

ሕጉ እንደ ተስፋው ከእግዚአብሔር በቀጥታ ወደ ሰው አልመጣም። ሕግ መካከለኛ በነበረው በሙሴ[18] በኩል *በመላእክት* አገዛ መጣ (ዘጸ. 31፥18፤ የሐዋ. 7፥53)። ስለዚህ በሙሴና በመላእክት አማካይነት እንደ መጣው ሕግ ሳይሆን ተስፋው በቀጥታ ስለመጣ ከሕጉ የላቀ ነው።

20 *መካከለኛ* አንደኛውን ወገን ብቻ ሳይሆን ሁለቱንም የሚወክል ነው። ሁለቱንም ቡድኖች በመወገን በመካከላቸው መስማማት እንዲገኝ ይጥራል። በሙሴ አማካይነት ለአይሁድ የተሰጠው ሕግ በሁለት ወገኖች እንደ ተደረገ ስምምነት ዓይነት ነው። እግዚአብሔር ሕጉን ሰጠ፤ ሰው ደግሞ የመጠበቅ ግዴታ ነበረበት። እግዚአብሔር አንድ ነገር አደረገ፤ ሰው ደግሞ በምላሹ ማድረግ ያለበት ነገር አለ። *ቃል ኪዳን* ለመመሥረት ሁለቱም ወገኖች የሚኖራቸው ድርሻ አለ። ስለዚህም የቀድሞው ኪዳን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሊቆም አንድ *መካከለኛ* (ሙሴ) አስፈልጎ ነበር።

ተስፋ ግን ከኪዳን ወይም ከውል የተለየ ነው። ተስፋ ለመስጠት አንድ ወገን ብቻ ያስፈልጋል፤ ይህም እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ተስፋን ሲሰጥ የሚፈጽመው እርሱ ብቻውን ነው። ተስፋው በነጻ ተሰጥቷል። ሰዎች ማድረግ የሚገባቸው ተስፋውን መቀበል ብቻ ነው። የሰው ወይም የመላእክት መካከለኛነት[19] ሳያስፈልግ እግዚአብሔር ወደ እኛ መጥቶ የደኅንነት ተስፋና መንፈስ ቅዱስን ሰጠን። በመንፈስ ቅዱስ ማለትም ክርስቶስ በእኛ ውስጥ በመኖሩ ሕግን መፈጸም የሚያስችል ኃይል ተቀበልን። ከተስፋው ቃል ጋር ኃይል ይመጣል።

የሕግ ዓላማ (3፥21-29)

21 ሕጉ ተስፋውን አይቃወምም። በሕጉና በተስፋው መካከል ያለው ልዩነት ሕጉ ኃይል የሌለው፥ ተስፋው ደግሞ ኃይል ያለው መሆኑ ነው። ሕጉ *ሕይወት አይሰጥም*፤ ተስፋው ግን ይሰጣል። *ሕይወት መስጠት* ማለት ሕያው ማድረግ፥ መንፈስን ንቁ ማድረግ፥ መንፈሳዊ ኃይልን ማግኘት ነው። ሕጉ መንፈሳዊ ሕይወትንና ኃይልን የሚሰጠን ከሆነ ሕጉን በመጠበቅ ጻድቃን እንሆናለን። ሕጉ ግን ይህን ሊያደርግ አይችልም (ሮሜ 8፥3)። ስለዚህ ሕጉ ሕይወትና ኃይል መስጠት ስለማይችል ማንም ሰው ሕጉን በመጠበቅ ሊጸድቅ አይችልም። በክርስቶስ በማመን በጸጋው ብቻ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆንና ደኅንነትንም ማግኘት ይቻላል (ኤፌ. 2፥8)።

22 *መጽሐፍ ቅዱስ (እግዚአብሔር)፥ ዓለም በሙሉ (የሰው ዘር ሁሉ) ለኃጢአት በመገዛት የኃጢአት እስረኛ እንደ ሆነ ይናገራል*። በሌላ አገላለጽ፥ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ስላመፀ እግዚአብሔር ሰውን የኃጢአት እስረኛ እንዲሆን አደረገ (ሮሜ 3፥9-10፤ 11፥32)። ሰው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ስለ ሠራ የተረገመ ሆነ። አሁን ግን እግዚአብሔር ሰው የሚያመልጥበትን መንገድ አዘጋጅቷል፤ ይህም በክርስቶስ በማመን የምንቀበለው ተስፋ የደኅንነት ተስፋ ነው።

23 እዚህ በታም ጳውሎስ የቁ. 22 ሐሳብን ይደግማል። *ይህ እምነት* (የክርስቶስ ወንጌል) *ከመምጣቱ በፊት የሕግ እስረኞች ሆነን ተዘግተብን ነበር*። በቁ. 22 ላይ ጳውሎስ *የኃጢአት እስረኞች እንደ ነበርን ተናግሯል*። የሕግ እስረኞች መሆንና የኃጢአት እስረኞች መሆን ማለት ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው። ኃጢአትና ሕግ *ሥራቸው* መኮንን ነው። ኃጢአት ኃይሉን ያገኘው ከሕግ ነው (ሮሜ 7፥8-11፤ 1ቆሮ. 15፥56 ይመለከቷል)።

24 በኃጢአቱ ምክንያት ሰው በአንድ ኃይል ሥር መሆን ነበረበት። በጳውሎስ ዘመን ሀብት ያላቸው ሰዎች ሕፃናት ልጆቻቸውን የሚያስተምሩላቸው ልዩ የግል አስተማሪዎችን ወይም የሚጠብቁላቸውን ሞግዚቶች ይቀጥሩ ነበር። በተመሳሳይ መንገድ በሕጉ ሥር ነበርን፤ ሕጉ የእኛ «ሞግዚት» ነበር። ሞግዚት በኀላፊነት የተሰጠውን ልጅ እንደሚያሳድግ ሕጉም *ወደ ክርስቶስ የሚመራን* ሞግዚታችን ነበር።

25 አሁን ወንጌል ስለ መጣና እኛም በክርስቶስ ስላመንን *የሕግ ሞግዚትነት* አያስፈልገንም።

26 ጳውሎስ በሕይወት በነበረበት ዘመን አንድ ወንድ ልጅ የልጅነት መብትና ሥልጣን የሚኖረው ተገቢው የእድሜ ደረጃ ሲደርስ ነበር፤ ከዚያ በፊት ከሞግዚት ኀላፊነት ሥር ይቆያል (ገላ. 4፥1-2)። በክርስቶስ *ያመኑ* በእድሜአቸው እንደ ጎለመሱ ልጆች የሚታዩ ናቸው። ስለዚህም አሁን ሙሉ የልጅነት መብት አላቸው። የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ዮሐ. 1፥12-13፤ ገላ. 4፥7)። ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች አይሁድ ብትሆኑ ወይም ግሪክ፥ ባሪያ ወይም ጌታ፥ ወንድ ወይም ሴት ሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ይላቸዋል (ቁጥር 28 ይመለከቷል)።

27 እድሜአችን ሲደርስና ሙሉ የልጅነት መብት ሲኖረን የድሮውን የተማሪነት የደንብ ልብሳችንን አውልቀን አዲሱን እንለብሳለን። በተመሳሳይ መንገድ በክርስቶስ ስናምን የድሮውን ልብሳችንን አውልቀን ክርስቶስን ማለትም የእርሱን ጽድቅ እንለብሳለን። *በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ ስንሆን ክርስቶስን እንለብሳለን*። ይህ የጥምቀት ትክክለኛ ትርጉም ነው። በክርስቶስ ስም ስንጠመቅ ያረጀውን ኃጢአተኛውን ኑሮአችንን አውልቀን በክርስቶስ ያገኘነውን መንፈሳዊ ሕይወት አዲሱን ማንነታችንን እንለብሳለን (ሮሜ 6፥3-4፤6፤ 2ቆሮ. 5፥17፤ ኤፌ. 4፥22-24 እና ማብራሪያዎቻቸውን ይመለከቷል)።

28 ወደ ክርስቶስ በእምነት ሊመጣ የሚችል ማነው? ሁሉ ሊመጡ ይችላሉ። በመንፈሳዊ ዓይን በሰዎች መካከል ምንም መበላለጥ የለም። ሁሉም በእምነት የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን እኩል መብት አላቸው። በክርስቶስ ስም ስንጠመቅ፥ ክርስቶስን ስንለብስ አንድ ቤተሰብና አንድ አካል እንሆናለን (1ቆሮ. 12፥13 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። *ሁላችንም አይሁድና ግሪክ፥ ባሪያና ጌታ፥ ወንድና ሴት በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ እንሆናለን*።

በጳውሎስ ዘመን በአይሁድና በግሪክ፥ በባሪያና በጌታ እንዲሁም በወንድና በሴት መካከል የነበረውን ልዩነት አስብ። አይሁዳውያን ግሪኮችን ይጸየፉሉ፤ ባሪያዎች በጌቶቻቸው ይጨቆናሉ፤ ሴቶች ከወንዶች የበታች እንደ ሆኑ ይቆጠራሉ። በክርስቶስ ግን እንዲህ ያለው ልዩነት የለም። በክርስቶስ ሁሉም አንድ ሆነዋል (ቆላ. 3፥9-11)።

በክርስቲያኖች መካከልም በዘር፥ በሀብት፥ በዜግነት ምክንያት ልዩነት ሊኖር አይችልም። እያንዳንዳችን ያለንበትን ቤተክርስቲያን ስንመለከት እነዚህ ልዩነቶች ይገኙ ይሆን? በዘር፥ በሀብት፥ በጾታ ምክንያት ልዩነቶች አሉ? ቤተክርስቲያን የአንዱ ወገን ወይም የሌላው ሳትሆን የክርስቶስ ናት። ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት (1ቆሮ. 12፥27፤ ኤፌ. 1፥22-23)። በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ያለን ሁላችን በክርስቶስ አንድ ነን። የዜግነት ልዩነት የለም። ምድራዊ ያልሆነ ሰማያዊ ዜግነት አለን። በመንግሥተ ሰማይ የውጭ ዜጋ የሚባል የለም። እነዚህ ልዩነቶች በቤተክርስቲያኖቻችን እንዲኖሩ ከፈቀድን የክርስቶስን አካል በመከፋፈል እግዚአብሔርን እየበደልን ነው።

29 ክርስቶስ የአብርሃም እውነተኛ *ዘር* (ልጅ) ነው (ቁ. 16)። ስለዚህ እኛም በክርስቶስ ስናምን እውነተኛ የአብርሃም ልጆች እንሆናለን (ቁ. 7)። እኛ ከክርስቶስ ጋር የምንወርስ እንሆናለን (ሮሜ 8፥17)። ተስፋውን እንወርሳለን። ይህም

---

[18] ሙሴ አንዱ የአይሁድ ታላቅ መሪ ነበር። የተወለደው ከአብርሃም አራት መቶ ዓመት በኋላ ነበር። በሲና ተራራ ላይ የእግዚአብሔርን ሕግ ተቀብሎ ለአይሁድ ሕዝብ አስተላልፎአል። አይሁድ ሕግን የተቀበሉት በሙሴ አማካይነት ነበር። ሙሴ መካከለኛ የተባለው በዚሁ ምክንያት ነው።

[19] በ1ጢሞ. 2፥5 ላይ ጳውሎስ፥ «በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አንድ መካከለኛ አለ እርሱም ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ሲል ጽፎአል። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰው ብቻ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር (አምላክ) ነው። ስለዚህ ለሰዎች በተሰጠው የደኅንነት ተስፋ «መካከለኛ» የሆነው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ሌላ መካከለኛም አያስፈልገም።

ተስፋ የዘላለም ሕይወትን የሚያስገኘው የደኀንነት ተስፋ ነው።

ምዕራፍ 4

በእምነት ወራሾች መሆን (4፥1–7)

1–2 ጳውሎስ በነበረበት ዘመን፥ እድሜው ያልደረሰ ወራሽ ልጅ፤ የቤት ውልድ ከሆነ ባሪያ የበለጠ ሥልጣን አልነበረውም። *በሞግዚትና በታመኑ ሰዎች አስተዳደር ሥር* ሙሉ በሙሉ ይቆይ ነበር።

3 ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት *ለዚህ ዓለም ሥርዓት ተገዢዎች ሆነን ባሪያዎች ነበርን*። ይህም ለዓለማዊ እምነቶችና ልማዶች ባሪያዎች፥ የሰይጣንና የርኩሳን መናፍስቱ ባሪያዎች ነበርን (ገላ. 3፥23፤ ቆላ. 2፥20)። እኛም ውርስ መቀበል እንደማንችል ሕጻናት ነበርን። ከሞግዚታችን ከሕግ በታች ነበርን። በተጨማሪም *በዚህ ዓለም ሥርዓት ሥር* ባሪያዎች ነበርን። ጳውሎስ በዚህ ቦታ የገለጸው የዓለም *ሥርዓት* የሰውን ወግ፥ ልማድና ባሕል ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። ይህም የጣዖት አምልኮን፥ በሰው የተደነገጉ ሃይማኖታዊ ሕግጋትንና *ሥርዓቶችን* የሚያካትት ነው። የሰው *ሥራዎች*፥ ሰው በራሱ ጥረት ለመጽደቅ የሚያደርገውን ጥረት በርኩሳን መናፍስት *ሥር* ሰው ለእነዚህ የሚሰጠውን አገልግሎት ሁሉ ያጠቃልላል (ገላ. 4፥8–9፤ ኤፌ. 2፥1–2 ይመለከቷል)።

4 *ነገር ግን የተወሰነው ጊዜ ደርሶ* ወራሾች ለመሆን እድሜአችን በደረሰ ጊዜ *እግዚአብሔር ልጁን* ክርስቶስን ላከ (ሮሜ 5፥6)። እንደ እኛ እርሱም *ከሴት ተወለደ* (ማቴ. 1፥18፤ ፊል. 2፥6–8)። የሰውን ፈተናና ድካም ሁሉ ተካፈለ (ዕብ. 2፥15፥18፤ 4፥15)። የተወለደው *ከሕግ በታች* ነበር። ሕግ ሰጪው እግዚአብሔር ወደ ምድር መጥቶ እንደ ሰው ሆነ፤ ራሱ ለሰጠው ሕግም ታዛዥ ሆነ። ይህም የሆነው ሕግን ሙሉ ለሙሉ ለመፈጸም ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ሕጉ የፈረደብንን የኃጢአት *ዕዳ* ከፈለልን። የከፈለው *ዋጋም* የራሱን ሕይወት ነበር፤ ምክንያቱም *የኃጢአት ደመወዝ ሞት* ስለሆነ ነው (ሮሜ 6፥23)።

5 እግዚአብሔር ልጁን የላከው ለምን ነበር? *ከሕግ በታች፥ በዓለም ከሥርዓት በታች* የነበሩትን አይሁድንና ሌሎች ሕዝቦችን *ለመዋጀት* ነው። ቀድሞ እንደ ባሪያዎች ሰይጣን፥ *የዚህም ዓለም ሥርዓት* ጌታችን ነበር (ዮሐ. 12፥31)። ስለዚህ የሰይጣን «ንብረት» ስለ ነበርን እኛን ከሰይጣን *ለመዋጀት* ክርስቶስ ዋጋ መክፈል ነበረበት (ገላ. 3፥13)።

ነገር ግን ክርስቶስ እኛን «ሲገዛን» የቀድሞው ባሪያነታችን አከተመ። እኛም የክርስቶስ ወንድሞች እና እህቶች ሆንን። የእግዚአብሔር ልጆች ተደርገን ሙሉ የወራሽነት መብትን አገኘን (ኤፌ. 1፥5፤ 1ዮሐ. 3፥1)። የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ምን ማለት ነው? በደም ግንኙነት የሌለውን ሰው የወራሽነት መብት እንደ ሥጋ ልጅ ማግኘት ነው። የሌላ ሰው ልጅ ቢሆንም ይህ ልጅ የአዲሱ አባት ሙሉ ወራሽነት መብት አለው።

በተመሳሳይ መልኩ በመንፈሳዊ አገላለጽ በክርስቶስ የሚያምኑ የልጅነት መብትን ያገኙ ናቸው። በመጀመሪያ በሥጋ የጨለማው ልጆች፥ የሰይጣን ልጆች ነበርን (ኤፌ. 2፥3፤ 5፥8)። አሁን ግን በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ የእግዚአብሔር ልጆች ነን። *ሙሉ የልጅነት መብትን ተቀብለናል* (ዮሐ. 1፥12–13 ይመለከቷል)።

አንድ ነገር ልብ እንበል። የሰይጣን *መንግሥት* የሆነውን የዚህን *ዓለም ሥርዓት ለመተው ፈቃደኞች* ካልሆንን ክርስቶስ አይገዛንም። እርሱ የሚዋጀው በእምነት ወደ እርሱ የቀረቡትን ብቻ ነው፤ ሰዎች ያለ ፈቃዳቸው ወደ መንግሥቱ እንዲገቡ አያስገድዳቸውም።

6 የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን የምንወርሰው ምንድን ነው? ርስታችን በሰማይ የዘላለም ሕይወት ነው። በዚህ ሕይወትም የምናገኘው ውርስ አለን? አዎን፤ መንፈስ ቅዱስ የምንወርሰው መያዣ ሆኖ ተሰጥቶናል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ምልክት፥ (ማኅተም) አሁንና ወደፊት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን የሚያረጋግጥልን ነው (2ቆሮ. 1፥21–22፤ ኤፌ. 1፥13–14)።

ክርስቶስ እንደ ቃሉ ወዲያው እግዚአብሔር *የልጁን መንፈስ* መንፈስ ቅዱስን *ወደ ልባችን* ላከ። መዳን፥ የእግዚአብሔር ልጆች መሆን፥ መንፈስ ቅዱስን መቀበል እነዚህ ሁሉ በአንድ ላይ የሚከናወኑ ነገሮች ናቸው። በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን በእርግጠኝነት እናውቃለን። የሰማያዊ አባታችንን በሕይወታችን መኖር በግላችን እንለማመዳለን። «አባ[20] አባት» ብለን እርሱን መጥራት እንችላለን። የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት በውስጣችን ስላለ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችን ምንም ጥርጥር አይኖረንም (ሮሜ 8፥14–16)።

7 የክርስቶስ መንፈስ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ወደ ልባችን እንደ ገባ ነጻ እንወጣለን። ባሪያነታችን ቀርቶ ልጆች እንሆናለን። ልጆች ከሆንን ደግሞ ወራሾች ነን (ሮሜ 8፥17)። የእግዚአብሔር ሀብት ሁሉ ወራሾች ነን። የእግዚአብሔር ልጆች መሆን ማለት ምን እንደ ሆነ እናስተውል። እግዚአብሔር ከሰጠን በረከቶች ሁሉ የሚልቅ ነው። አንዳንድ ሰዎች ሁሉም ሰው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ያስባሉ፤ ይህ ግን እውነት አይደለም። በእርግጥ እግዚአብሔር የሰው ሁሉ ፈጣሪ ነው፤ ቢሆንም የሁሉም አባት አይደለም። በክርስቶስ የሚያምኑ ብቻ እግዚአብሔርን አባታቸው አድርገው መጥራት ይችላሉ (ዮሐ. 1፥12–13፤ ገላ. 3፥16)። በየትኛውም ሌላ ሃይማኖት እግዚአብሔር አባት ተብሎ አይጠራም። የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች እግዚአብሔርን አያውቁትም። ምክንያቱም እግዚአብሔርን እንደ አባት ስለማያውቁት ነው። እግዚአብሔር ሕያው፥ ቅዱስ፥ ሁሉን ቻይ፥ ሁሉን የሚያውቅ እንደ ሆነ ያውቃሉ። እግዚአብሔር ግን ከእነዚህ ሁሉ በላይ ነው። እግዚአብሔር አፍቃሪና መሐሪ የሆነ ሰማያዊ አባታችን ነው። በክርስቶስ የምናምን እኛ ደግሞ ልጆቹ ነን።

ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች ያለው ጥንቃቄ (4፥8–20)

8–9 የገላትያ ሰዎች አስቀድሞ የሰይጣንና የርኩሳን መናፍስቱ ባሪያዎች ነበሩ። የማይሰ ሟቸውንና የማይረዷቸውን አማልክት ያልሆኑትን ጣዖታትን ያመልኩ ነበር (1ቆሮ. 8፥4)። *የዚህ ዓለም ሥርዓት* ባሪያዎች ነበሩ (ቁ. 3)።

አሁን ግን እውነተኛውን ሕያው አምላክ አውቀዋል፤ እርሱም አባታቸው ነው። እነርሱን ልጆቹ አድርጓቸው የመንፈሳዊ ሀብቱ ወራሾች ሆነዋል። ነፃነትና የዘላለም ሕይወት ሰጥቷቸዋል። *ታዲያ* የገላትያ ክርስቲያኖች ሊያድናቸው ወደማይችሉት *ደካሞችና የማይጠቅሙ ወደ ሆኑት የዓለም ሥርዓቶች* (ቁ. 9) ለመታሰር እንዴት ዘወር ሊሉ ቻሉ? (ቆላ. 2፥8 ይመለከቷል)። በዚህ ቦታ *ደካሞችና የማይጠቅሙ የዓለም ሥርዓቶች* የተባሉት በቁ. 3 *የዚህ ዓለም ሥርዓት* ተብሎ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ናቸው። በዚህ ቦታ ጳውሎስ በተለይ ስለ አይሁድ የማንጻት ሥርዓት በማሰብ ነው የጻፈው።

ሰዎች እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚፈልጉበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚለው ዋና ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚፈልጉት ለራሳቸው በረከትን ለማግኘት ሲሉ ነው። በክርስቶስ የምናምን እኛ ግን እግዚአብሔርን ለማስደሰት የምንፈልገው እግዚአብሔር ስለ ሰጠን በረከቶች ነው። ስለ ተደረገልን ምስጋናችንን እናቀርባለን። ልጆቹ ስለ ሆንን እንደ ልጆቹ ለመሆን እንፈልጋለን። ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች እንዲህ ብሏል. . . *በጌታ ብርሃን ውስጥ ስለ*

---

[20] አባ በአራማይክ ቋንቋ «አባቴ» ማለት ነው። አራማይክ በአዲስ ኪዳን ዘመን በመከከለኛው ምሥራቅ በነበሩ አያሌ ሰዎች ይነገር የነበረ ቋንቋ ነው። ይሽው ቋንቋ በኢያሱስና በደቀ መዛሙርቱም ይነገር ነበር (ማር. 14፥36 ይመለከቷል)።

ሆናችሁ፥ በብርሃን እንደሚኖሩ ሰዎች ኑሩ (ኤፌ. 5፥8)። ከዚህ በመነሳት በክርስትና እምነትና በሌሎች ሃይማኖቶች መካከል ያለውን ልዩነት ማየት እንችላለን። ሌሎች ሃይማኖቶች እንድትድን ታዘዝ ሲሉ ክርስትና ግን ስለ ዳንህ ታዘዝ ይላል። በአንድ በኩል አንዳንድ ጥቅሞችን ለማግኘት ሰዎች እግዚአብሔርን ይታዘዛሉ። በሌላ በኩል ክርስቲያኖች ጥቅማ ጥቅሞቹን ስለ ተቀበሉ፥ እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ነገር ይታዘዛሉ።

ሰው ሃይማኖታዊ ሕግጋትንና ሥርዓ ቶችን ስለ ፈጸመ ይድናል የሚለውን እምነት የሚከተሉ ሰዎች ስተዋል። የሃይማኖት ሥርዓቶችን በመከተል ደኅንነትን ለማግኘት መጣር ከንቱ ድካም ነው። ደኅንነት የሚገኘው በእምነት ጸጋውን በመቀበል ብቻ ነው (ኤፌ. 2፥8)። የገላትያ ክርስቲያኖች ይህን መዘንጋት ጀምረዋል።

ስለዚህ እኛም ራሳችን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የምንጥረው ለምንድን ነው? ፈቃዱን የምናደርገው ደኅንነትን ለማግኘት ወይም በረከትን ለመቀበል ይሆንን? እንዲህ ከሆነ እንደ ተታለሉት የገላትያ ክርስቲያኖች እያደረግን ነው (ገላ. 3፥1)። ከዚህ ይልቅ ጸጋውን በላያችን ስላፈሰሰልን እግዚአብሔርን ልንታዘዘው ይገባናል። ሐዋርያው ዮሐንስ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስላፈቀረን እኛም እናፈቅራለን ሲል ጽፎአል (1ዮሐ. 4፥19)። አስቀድሞ የእግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ በእኛ ላይ ባይፈስ ኖሮ እርሱን ደስ ማሰኘት ባልቻልንም ነበር።

በውጪያዊው ገጽታ የክርስቲያኖችና የሌሎች ሃይማኖቶች ባሕርይ ተመሳሳይ ሊመስል ይችላል። ሁለቱም እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ይጥራሉ። ነገር ግን ልዩነታቸው እርሱን ለማስደሰት የሚፈልጉበት ምክንያት ላይ ነው። የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚጥሩት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ነው። የክርስቶስ ተከታዮች እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚጥሩት እርሱ ስላደረገላቸው ነገር ለእርሱ ሲሉ ነው።

10–11 በእነዚህ ቁጥሮች ጳውሎስ ስለ ገላትያ ክርስቲያኖች ያለውን ፍራቻ ይገልፃል። እነዚህ ሰዎች የአይሁድን ሥርዓትና ወግ እንደ ገና መከተል ጀምረዋል። የአይሁድ የበዓል ቀናትንና ሥርዓትን እየፈፀሙ ናቸው (ቆላ. 2፥20 ይመለከቷል)። የጳውሎስ ፍራቻ በእነርሱ መካከል የሠራው ሥራ ከንቱ እንዳይሆን ነው።

12 . . . *እንደ እኔ ሁኑ* (1ቆሮ. 11፥1)። ጳውሎስ «እኔን ምሰሉ» ይላል። «ከሕግ፥ *ከዚህ ዓለም ሥርዓት ነጻ ነኝ* (ቁ. 3)። አንተም ነጻ መሆን ትችላለህ። እንደ አይሁድ ለመምሰል አትሞክር።» ጳውሎስ *እኔ እንደ እናንተ ስለሆንሁ* ይላል ይህም «አይሁድ የሆንኩ እኔ እንደ እናንተ አሕዛብ ሆኛለሁ። ከአሁን ወዲህ ሕግን በመፈጸም ለመጽደቅ አልሞክርም። እናንተ አሕዛብ እንዳደረጋችሁት እኔም በእምነት ብቻ ክርስቶስን ተቀብያለሁ» ማለቱ ነው።

የገላትያ ክርስቲያኖች ጳውሎስን *አልበደሉትም*። እንዲያውም ይወዱት ነበር። ጳውሎስ አሁን የሚጠይቃቸው እርሱን መቃወ ማቸውን ትተው እንደ ቀድሞው እንዲወዱት ነው።

13 ጳውሎስ በመጀመሪያ ወደ ገላትያ ሰዎች በሄደ ጊዜ *በሕመም* ላይ ነበር። ምናልባት በሕመሙ ምክንያት ጉዞውን መቀጠል ባለ መቻሉ እስኪያገግም ድረስ በገላትያ መቆየት ግድ ሆኖበት ነበር። ስለዚህ የገላትያ ሰዎች የጳውሎስን ወንጌል የሚሰሙበት እድል አገኙ።

ጳውሎስ በምን ሕመም እንደታመመ በእርግጠኝነት ባይታወቅም አንዳንዶች የገላትያ ከተማ በሆነችው በልስጥራ በድንጋይ የወገሩት ውጤት ነው ይላሉ (የሐዋ. 14፥19–21)። ሌሎች ደግሞ ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 12፥7 ላይ የተናገረው የሥጋው መውጊያ እንደ ሆነ ይናገራሉ።

14 ጳውሎስ *ታማሚና* በዚህም ምክንያት ደካማ ቢሆንም፥ የገላትያ ክርስቲያኖች የክርስቶስን ኃይል በጳውሎስ ሕይወትና ንግግር ውስጥ ማየት ችለዋል (1ቆሮ. 2፥3–4፤ 2ቆሮ. 4፥7)። እግዚአብሔር ጳውሎስን *«የእኔ ኃይል የሚገለጠው በአንተ ደካማነት ስለ ሆነ ጸጋዬ ይበቃሃል»* አለው (2ቆሮ. 12፥9–10)። የገላትያ ክርስቲያኖች ጳውሎስን እንደ መልአክ እንዲያውም እንደ ክርስቶስ አድርገው ተመልክ ተውታል (የሐዋ. 14፥8–15)። *ታዲያ* አሁን ከእርሱ ለምን ዘወር አሉ?

15–16 *የነበራችሁ ደስታ ሁሉ የት ሄደ?* ብሎ ጳውሎስ ይጠይቃቸዋል። በሌላ አገላለጽ፥ በደኅንነትና በነጻነታቸው አግኝተውት የነበረው ደስታቸው ወዴት ሄደ? ማለት ነው። ሰይጣን ደስታቸውንና ነጻነታቸውን እየወሰደባቸው ነው። ሰይጣን የክርስቲያኖችን ደኅንነት ሊወስድ አይችልም (ዮሐ. 10፥18)፤ ነገር ግን የክርስቲያንን ደስታና የነጻነት ስሜትን ሊወስድ ይችላል።

ጳውሎስ ስለ ደስታ በዚህ ቦታ የሚናገረው በዓለም ሁኔታዎች ላይ ተደጋፊ ስለ ሆነው ሳይሆን ስለ መንፈሳዊው ደስታ ነው። ደስታ ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አንዱ ነው (ገላ. 5፥22)። ደስታን በሕይወታችን የምንለማመደው የሕግ ወይም የዓለም እስረኞች ባለመሆናችን ነው። እነዚህ የገላትያ ክርስቲያኖች ወደ ዓለም ሥርዓት፥ ወደ አይሁድ ልማድና ወግ ፊታቸውን አዙረዋል! በዚህም ደስታቸውን አጥተዋል።

የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች የክርስ ትናን እምነት ለመከተል በጣም ቀላል እንደ ሆነ ይገምታሉ። በአንድ በኩል ትክክለኞች ናቸው (ማቴ. 11፥28–29)። ቀላል የሆነበት ምክንያት ምንም ሕግ ስለ ሌለ አይደለም። ክርስቶስን መከተል ቀላል የሆነው እርሱን መከተል የምንችልበት በመንፈስ ቅዱስ ኃይልን ስለ ሰጠን እንዲሁም በደስታ ስለ ምንከተለው ነው።

በመጀመሪያ የገላትያ ሰዎች የጳውሎስን ወንጌል በመስማታቸው ደስተኛ ከመሆናቸው የተነሣ ለእርሱ ማንኛውንም እንደሚያደርጉ ያስቡ ነበር። *ዓይኖቻቸውን አውጥተው* እስከ መስጠት[21] ድረስ የሚቻል ከሆነ ፈቃደኞች ነበሩ። ታዲያ ጳውሎስ ያሉበትን ስህተት ስለ ነገራቸው ብቻ በጠላትነት እንደማያዩት ተስፋ አድርጓል።

ቀድሞ ወዳጆቻችን የነበሩ ወደ ጠላትነት ለመቀየር እንዴት ቀላል ነው! ደግሞም ስለ ስህተታችን የሚነግሩንን እንደ ጠላቶች ለመቁጠር እንቸኩላለን!

ሆኖም *እውነትን በፍቅር* ለመናገር ዘወትር የተዘጋጀን ልንሆን ይገባናል (ኤፌ. 4፥15)፤ ይህንም በማድረግ ጠላትን ልናፈራ እንችላለን። የምንናገረው *እውነት* ለመሆኑ እርግጠኞች እንሁን። በሐሜት መንገድ ሳይሆን ፊት ለፊት *በፍቅር* ለመናገርም እርግጠኞች እንሁን። እነዚህን ጥንቃቄዎች ልብ ብንል የስንፍና ንግግር ሌሎችንም የሚጎዱ ቃላትን ከመናገር እንጠበቃለን።

17 ጳውሎስ *ሌሎች ሰዎች* (ሐሰተኛ የአይሁድ መምህራን) *እናንተን ወደ እነርሱ ሐሳብ ሊያመጧችሁ በብርቱ ይፈልጓችኋል* ይላል። እነዚህ አስተማሪዎች የገላትያ ሰዎች እንዲከተሏቸው ይመክሯቸዋል። ታላቅ እና ተፈላጊ ለመሆን ብዙ ተከታዮችም እንዲኖሯቸው ይመኛሉ። የገላትያ ሰዎች ጳውሎስን ማገልገል ትተው እነርሱን እንዲያገለግሉ ይፈልጓቸዋል። ስለዚህ የገላትያ ክርስቲያኖችን *ከእኛ ለመለየት* ይፈልጋሉ ሲል ጳውሎስ ይናገራል። ይህም ማለት ከጳውሎስ ተለይተው ለሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚቀኑና በትጋት የሚያስቡ እንዲሆኑ ነው።

18 የገላትያ ክርስቲያኖች በመጀመሪያ ለጳውሎስ የሚያስቡ ነበሩ። የእርሱን ወንጌል ለመስማት ናፍቆት ነበራቸው። አሁን ግን ጳውሎስ ከእነርሱ ጋር ስለ ሌለ ዓላማቸው *ለመልካም ሳይደለ* (ቁ. 17) ለሐሰተኛ አስተማሪዎች በትጋት ማሰብ ጀመሩ። ጳውሎስ ይህ እንዳይሆን ይመክራቸዋል። ምንም እንኳን አሁን ከእነርሱ ጋር በአካል ባይሆንም፥ እርሱ የሰጣቸውን እውነተኛ ትምህርት እንዳይተው ይነግራቸዋል።

19–20 ጳውሎስ እንደ እናት በገላትያ የሚገኙ ቤተክርስቲያናትን ወልዷል። አሁን ግን እንደ ገና *በምጥ ጭንቅ* ላይ እንደ ሆነ ይናገራል። ምክንያቱም የገላትያ ክርስቲያኖች ከወንጌል ፊታ ቸውን መልሰዋል። እንደ ገና መወለድ ያስፈልጋቸዋል።

የጳውሎስ ልብና ፍላጎት ክርስቶስ በገላትያ ክርስቲያኖች ባሕርይ *እንዲታይ* ነው (ቁ. 19)። ይህ

---

[21] በመካከለኛው ምሥራቅ ባሉ አገሮች የተለመደ አባባል ነው። ትርጉሙም አንድ ሰው ለሌላው ማንኛውንም ነገር ያደርጋል ማለት ነው።

የማንኛውም እውነተኛ መጋቢና ሰባኪ ግብ ነው። የወላድ ምጥ ልጁ እስከሚወለድ ድረስ እንደማያቋርጥ የጳውሎስ ጭንቀም በገላትያ ክርስቲያኖች ውስጥ የክርስቶስ ባሕርይ *እስከሚታይ ድረስ* አያቋርጥም።

. . . *የክርስቶስ ባሕርይ በእናንተ እስኪታይ ድረስ*። የክርስቶስ ባሕርይ በእኛ *እስኪታይ* ማለት ክርስቶስ በእኛ ውስጥ በመንፈሱ እስከሚኖር ማለት ነው (ሮሜ 8፥10–11)። በተጨማሪም ክርስቶስን *ወደ መምሰል መምጣት ማለት ነው* (ሮሜ 8፥29፤ 2ቆሮ. 3፥18)። ደግሞም *ክርስቶስ ፍፁምና ሙሉ እንደ ሆነው እኛም ሙሉ ሰው እንድንሆን ማለት ነው* (ኤፌ. 4፥13)።

የአጋርና የሣራ ምሳሌ (4፥21–31)

21 ሰነፎቹ የገላትያ ክርስቲያኖች እንደ ገና በአይሁድ ሕግ ሥር ለመሆን በእርግጥ ከፈለጉ *ሕጉ የሚለውን መማር* ይኖርባቸዋል። እዚህ ቦታ ሕግ ተብሎ በጳውሎስ የተጠቀሰው የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት ናቸው።[22]

22–23 ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ሁለት ሴቶችን ጠቅሷል፤ አንደኛዋ አገልጋይ የሆነች ሌላኛዋ ነፃ ሰው የሆነች። *አገልጋይቱ ሴት* አጋር፥ የአብርሃም ሚስት የሣራ አገልጋይ ነበረች። የአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ እስማኤል የተወለደው ከአጋር ነው (ዘፍ. 16፥1–14፥15)።

ነፃይቱ ሴት ሣራ ናት። ሣራ በሕይወት ዘመኗ መካን ነበረች። እድሜዋም ዘጠና ዓመት ደርሶ ነበር። ልጅ የምትወልድበትም ጊዜ አልፎ ነበር (ዘፍ. 16፥1፤ 17፥17)። ሆኖም ለአብርሃም ወንድ ልጅ እንደምትወልድለት እግዚአብሔር ቃል ገባላት (ዘፍ. 17፥15–16)። የሣራ ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተወለደ ነው (ቁ. 29)፤ ይህም በእግዚአብሔር ኃይል መሆኑ ነው። የልጁ ስም ይስሐቅ ነበር (ዘፍ. 21፥1–3)።

24–25 አጋር የድሮው ቃል ኪዳን የነበረውን ሕጉን ትወክላለች። ሣራ ደግሞ አዲሱን ኪዳን (ጸጋን) ትወክላለች።

አጋር የሲና ተራራ ምሳሌ ናት (ቁ. 25)። የአይሁድ ሕግ ለሙሴ የተሰጠው በሲና ተራራ ላይ ነበር (ዘጸ. 31፥18)። ስለዚህ አጋር ከሕግ ሥር ያሉትን አይሁዳውያንን የምትወክል ናት። እንዲሁም ኢየሩሳሌም የአይሁድ ቅዱስ ከተማ ስለሆነች ኢየሩሳሌምንም ትወክላለች። (ሐሰተኞዎቹ የአይሁድ አስተማሪዎች ወደ ገላትያ የመጡት ከኢየሩሳሌም እንደ ነበር፥ በዚህም ምክንያት ጳውሎስ ይህን መልእክት እንደ ጻፈ ያስተውሏል)።

አጋር አገልጋይ ስለነበረች ልጆቿም አገልጋዮች ናቸው። የሕጉ አገልጋዮች ናቸው። አይሁዳውያን በሥጋ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ በመናገር ይኩራራሉ። ጳውሎስ ግን ልጆች ሳይሆኑ እንደ አገልጋይቱ ሴት ልጆች አገልጋዮች እንደ ሆኑ ይናገራል።

26 *ከላይ ከሰማይ የሆነችው ኢየሩሳሌም ግን ነፃ ናት*፤ ይህችኛዋ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር መንግሥት ናት (ዕብ. 12፥22፤ ራእ. 21፥2 ይመለከቷል)። ይህች ከተማ ክርስቶስ የሚኖርባትና ከሕግ ነፃነት ያለበት ናት። ሣራ ከላይ ከሆነችው ኢየሩሳሌም ጋር ትመሳሰላለች። እርሷ በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ «እናት» ነች። እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ ልጅ እንደሚያገኙ ለተሰጣቸው ተስፋ ውጤት ለሆኑ *በተስፋው ቃል መሠረት* ለተወለዱ (ቁ. 23) የአብርሃም እውነተኛ ወራሾች ለሆኑት እናት ነች።

27 እዚህ ቦታ ጳውሎስ ከኢሳ. 54፥1 ይጠቅሳል፤ *መካን የሆነችው ሴት ሣራ ናት። በደስታ እልል ትበል። ባል ካላት ሴት*[23] ከአጋር ይልቅ ብዙ ልጆች አሏት።

28 የእግዚአብሔር ተስፋ ይህም የእርሱ ቃል ኃይል ያለው ነው። ሕያው ቃል ነው። እርሱ ሕይወት ይሰጣል። ሣራ ምንም እንኳ የዘጠና ዓመት ሴት ብትሆንም በእግዚአብሔር ቃል ይስሐቅን ልትወልድ ቻለች። በተመሳሳይ መንገድ የገላትያ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተወልደዋል (ቁ. 29)። እነርሱም በተፈጥሮ የሥጋ ልጆች በመሆን ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ጸጋ የሰማይቱ ኢየሩሳሌም ዜጎች፥ የአብርሃም እውነተኛ ልጆች ሆነዋል። ታዲያ የገላትያ ክርስቲያኖች አሁን የአገልጋይቱ የአጋር ልጆች ለመሆን ወደ ኋላ መመለስ ለምን ይፈልጋሉ?

29 በዘፍ. 21፥9 *መሠረት በሥጋ ተራ በሆነ መንገድ* የተወለደው የአጋር ልጅ እስማኤል፤ *በመንፈስ ቅዱስ ኃይል* የተወለደውን የሣራን ልጅ ይስሐቅን አሳደደው። ጳውሎስ *ዛሬም እንዲሁ ነው* ይላል። ጳውሎስ በነበረበት ዘመን እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የተወለዱትን የክርስቶስ አማኞችን እንደ ሥጋ ፈቃድ የተወለዱት ሮማውያንና አይሁዶች ያሳድዷቸው ነበር። በሥጋ ወራሾች የሆኑት ሁልጊዜ በመንፈስ ወራሽ የሆኑትን ያሳድዳሉ።

30 በዘፍ. 21፥10 መሠረት ጳውሎስ «*ይህችን አገልጋይ* (አጋርን) *ከነልጅዋ* (እስማኤል) *ወዲያ አባርልኝ*» ይላል። አብርሃም ሣራ እንዳለችው አደረገ (ዘፍ. 21፥12–14)። የገላትያ ክርስቲያኖችም የሥጋ ልጆች የሆኑትን ሐሰተኛ አስተማሪዎችን *ማባረር* ይኖርባቸዋል።

31 በክርስቶስ የምናምን *የነፃይቱ ሴት* የሣራ ልጆች ነን። እኛ የተስፋው ልጆች ነን (ቁ. 28)፥ የእግዚአብሔር ስጦታ በሆነው በጸጋው የእርሱ ልጆች ነን። በክርስቶስ በማመን በተቀበልነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእርሱ ልጆች ሆነናል (ሮሜ 8፥14፤ ገላ. 3፥26)።

ስለዚህ እንዲህ ያለውን ስጦታ መጣል አይኖርብንም። ሕግን ወይም የማንኛውንም ሃይማኖት ወግና ሥርዓት በመፈጸም የእግዚአ ብሔርን ጸጋ አንጣል። እምነታችን በክርስቶስ ብቻ ይሁን።

ምዕራፍ 5

በክርስቶስ የሚገኝ ነፃነት (5፥1–12)

1 *ክርስቶስ ነፃ አውጥቶናል*። እርሱ ከሕግ እርግማን ይህም ከሞት ፍርድ አድኖናል (ገላ. 3፥13)። ለሞት በወህኒ እንደሚጠበቁ ሰዎች ነበርን። ክርስቶስ በእኛ ምትክ በመሞት ነፃ አወጣን (ሮሜ 7፥6)። በዚህ መንገድ ነፃ የወጣ እንደ ገና ወደ ወኅኒ ለመውረድ የሚሞክር ሰው በእርግጥ ጤናማነቱ ያጠራጥራል። የገላትያ ክርስቲያኖች እንዲህ ያለውን ነገር አድርገዋል። ከሕግ ወህኒ ቤት ነፃ ከወጡ በኋላ እንደ ገና ራሳቸውን መልሰው በዚሁ እስራት ውስጥ ጨምረዋል። ጳውሎስ *ስለዚህ ጸንታችሁ ቁሙ!* እንዲህ ያለው ነገር በሕይወታችሁ እንዲሆን አትፍቀዱ ይላል።

2 የገላትያ ሰዎች ራሳቸውን ከእስራት በታች ካደረጉበት ነገር አንዱ፥ የግርዘት ሥርዓት ነው። መገረዝ ስህተት አይደለም (የሐዋ. 16፥3)። ነገር ግን በመገረዝ ደኅንነት እንደሚገኝ ማሰቡ ስህተት ነው። በመገረዝ ወይም ሌላ ሥራ በመሥራት እንደምንድን የምናምን ከሆነ፥ የክርስቶስን ሥራ ከንቱ አድርገናል ማለት ነው። ክርስቶስንም መቃወማችን ነው። ክርስቶስንም ማመን ምንም ዋጋ አይኖረውም ማለት ነው። እምነታችንን በክርስቶስ ብቻ ካላደረግን ክርስቶስ እኛን አያድንም። የዳንነው በክርስቶስ በማመንና ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን ክርስቶስን በማመን ብቻ ደኅንነትን አግኝተናል።

3 ጳውሎስ የገላትያ ክርስቲያኖች መገረዝ ብቻውን ዋጋ እንደሌለው ያስታውሳቸዋል። ሕግን በመጠበቅ እንደሚድኑ ተስፋ ካደረጉ የተወሰኑትን ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ሕጉን መፈጸም አለባቸው። በአይሁድ ሕግ ደግሞ ከስድስት መቶ የሚበልጡ የተለያዩ ትእዛዛትና ሥርዓቶች አሉ። እነዚህን ሁሉ ሙሉ በሙሉ መፈጸም የማይቻል ነው (ገላ. 2፥15–16፤ 3፥10 ይመለከቷል)።

---

[22] የመጀመሪያዎቹ አምስት የኦሪት መጻሕፍት፥ ሕግ ወይም የሙሴ ሕግ በመባል ይታወቃሉ።

[23] ሣራ ልጅ ባልወለደች ጊዜ አብርሃም አጋርን «ሁለተኛ ሚስቱ» እንድትሆነው ወሰዳት (ዘፍ. 16፥1–4)። ስለዚህ ሣራ «ባል እንደ ሌላት» ስትሆን አገልጋይዋ አጋር ግን ባል ያላት ሴት ተባለች።

4 ሕግና ጸጋ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ናቸው። ስለዚህ ሁለቱንም በአንድነት ለማስኬድ አንችልም። የገላትያ ሰዎች የጸደቁትና የዳኑት በጸጋ ነው። አሁን ግን እምነታቸውን ሕግን በመጠበቅ በራሳቸው *ሥራና ጥረት* ላይ ማድረግ ጀምረዋል። በዚሁ ከቀጠሉ ጸጋቸውን ያጣሉ። አዳኛቸው ከሆነው *ከክርስቶስ ይለያሉ*።

አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስን በጸጋ ከተቀበሉ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ (ማር. 4፥16–17)። ወደ ቀደመው የሃይማኖት *ሥርዓታቸው* ተመልሰዋል። እንደ ገላትያ ሰዎች እንዲህ ያለውን ነገር የሚያደርጉ *ከጸጋው ርቀዋል*። ስለዚህ ጳውሎስ *ጸንታችሁ ቁሙ፤* እንዲህ ያለው ነገር በሕይወታችሁ አይሁን ይላል (ቁ. 1)።

ክርስትናን ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ለማዋሀድ አይቻልም። ቀድሞ ከምናመልካቸው አማልክት ጋር ክርስቶስን መደመር አንችልም። እምነታችንን በክርስቶስ ወይም በቀድሞው ሃይማኖታችን ላይ እናደርጋለን እንጂ በሁለቱም ላይ አናደርግም። ክርስቶስ ወደ መንግሥተ ሰማይ ከሚወስዱ መንገዶች አንዱ ሳይሆን፥ አንድና ብቸኛ መንገድ ነው (ዮሐ. 14፥6 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

አንድ ሰው በሁለት የተለያዩ መንገዶች ላይ በአንድ ጊዜ መሄድ አይችልም። ክርስቶስን ለደኅንነቱ ያመነና የቀድሞ ሃይማኖቱን በማመን ለመቀጠል የሚያስብ ሰው ራሱን ያታልላል። ይህን የሚያደርግ ማንኛውም ሰው በእውነት በክርስቶስ የሚያምን አይደለም፤ ደኅንነትንም አያገኝም።[24]

5 በገላትያ ያሉ የአይሁድ አስተማሪዎች፥ ሰው ሕግን በመፈጸም ጻድቅ ይሆናል ብለው ያስተምሩ ነበር። ጳውሎስ ግን የክርስቶስ ጽድቅ የሆነው የሚገኘው *በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት በእምነት ነው*። በክርስቶስ በማመናችን ጻድቃን ተባልን (ሮሜ 5፥1–2)፤ በዚህም ከኩነኔ አመለጥን ይላል (ሮሜ 8፥1)።

6 በክርስቶስ ኢየሱስ ደኅንነት ለማግኘት አንድ ሰው ቢገረዝ ወይም ባይገረዝም ምንም ልዩነት አያመጣም። በመገረዝ የሚገኝ ጥቅም፥ ባለ መገረዝ ደግሞ የሚቀር ጥቅም የለም (ገላ. 6፥15)። በክርስቶስ በማመን ብቻ ድነናል።

እዚህ ቦታ ላይ እምነት ምንድን ነው? የሚል ዋና ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ብዙ ሰዎች «እኔ አምናለሁ» ይላሉ። ይህ ምንም ትርጉም የለውም (ማቴ. 7፥21 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ትርጉም የማይኖረው ለምንድን ነው? ምክንያቱም እምነታቸው እውነተኛ አይደለምና። እምነት ራሱን በፍቅር አማካይነት ይገልፃል፤ ካልገለጸ ግን የሐሰት እምነት ነው (ያዕ. 2፥14፥17 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

በክርስቶስ ስናምን መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወታችን ይመጣል፤ በመንፈስ አማካይነት የእግዚአብሔር ፍቅር *በልባችን ይፈሳል* (ሮሜ 5፥5)። ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያውና ዋነኛው ፍሬ ነው (ቁ. 22)። ስለዚህ እውነተኛ እምነት ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራችን በልባችን ፍቅርን ያፈራል። ፍቅር በልባችን ከሆነ ከሕይወታችን ወደ ሌሎች ሕይወት መፍሰስ ይኖርበታል። በሌላ አገላለጽ በውስጣችን ያለውን ፍቅር ለባልንጀራችን መግለጽ ይኖርብናል። እውነተኛ እምነት ሁልጊዜ *ራሱን በፍቅር ይገልጻል*።

7 የክርስቲያን ሕይወት እንደ ሩጫ ውድድር ነው (2ጢሞ. 4፥7፤ ዕብ. 12፥1)። የገላትያ ሰዎች ይህን በጥሩ ሁኔታ ጀምረው ነበር። ነገር ግን ሐሰተኛ አስተማሪዎች አደናቀፉአቸው። ይህም ብቻ ሳይሆን ሩጫውን በተሳሳተ አቅጣጫ ለመሮጥ ጀመሩ። ዓይኖቻቸውን ከኢየሱስ ላይ አነሡ (ዕብ. 12፥2)። የገላትያ ሰዎች *እውነትን መታዘዝ ተው*። *እውነቱን ማመን* ብቻ ሳይሆን መታዘዝም አስፈላጊ ነው።

8 ጳውሎስ የገላትያ ክርስቲያኖች *እንዲህ ዓይነቱ ምክር* (ሕግን መፈጸም ደኅንነትን ለማግኘት አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚናገረው የተሳሳተ ትምህርት) *ከጠራችሁ ከእግዚአብሔር የመጣ አይደለም* ይላቸዋል።

9 ሌላው ቀርቶ እንዲህ ያለው የስህተት ትምህርት፥ ጥቂቱ ከግምት በላይ የሆነ ጥፋት ያስከትላል። *ጥቂት እርሾ* (የስህተት ትምህርት) *ሊጡን በሙሉ ያቦካዋል*። በቤተክርስቲያን ውስጥ ይሠራጫል (1ቆሮ. 5፥6 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

10 ሆኖም ጳውሎስ በገላትያ ሰዎች ተስፋ አልቆረጠም። እርሱ ካስተማራቸው ከእውነተኛው ወንጌል ወደ ሌላ ሃሳብ ዘወር አይሉም በማለት ጳውሎስ በእርግጠኝነት ይናገራል። የገላትያ ሰዎችን ግራ የሚያጋቡት የሐሰት ' አስተማሪዎች በእግዚአብሔር ለመቀጣት *ፍርድ ይጠብቃቸዋል*።

11 አንዳንድ የገላትያ ሰዎች ከመወናበዳቸው የተነሣ ጳውሎስ *መገረዝ እንደሚያስፈልግ ያስተምራል* ሲሉ በሐሰት ከሰውት ነበር። ጳውሎስ መልስ ሲሰጥ፤ ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ አይሁዳውያን እርሱን ባላሳደዱትም ነበር። አይሁዳውያን ያለ ማቋረጥ ስለሚያሳድዱት ክሱ ሐሰተኛ ነው።

መገረዝ አስፈላጊ እንደ ሆነ ጳውሎስ ቢሰብክ ኖሮ፤ መሰቀል እንቅፋት መሆኑ ይቀር ነበር። ሰዎች በመገረዝ የሚድኑ ቢሆኑ ኖሮ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ መሞቱ መስበክ አያስፈልግም ነበር። የክርስቶስ መስቀል ለአይሁዳውያን *እንቅፋት፥ የመሰናከያ ድንጋይ* ነበር (1ቆሮ. 1፥23)። አይሁዳውያን «በመስቀል ላይ የተሰቀለ አንድ ወንጀለኛ ሰውን እንዴት ሊያድን ይችላል? ይህ የማይመስል ነገር ነው» በማለት ያፌዛሉ። ስለዚህ ሰው የሚድነው በመገረዝ ሳይሆን በተሰቀለው ክርስቶስ በማመን ነው በማለት ጳውሎስ ስለሚሰብክ ይቃወሙታል።

ሰዎች ስለ መስቀል መስማት አይፈልጉም። ክርስቶስ ከመስቀል ላይ ወደ ታች እየተመለከተ «በእኔ እመኑ፤ እኔም አድናችኋለሁ» ይላል፤ ሰው ግን «እኔ ራሴን ማዳን እችላለሁ፤ የማንንም እርዳታ አልፈልግም፤ ብቁ ስለሆንኩ ሕግን መጠበቅ እችላለሁ» ይላል። ስለዚህ ሰው እንዲህ በማለቱ የመስቀሉን መልእክት ይቃወማል መስቀል «የመሰናከያ ድንጋይ» ሆኖበታል።

12 ጳውሎስ ለመዳን መገረዝ አስፈላጊ ነው እያሉ ግራ ለሚያጋቡ የአይሁድ አስተ ማሪዎች ጠንከር ያሉ መልእክቶች ያስተላልፋል። «እንግዲህ እነዚህ ግራ የሚያጋቡአቸው ሰዎች ቢፈልጉ መገረዝ ብቻ ሳይሆን ይቆረጡ» በማለት ጳውሎስ ይናገራል። ጳውሎስ በነበረበት ዘመን አረማውያን በሆኑ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ አምላኮቻቸውን ለማስደሰት ሲሉ ይሰለቡ ነበር። የሐሰት አስተማሪዎችም ከፈለጉ እንዲህ ያድርጉ ይላል።

በመንፈስ የሚገኝ ሕይወት (5፥13–26)

13 እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በነፃነት እንዲኖር ነው እንጂ በባርነት እንዲኖር አይደለም (ዮሐ. 8፥32፥36፤ ሮሜ 8፥2፤ ገላ. 5፥1)። ጳውሎስ ግን *ነፃነታችሁ የሥጋን ምኞት መፈጸሚያ ምክንያት አይሁን*[25] ይላል።

ክርስቲያኖች ስለሆንን ነፃነት ያለን ሰዎች ነን፤ ነገር ግን ኃጢአትን ለማድረግ ነፃነት የለንም (ሮሜ 6፥1–2፡12–14)። ከሕግ እስራት ነፃ ነን፤ ሕግን ለመተላለፍ ግን ነፃነት የለንም። ነፃነት ያለን ሰዎች ብንሆንም ሕይወታችን ቅዱስና ንጹሕ ሊሆን ይገባዋል (ማቴ. 5፥48፤ 1ጴጥ. 1፥15–16)።

የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች የክርስቲያኖች ኑሮ ሕግ ስለሌለው ልቅ ነው በማለት ይወነጅላሉ። ክርስቲያኖች ስለ ሌሎች ባለመጠንቀቅ የፈለጉትን ያደርጋሉና መጥፎ ባሕርይ አላቸው ተብሎ ይነገራል። እንዲህ ያለው ክስ ብዙውን ጊዜ እውነተኛ እንደ ሆነ ቢነገርም እንዲህ ሊሆን አይገባም።

ክርስቲያኖች ነፃ ብንሆንም በሕግ ሥር እንኖራለን፤ ያ ደግሞ የፍቅር ሕግ ነው (ማር. 12፥29–31፤ ዮሐ. 13፥34–35 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። እርስ በርሳችን በፍቅር ልንረዳዳ ነፃነት አለን። አገልጋይ (ባሪያ) ጌታውን ከፍቅር

---

[24] 24 አስፈላጊ አይደለም (ተርጓሚው)።

[25] የሥጋ ምኞት የሚለው የሰውን ሃጢያተኛ ባህሪ ይመለከታል። ለተጨማሪ ማብራሪያ በቃላት መፍቻው «ሥጋ» የሚለውን ይመለከቷል።

የተነሣ ሳይሆን ከግዴታና ከፍርሃት የተነሣ ያገለግለዋል። እኛ ግን ነፃ ስለሆንን በፍቅር እርስ በርሳችን እንረዳዳለን። ነፃ የሆነ ሰው በነፃነት ሌላውን ይወዳል።

ክርስቲያኖች ከኃጢአት ባርነት ነፃ ወጥተናል፤ ሆኖም ራሳችንን ለእግዚአብሔር አገልጋዮች አድርገን ሰጥተን (ሮሜ 6፥22) ወደ ሞት ከሚመራው ከቀድሞው ጌታችን ከሕግ፥ ነፃ ወጥተን ወደ ሕይወት ለሚመራን አዲሱ ጌታ አገልጋዮች ሆነናል። ሕግን የምንጠብቀው በፍርሃት ነበር። አሁን ግን ክርስቶስን የምንታዘዘው ከፍርሃት ሳይሆን ከፍቅር የተነሣ ነው (ዮሐ. 14፥15፡21፤ 1ዮሐ. 4፥18)።

14 በገላትያ የነበሩ የአይሁድ አስተማሪዎች ስለ ፍቅር ማወቅ ነበረባቸው። የገዛ ራሳቸው ሕግ በአንድ ትእዛዝ ይጠቃለላል፤ ይህም *«ሰውን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ»* የሚል ነው (ዘሌ. 19፥18፤ ማቴ. 22፥35-40፤ ማር. 12፥31፤ ሮሜ 13፥8-9፤ ገላ. 6፥2)።

እንደ አይሁድ ሕግ ጳውሎስ በዚህ ቦታ ልንከተለው የሚገባንን አዲስ ሕግ እየሰጠን ነውን? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ሌላ አዲስ ሕግ የሚጨምር ከሆነ ክርስቲያኖች ከአይሁዳዊ ምንም የተለየን አይደለንም።

ይህ አዲስ የፍቅር ሕግ እንደ አይሁድ ሕግ ወይም እንደ ሌሎች ሃይማኖቶች ሥርዓቶችና ሕጎች አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ አይሁዶችና የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ሕጎቻቸውን የሚፈጽሙት ለመዳን ነው። ክርስቲያኖች ግን የፍቅርን ሕግ የምንጠብቀው ለመዳን ብለን ሳይሆን ስለዳንን ነው። ሕግን ስለ ጠበቅን ሳይሆን ክርስቶስን በማመናችን ድነናል። የዳንነው የክርስቲያን ሥርዓትን ስለጠበቅን ሳይሆን ክርስቶስ አዳኛችንን ስለ ተከተልን ነው። ደኅንነታችን ከሃይማኖት የተነሣ ሳይሆን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ የተገኘ ነው።

ሁለተኛው ልዩነት ደግሞ አይሁዶችና የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች ሕጎቻቸውን ለመከተል የሚሞክሩት በራሳቸው ጥረት በመሆኑ ነው። ክርስቲያኖች ግን የፍቅርን ሕግ በራሳችን ብርታት ለመፈጸም አንሞክርም፤ የክርስቶስን ቅዱስ መንፈስ ተቀብለናል፤ በዚህም መንፈስ ኃይል ብቻ የፍቅርን ሕግ እንከተላለን። ፍቅራችን ከእኛ የተፈጥሮ ባሕርይ የመጣ ሳይሆን በውስጣችን ከሚኖረው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። ሌሎችን የምንወደው *በልባችን በመንፈስ ቅዱስ ከፈሰሰው* ፍቅር የተነሣ ነው (ሮሜ 5፥5)።

በእርግጥ ክርስቲያኖች የፍቅርን ሕግ መታዘዝ ይኖርባቸዋል። በመንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ይህን ሕግ እንድንፈጽም ኃይል ይሰጠናል። የምንሠራው ሁሉ በእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል ነው።

እዚህ ላይ፥ ሌላ ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፤ ሕጉ *ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ* ይላል። *እንደ ራስህ* የሚለው ምን ማለት ነው? ራሳችንንና ባልንጀራችንን እኩል እንወዳለን ማለት ነው? አይደለም። ባልንጀራችንን ራሳችንን ከምንወደው ይበልጥ ልንወድ ይገባናል። ኢየሱስ *«ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ»* ብሏል (ማር. 8፥34)። የኢየሱስን ምሳሌ ተከትለን ለሌሎች ራሳችንን ለመስጠት እንኳ የተዘጋጀን ልንሆን ይገባናል (ዮሐ. 15፥13)።

ስለዚህ *እንደ ራስህ* የሚለው አባባል መንፈሳዊ የሆንን እኛ ተፈጥሮአዊው ሰው ራሱን የሚወደውን ያህል ሌሎችን ልንወድ ይገባናል ማለት ነው። ተፈጥሮአዊው ሰው ከሁሉ በፊትና ከሁሉ በላይ ራሱን ይወዳል። መንፈሳዊ የሆንን እኛ ደግሞ ሌሎችን ከራሳችን አስቀድመንና አስበልጠን ልንወድ ይገባናል።

ጳውሎስ እዚህ ቦታ የጠቀሰው *አንተም እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም አሳብህ፥ በፍጹም ኃይልህ ውደድ* የሚለውን የመጀምሪያውን ትእዛዝ አይደለም። እያንዳንዱ አይሁድ ይህ ትእዛዝ የመጀመሪያውና ትልቁ እንደ ሆነ ያውቃል። ጳውሎስ ይህን መጥቀስ አላስፈለገውም። ቢሆንም እኛ እግዚአብሔርን ካልወደድን ሌሎች ሰዎችን መውደድ እንደማንችል ልናስተውል ይገባናል። ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ሁልጊዜ መቅደም ይገባዋል።

ሆኖም በሌላ በኩል ሰውን ሁሉ እንደ ራሳችን ካልወደድን እግዚአብሔርን እንወደዋለን ማለት አንችልም። ለእግዚአብሔር ያለ እውነተኛ ፍቅር ሁልጊዜ ለሰው ወዳለ ፍቅር ያመራል (1ዮሐ. 4፥20-21)። ባልንጀራችን ማነው? ባልንጀራችን የእኛን እርዳታ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ነው (ሉቃ. 10፥25-37)። ስለዚህ ሁሉም ባልንጀራችን ነው።

15 መንፈስ ቅዱስ በሌለበት ፍቅር የለም። ፍቅር በሌለበት እርስ በርስ መነካከስና መበላላት አለ። ይህም እርስ በርስ መቀዋወም፥ መካሰስና መተማማት ማለት ነው።

እርስ በርሳችን ከተካሰስንና ከተማማን ቤተክርስቲያን ትጠፋለች። ኢየሱስም በማርቆስ 3፥25 *«አንድ ቤተሰብ እርስ በርሱ ከተለያየ ጸንቶ መኖር አይችልም»* ብሏል። ስለ አንድ ሰው እውነተኛ የሆነ፤ ነገር ግን መጥፎ ወሬ ብናወራ ቤተክርስቲያን መፍረሷ አይቀርም። ሐሜት ስለ ሰዎች እውነት ይሁን ውሸት መጥፎ ወሬ ማውራት ማለት ነው። ወንድማችን በስህተት ወይም በኃጢአት ቢወድቅ ልናደርገው የሚገባን በመጀመሪያ ለብቻው እርሱን መውቀስ ነው። ስለ ራሱ መልስ እንዲሰጥ እድል ሊኖረው ያስፈልጋል (ማቴ. 18፥15 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ወደ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ልንሄድና ልንናገር የምንችለው ከዚህ በኋላ ነው (ማቴ. 18፥16 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። እርስ በርሳችን ግን ስለ ወንድማችን ወይም እህታችን ክፉ ወሬ ልናቀርብ አልተፈቀደልንም።

16 መንፈስ ቅዱስን የተቀበልን እኛ *በመንፈስ ልንኖር፥* በመንፈስም ልንመራ ይገባናል። ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችንን (ሥጋችንን) በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ማስገዛት አለብን። ይህን ካደረግን መንፈስ ቅዱስ *የኃጢአተኛ ተፈጥሮአችንን ምኞት* እንዳናፈጽም ይገታናል። በሌላ አነጋገር መንፈስ ቅዱስ ኃጢአት እንዳናደርግ ይጠብቀናል። ነገር ግን በኃጢአት እንዳንወድቅ ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ያለ ማቋረጥ ልናስገዛ ይገባናል። ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ተደግፈን መጓዝ አለብን።

በመጨረሻ በመንፈስ ባንኖር፥ በመንፈስ ቅዱስ ባንመራ ራሳችንን የእግዚአብሔር ልጆች ብለን ልንጠራ አንችልም (ሮሜ 8፥14)።

17 ምንም እንኳ እምነታችንን በክርስቶስ ላይ ብናደርግና መንፈስ ቅዱስን የተቀበልን ብንሆን የድሮው ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን ሙሉ ለሙሉ ሞቶ አይወገድም። በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ቢሆንም ሁልጊዜ ከእኛ ጋር አለ፤ መንፈስ ቅዱስንም ሁልጊዜ ይቃወማል። ባመንን ጊዜ የተቀበልነውን አዲሱን ሰውነት፥ አዲሱን መንፈሳዊ ሕይወት ይቃወማል፤ ስለዚህ በነፍሳችን የማያቋርጥ ውጊያ ይካሄዳል፤ ይህም ውጊያ እስከምንሞት ይቀጥላል። አዲሱ መንፈሳዊ ሕይወት መልካም የሆነውን ለማድረግ ይፈልጋል አሮጌው ኃጢአተኛ እኔነት ግን ያግደዋል (ሮሜ 7፥18-19)።

በመንፈስ ቅዱስ እስከኖርን ድረስ (ቁ. 16)፥ ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን በቁጥጥር ሥር ይሆናል። በመንፈስ ስንኖር ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን ይሰቀላል፤ ኃይል አልባ ይሆናል (ሮሜ 6፥6-7፡12-14፤ ገላ. 2፥20፤ 5፥24 ማብራሪያውን ይመለከቷል)። በመንፈስ ስንኖር የኃጢአተኛ ተፈጥሮ ምኞት ኃጢአት በማድረግ አንፈጽምም፤ ምክንያቱም ኃጢአተኛ ተፈጥሮ በእኛ ላይ ኃይል አይኖረውም። ይህ በክርስቶስ ያገኘነው ጥልቅ ነፃነት ነው።

ነገር ግን በመንፈስ መኖርን ብንተው፥ በመንፈስ መደገፍን ብናቆም ወዲያው የቀድሞው ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን ሕይወት ዘርቶ ከሰቀልንበት ይወርዳል፤ ከዚያም እንደ ገና በእርሱ ሥር እንሆናለን፤ ነፃነታችንን እናጣለን፤ ደግሞም እንደ ገና በኃጢአት ቀንበር ሥር እንወድቃለን።

18 *በመንፈስ ብትመሩ ግን የሕግ ተገዢዎች አትሆኑም።* እዚህ ቦታ የተጠቀሰው የአይሁድ ሕግ ሲሆን ጳውሎስ በሌላ ስፍራ *የኃጢአትና የሞት ሕግ* ብሎ ይጠራዋል (ሮሜ 8፥2)። ከሕግ በታች መሆን ከእርግማን በታች መሆን ማለት ነው (ገላ. 3፥13)፤ ይህም ከሞት ፍርድ፥ ከኃጢአት ኃይል በታች መሆን ነው። ጳውሎስ በመንፈስ ብንመራ እንዲህ ካለው ሕግ በታች አንሆንም ይላል። በእርግጥ በነፍሳችን በሥጋና በመንፈስ መካከል ፍልሚያ አለ። ነገር ግን በየእለቱ በፍልሚያው አሸናፊ ልንሆን እንችላለን። በኃጢአት ልንሸነፍ አይገባንም።

እንዴት በኃጢአት ላይ ድልን እንቀዳጃለን? ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን በመፍቀድ ነው።

በራሳችን የምናደርገው ትግል የለም። ራሳችንን ከመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ማድረግ ነው (ሮሜ 8፥9)። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ድል አድራጊዎች ሆነን እንዘልቃለን።

አይሁድና የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ሕጎችንና ወጎችን በመፈጸም በኃጢአት ከመውደቅ እንደሚተርፉ ያምናሉ። ይህ ግን እውነት አይደለም። ሕጎች ሰዎች ኃጢአት እንዳይሠሩ የሚያደርግ ኃይል የላቸውም። በእርግጥ ውጪያዊ የሆኑ የሚታዩ ኃጢአቶችን እንዳይፈጽሙ ያግዱቸው ይሆናል፤ ውስጣዊ ከሆኑት ኃጢአቶች ግን ሊያግዱቸው አይችሉም። ሕጎች የሰዎችን ልብ ከኃጢአት ሊያነጹ አይችሉም። በውስጣችን በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በልባችን ባለ ኃጢአት ላይ ድልን እናገኛለን። ልናስተውለው የሚገባን ነገር እግዚአብሔር በቅድሚያ የሚመለከተው ውጪያዊ የሆነውን ተግባራችንን ሳይሆን ልባችንን ነው (1ዜና 28፥9፤ ኤር. 17፥10፤ ማር. 7፥6)።

ታዲያ ክርስቲያኖች ለምን ኃጢአት ይሠራሉ? የሚል ጥያቄ ልንጠይቅ እንችላለን። ኃጢአትን የሚያደርጉት ኃጢአት ለመሥራት ስለሚፈልጉ ወስነው ያደርጋሉ። ፈተና በሚመጣበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ «ወደ እኔ ና/ነይ» ይላል። እኛ ግን አንቀበልም። ከዚያም ወዲያው በኃጢአት እንወድቃለን። በኃጢአት መውደቅ ብቻ አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስ ተገቢ ባልሆነ ስፍራ መኖር ስለማይፈልግ ከእኛ ይርቃል። መንፈስ ቅዱስ ያዝናል። ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑ የሚለው ለዚሁ ነው (ኤፌ. 4፥30)። ኃጢአታችንን በተናዘዝንና ንስሐ በገባን ጊዜ ብቻ መንፈስ ቅዱስ ወደ እኛ ተመልሶ ይመጣል።

በመካከላችን መንፈሳዊ ሕይወቱ የደረቀበት፥ መንፈሳዊ ኃይል የሌለው አለ? ካለ ይህ ሰው ልቡን ይመርምር፤ መንፈስ ቅዱስም በውስጡ እንዳይኖር ያደረገ ኃጢአት እንዳለ ይመልከት። ያንን ኃጢአት ወደ ብርሃን ያውጣ፤ ከዚያም ይራቅ። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር እየራቅን የምንሄደው የተሰወረ ኃጢአት በልባችን ስላለ ነው።

19–21 ጳውሎስ ከእግዚአብሔር የሚለዩንን ኃጢአቶች በዝርዝር አቅርቧል። የኃጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎች የሆኑትን እያንዳንዳቸውን በትኩረት እንመልከት። ከእነዚህ ውስጥ በሕይወታችን የሚገኙ ይኖሩ ይሆን? (ሮሜ 1፥29–31 ይመለከቷል)።

ኃጢአትን በሌሎች ሰዎች ላይ በፍጥነት እናያለን። ነገር ግን እነዚያኑ ኃጢአቶች በእኛ ላይ ቶሎ አንመለከትም፤ በራሳችን ዓይን ጻድቃን ነን።

የሌሎቹን ሳይሆን የራሳችንን ኃጢአት ልንመለከት ይገባናል። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የተሰወሩ ኃጢአቶችን እንዲያሳየን ልንጸልይ ይገባናል (መዝ. 139፥23–24)።

በዚህ ስፍራ ከተጠቀሱት *ዐሥራ አምስት* ኃጢአቶች ስምንቱ በክርስቲያኖች መካከል ስላለው መለያየትና ግጭት ያሳያሉ፤ ማለትም *ከእርስ በርሳችን መነካከስና መበላላት* ጋር የተያያዙ ናቸው (ቁ. 15)።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ወንድምን ለመቃወም ወይም ከእርሱ ለመለየት ሁለት በቂ ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ያ ወንድም ንስሐ ባለ መግባት በኃጢአት ውስጥ ከተመላለሰ ሲሆን (1ቆሮ. 5፥11)፥ ሁለተኛው ደግሞ በሥጋ የተገለጠው ኢየሱስ እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ሲክድ ነው (1ዮሐ. 4፥2)። ከእነዚህ ከሁለቱ ምክንያቶች ውጪ የትኛውንም ወንድም ብንቃወም ጳውሎስ በዚህ ክፍል ከጠቀሳቸው ኃጢአቶች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ መፈጸማችን ይሆናል።

. . . *እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች የሚያደርጉ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም*። እነዚህን ኃጢአቶች ሁልጊዜ የሚያደርጉ፥ ንስሐም የማይገቡ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገቡም። አልፎ አልፎ ኃጢአትን እናደርጋለን፤ ወዲያው ንስሐ ገብተን ይቅርታውን ስንጠይቅ እግዚአብሔር ከኃጢአታችን ያነጻናል (1ዮሐ. 1፥9)። ነገር ግን እያወቀ ኃጢአትን የሚያደርግ ንስሐም የማይገባ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም፤ አይድንምም።

22–23 *በመንፈስ የሚኖሩ የመንፈስ ፍሬ* በሕይወታቸው ይታያል። በክርስቶስ በሚኖሩ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ፍሬ ይፈራል (ዮሐ. 15፥4–5)። በእነዚህ ዋነኛ ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ እነዚህ ፍሬዎች ምን እንደ ሆኑ ይነግረናል።

በመጀመሪያ የመንፈስ ፍሬ ከመንፈስ ቅዱስ *ስጦታዎች* የተለዩ መሆናቸውን ልብ እንበል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በተለያዩ ጊዜያት ለክርስቲያኖች የሚሰጡ ናቸው (1ቆሮ. 12፥7–11 ይመለከቷል)። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ግን በማናቸውም ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሁልጊዜ ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው። በቤተክርስቲያንም ሆነ በግል ሕይወታችን ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይልቅ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አስፈላጊና ጠቃሚዎች ናቸው።

ጳውሎስ የጠቀሰው የመጀመሪያው ፍሬ *ፍቅር* ነው፤ ፍቅር ለእግዚአብሔርና ፍቅር ለባልንጀራ (ቁ. 13–14 ማብራሪያው ይመለከቷል)።

ሁለተኛው ፍሬ *ደስታ* ነው፤ መንፈሳዊ ደስታን ያመለክታል። ይህ ደስታ በመከራና በችግር ጊዜ እንኳ የማይጠፋ ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ ወደ እኛ የመጣው ደስታ የደኅንነታችን ደስታ ነው (ዮሐ. 15፥11፤ ፊል. 4፥4)።

ሦስተኛው ፍሬ *ሰላም* ነው፤ በመጀመሪያ ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር ያስፈልጋል። ይህ ሰላም በክርስቶስ በማመናችን አለን (ሮሜ. 5፥1፤ ፊል. 4፥7)። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም በመመሥረታችን በቤተክርስቲያን ውስጥ ካሉ ወንድሞችና እህቶች ጋር ሰላም እንዲኖረን እንጥራለን (ሮሜ 14፥19፤ ኤፌ. 4፥3)።

አራተኛው ፍሬ *ትዕግሥት* ነው፤ ይህም በፈተናና በመከራ ጊዜ ያለ ጽናት ነው። በተጨማሪም ለወንድማችን ያለንን ርኅራኄና መረዳት ያመለክታል። ወንድማችን ባለው ድካምና ኃጢአት በትዕግሥት ልንይዘው ይገባናል (ኤፌ. 4፥2)። ኢየሱስ እኛን በትዕግሥት እንደያዘን እኛም እርስ በርሳችን በትዕግሥት ልንሆን ይገባናል (1ጢሞ. 1፥16)።

የሚቀጥሉት ደግሞ *ደግነት*፥ *በጎነትና ታማኝነት* ናቸው። ደግነት መሐሪና ይቅር ባይ መሆንን ያመለክታል (ማቴ. 18፥21–22)። በጎነት ለሰው ሁሉ መልካም ነገርን ለማድረግ መመኘትና መፈለግ ማለት ነው። ታማኝነት ደግሞ የሚታመን ሰው መሆን ማለት ነው።

በመቀጠልም በቁ. 23 ላይ ስምንተኛው ፍሬ *ገርነት* ተጠቅሷል። ገርነት ውጪያዊ የሆነውን ባሕርያችንን ብቻ ሳይሆን ውስጣዊው መንፈሳችንንም ያጠቃልላል። ውስጣዊ ገርነት ትሑት ከመሆን ጋር የተያያዘ ነው። ከመንፈስ ፍሬዎች በቀላሉ ሊበላሽ የሚችል ጥንቃቄ የሚያሻው ነው። የገርነትና የትሕትና ዋነኛ ጠላት የሆነው ትዕቢት፥ ሰው ሊያሸንፈው የማይችለው ኃጢአት ነው። ብዙውን ጊዜ ትዕቢት እንዳለብን አናስታውስም። ሁልጊዜ ግን ይኖራል። ትዕቢትን አስወግደናል ብለን የምናስብ ከሆነ ይህ ራሱ ትዕቢት እንዳለብን ማረጋገጫው ነው።

ትሑት እንደ ሆንን እናስባለን፤ ነገር ግን አንድ ሰው ሲሰድበን ወዲያው ይስማናል ያሳዝነናልም። ለዚህ ምክንያቱ ትዕቢት ነው። ትዕቢት ባይኖርብን ሌላውን ለመከላከል እርምጃ አንወስድም። ክብራችንን ለመጠበቅ ብለን የምናደርገው ሁሉ ከትዕቢት የሚነሣ ነው። ትሑት ሰው ስለ ራሱ ክብር ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ክብር ብቻ ይጠነቀቃል።[26]

በራሳችን ጥረት ትዕቢትን ከውስጣችን ልናስወግድ አንችልም፤ ይህን ማድረግ የሚቻለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።[27] ትሕትናን መልበስ እንድንችል መጸለይ ይኖርብናል። ልብ ልንል የሚገባን መንፈስ ቅዱስ እኛ ትሑታን ሊያደርገን በትዕቢታችን ላይ አንዳንድ ጥቃት ይሰነዝራል። መንፈስ ቅዱስ እኛን ትሑታን ለማድረግ የሚሠራውን ሥራ ለመቀበል ዝግጁዎች ነን?

የመንፈስ ቅዱስ የመጨረሻው ፍሬ *ራስን መግዛት* ነው። ይህ የቀድሞውን ኃጢአተኛ እኛነታችንን በመንፈስ

---

[26] እኛ ከተዋረድን ክርስቶስም መዋረዱ የማይቀር ነው። ስለዚህ ስለክርስቶስ ብለን፤ በራሳችን ላይ የሚያዋርድ ነገር ማምጣት አይገባም።

[27] የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እኛን ትሑታን ማድረግ ነው። የእኛ ሥራ ራሳችንን ዝቅ በማድረግ ማዋረድ ነው (1ጴጥ. 5፥5–6)።

ቅዱስ ሥር ማስገዛት ማለት ነው፤ *የሥጋ ምኞትን አለመፈጸም ማለት ነው* (ቁ. 16)።

የመንፈስ ፍሬ በሕይወታችን ሙሉ በሙሉ በስሉና ጎምርቶ እንደሚገኝ እንዴት ማወቅ እንችላለን? አንድ ፍሬ መብሰሉን ስንጨምቀው እንደሚታወቅ እንዲሁ የመንፈስ ፍሬ በሕይወታችን መብሰላቸው የሚታወቀው በፈተና ወይም በመከራ ውስጥ ስናልፍ ነው። ሁሉ ነገር ሰላም በሚሆንበት ጊዜ ክርስቲያን መምሰል አያስቸግርም። በሕይወታችን የተለያዩ ችግሮች ሲመጡ ለእነዚህ ችግሮች የምንሰጠው ምላሽ ምን ይመስላል? ፍሬአችን ሲጨመቅ የሚወጣው የትዕቢትና የከፋት መራራ ጭማቂ ነው? ወይም የፍቅር፥ የደስታ፥ የትዕግሥት፥ የበጎነት ጣፋጭ ጭማቂ ነው? ሕይወታችን መከራ ሲገጥመን የዚያን ጊዜ ምንነቱ ይፈተናል።

እነዚህ ዘጠኝ ፍሬዎች የሚገኙት በእኛ ሥራና ጥረት ሳይሆን በውስጣችን በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እንደ ሆነ ልብ ልንል ይገባናል። እነዚህ ፍሬዎች በሕይወታችን ቢታዩ የእግዚአብሔርን ሕግ በሕይወታችን እየፈጸምን ነው፤ ቅዱሳንና ጻድቃን እንሆናለን የትኛውም ሕግ እኛን ሊወነጅለን አይችልም። እነዚህ ሕጎች ከቶዎች ናቸው የሚል ሕግ የለም። *እንደነዚህ ያሉትን* (ዘጠኙን የመንፈስ ፍሬዎች) *የሚቃረን ሕግ የለም* (ቁ. 23)።

24 መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ሙሉ በሙሉ እንዲገለጥ ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን በመስቀል ላይ መሰቀል አለበት። ጳውሎስ በሮሜ መጽሐፉ ባስተማረው መሠረት በኃጢአተኛ ተፈጥሮ ሥር ያለው የቀድሞው እኛነታችን በመስቀል ላይ ሊሆን ይገባዋል (ሮሜ 6÷6)። በእዚህ ስፍራም ጳውሎስ ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን በመስቀል ላይ ሊሆን ይገባዋል ይላል። በአንድ በኩል የቀድሞው እኛነታችን መሞት አለበት። በሌላ በኩል ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን ሙሉ ለሙሉ አይሞትም። ሁልጊዜ ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችንን ልንሰቅለው ይገባናል (ሉቃ. 9÷23)። እንደተሰቀለ ልንጠብቀው ይገባል።[28]

የቀድሞው ተፈጥሮአችን መስቀልን ይወዳልን? በፍጹም አይወድም፤ የሚመች አይደለም፤ ስለዚህ የክርስትና ሕይወት ለመኖር ቀላል አይደለም። በእርግጥም በራስ ጥረት የሚቻል አይደለም።

ነገር ግን እግዚአብሔር «የክርስትናን ሕይወት እንድንኖር» አይጠብቅብንም። እግዚአ ብሔር በየቀኑ *በመንፈስ እንድንኖር* ይናገረናል (ቁ. 16 እና 25)። እያንዳንዱን እርምጃ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ተደግፈን መንዝ ይኖርብናል። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት መምራት የምንችለው *በመንፈስ ብቻ* ነው።

25 *በመንፈስ የምንመራ ከሆንን፥ በመንፈስ እንመራ!* በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ከሆንን እንደዚያው ልንኖር ያስፈልጋል። በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን እንደ እግዚአብሔር ልጆች ልንኖር ይገባናል።

በክርስቶስ እንዳመንን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን እንባላለን፤ ይህ እውነት ነው። እንደምናውቀው የየእለቱ ኑሮአችን ሁልጊዜ እንደ ጻድቃን አይደለም። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እነዚህን እውነታዎች ሊገልጽ የሚችል ምሳሌ እንመልከት፤ ኛ በዛፍ ላይ እንዳሉ እየበሰሉ እንደሚሄዱ ፍሬዎች ነን። በመጀመሪያ ፍሬው አረንጓዴና ጠንካራ ነው። ቀስ በቀስ በፀሐይና ዝናብ አማካይነት ፍሬው ይጎመራል። ፍሬው እንደሚበስል እኛም በመጨረሻ እንዲሁ እንደምንሆን እግዚአብሔር ያውቃል። ስለዚህ አሁን እንኳ ሙሉ በሙሉ እንደበሰሉ ፍሬዎች ይመለከተናል። ራሳችንን ስንመለከተው ግን ሙሉ በሙሉ ያልበሰልን ጥሬ ፍሬዎች እንደ ሆንን እናስባለን።

የክርስትና ሕይወታችንን የጀመርነው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። የምንበስለውም ቅዱስና ፍጹም የምንሆነው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ክርስቶስ ፍጹም እንደ ሆነ እኛም ወደ ፍጹምነት ደርሰን ወደ መንግሥቱ በደስታ የምንገባው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ወገኖች ስለ ጸጋው ክብር እግዚአብሔርን ማመስገን አንተው! (ኤፌ. 1÷6)።

26 ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ከመንፈስ ቅዱስ ስላልሆነ ባሕርይ ሦስት ምሳሌዎች ይሰጣል። የመጀመሪያው፥ ሌላውን ለጥል ማነሣሣትና ሌሎችን ወደታች ማድረግ ሲሆን፥ ሁለተኛው በሌሎች ዓይን የተሻለ መስሎ የመታየት *የትምክህት* ፍላጎት ነው። ሦስተኛው፥ ሌሎች ከእኛ የተሻሉ ወይም እድለኞች እንደ ሆኑ በመቁጠር *መቀናናት* ነው። በትምክህትና በመቀናናት ምክንያት ሌሎችን ለጥል ለማነሣሣት እንፈልጋለን። ይህን በማድረግ ራሳችንን ከፍ ለማድረግ እንመኛለን።

ነገር ግን ኢየሱስ ይህን ስናደርግ ተቃራኒው እንደሚገጥመን አስተምሯል። *«ራሱን ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳል፤ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ከፍ ይላል»* (ማቴ. 23÷12)። ስለዚህ ወንድሞቻችንና እህታችንን ከፍ እናድርግ ራሳችንንም ዝቅ እናድርግ።

ምዕራፍ 6

ለሰው ሁሉ መልካምን (በጎን) ማድረግ (6÷1–10)

1 *ወንድሞች ሆይ! ሰው ማናቸውንም ስህተት አድርጎ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንዲህ ዓይነቱን ሰው በገርነት አቅኑት፡፡ መንፈሳዊያን የሆኑ እነርሱ በመንፈስ የሚኖሩ* ናቸው (ገላ. 5÷16፥25)። መንፈሳዊያን የሆንን በቤተክርስቲያን ላሉት ወገኖች ኀላፊነት አለብን። በኃጢአት በወደቁ ጊዜ ከመገሠጻችን በፊት በገርነት ልንመልሳቸው ይገባናል። ሌላው በመውደቁ በልባችን ሐሴት ማድረግ ሳይሆን እኛ ራሳችን ደካሞች እንደ ሆንን አውቀን በገርነት ልንመልሰው ያስፈልጋል። ምክንያቱም ዛሬ በወንድማችን የመጣው ፈተና ነገ እኛንም ሊገጥመን ይችላል። አንድ ወንድማችን በኃጢአት ሲወድቅ ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳቆመን ልናስተውል ይገባናል (1ቆሮ. 10÷12 ይመለከቷል)። «በኃጢአት ብወድቅ እንዴት ባለ መንገድ ሰዎች እንዲጠጉኝ እፈልጋለሁ?» ብለን እናስብ፤ በዚህ ሁኔታ ወንድማችንን እናገለግላለው።

2 *እርስ በርሳችሁ ከእናንተ እያንዳንዱ የሌላውን ሸክም ይሸከም*። ሸክም የተባለው ምንድን ነው? የአንዳንድ ሸክም ምክንያት የአንድ ሰው ሥራና ኀላፊነት መብዛት ነው። ምናልባት የወንድማችን ሥራ ከባድ ከመሆኑ የተነሣ ይደክማል። ስለዚህ የሥራውን ሸክም ማገዝ ይኖርብናል።

ሌሎች ሸክሞች እንደ ጭንቀት፥ ተስፋ መቁረጥ፥ ሐዘን፥ ድካም፥ ሕመም የመሳሰሉት ይሆናሉ። እነዚህ የአካል ወይም የመንፈስ ሸክሞች ሊሆኑ ይችላሉ።

ሦስተኛው የሸክም ዓይነት ኃጢአት ነው። ለወንድማችን ሸክሙ ኃጢአት ነው። ምናልባት ወንድማችን ቁጡነት ያስቸግረው ይሆናል። ቁጣውን መቆጣጠር አለመቻሉ ለእርሱ ሸክም ሆኖበታል። ይህን ሸክሙን እንዲሸከም እንዴት ልናግዘው እንችላለን? ይቅርታ በማድረግ፥ በመምከር፥ በገርነት በመመለስና በፍቅር በመቀበል ልንረዳው እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ ወንድማችን «መጥፎ ፀባዩንና ልማዱን ከተወ በኋላ ብቻ እቀበለዋለሁ» እንላለን። ክርስቶስ እኛን እንደዚህ አላለንም። እርሱ ከነድካማችንና ኃጢአታችን ተቀበለን፤ በመስቀል ላይም ሸክማችንን ተቀበለ።

ወንድማችን ኃጢአትን ሲያደርግ ኃፍረትና ውርደት በእርሱ ላይ ይሆናሉ። አንዳንዴም በእርሱ ኃጢአት ምክንያት በቤተ ክርስቲያንና በእኛ ላይ ኃፍረትና ውርደት ይመጣል። በዚህ መንገድ ወንድማችን እኛን ይበድላል። በኃጢአቱም ምክንያት ችግር ይደርስብናል። *ታዲያ* ይህንን ሁሉ ልንሸከም ይገባናል? አዎን ልንሸከም ይገባናል። ይህ ጥቅስ የሚናገረው ይህንኑ ነው። ሸክሙን መሸከም ብቻ ሳይሆን የሚመጣውን ችግር አብሮ መቀበል ነው። ክርስቶስ ለእኛ ያደረገው ይህን ነው። ስለዚህ በወንድማችን ኃጢአት ምክንያት የሚመጣውን መከራ እንቀበል ያስፈልጋል፤ ይህን ካደረግን የክርስቶስን ሕግ ፈጸምን ማለት ነው። ኢየሱስም *«እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ»* ብሏል (ዮሐ. 15÷12)።

[28] በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ አማኞች ሁለት ዓይነት መስቀል ተጠቅሶ ይገኛል። በሮሜ 6÷6 እና በገላ. 2÷20 አሮጌው ሰውነታችን ከክርስቶስ ጋር በእምነት እንደተሰቀለ የሚናገረው አንደኛው ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ በማር. 8÷34 እና ሮሜ 8÷13 እንዲሁም እዚሁ ገላትያ 5÷24 ላይ የተጠቀሰው በየዕለቱ ተሸክመን የምንዞረው መስቀል ነው።

3 ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሲወዳደር *ባዶ* ነው (መዝ. 8፥4)። ስለዚህ ምንም ሳንሆን አንድ ነገር እንደ ሆንን አናስብ። መልካሞች፣ የምንጠቅምና አስፈላጊ እንደ ሆንን አናስብ በትዕቢት ራሳችንን እናታልላለንና። ራሳችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር አናወዳድር። እንዲህ ካደረግን ከሌሎች ሰዎች የተሻልን ሆነን ለመገኘት ሁልጊዜ እንጥራለን። ነገር ግን ራሳችንን ከኢየሱስ ሕይወት ጋር ካነጻጸርን የበለጠ ትሑታን እንሆናለን።
4 ሁላችንም ለራሳችን *ሥራ* ተጠያቂዎች ነን። ባሕርያችን እንዴት እንደ ሆነ ልንመረምር ይገባናል። ፍሬ የዛፉን ምንነት እንደሚያሳይ የእኛም ሥራና ባሕርይ የእምነታችንን ሁኔታ ይገልጻል። ጳውሎስ እንዳለው አንድ ሰው ሥራው በጎ ከሆነ *ለራሱ የሚመካበትን ነገር ያገኛል*። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ በሥራችን እንድንታበይ አልተናገረም፤ ምክንያቱም መልካም ሥራችን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ እንደ ሆነ እናውቃለን (1ቆሮ. 15፥10)። ወንድሞቻችን ከእኛ ይልቅ ደካማ ወይም ኃጢአተኛ ስለሆኑ *መመካት ሳይሆን* በእግዚአብሔር ፊት ሥራችን ደስ የሚያሰኝ በመሆኑ *ልንመካ* እንችላለን (2ቆሮ. 10፥17–18)።
ራሳችንን ከክርስቶስ ጋር ስናነጻጽር ምን ያህል ደካሞችና ኃጢአተኞች እንደሆንንና ሌሎችን መናቅ እንደማንችል እንረዳለን። ከክርስቶስ ጋር ብቻ ራሳችንን እናነፃፅር።
5 ጳውሎስ በቁ. 2 ላይ *እርስ በርስ በመተጋገዝ አንዱ የሌላውን ሸክም ይሸከም* ይላል። በዚህ ቦታ *አንዳንዱ የራሱን ሸክም መሸከም አለበት* ይላል። ጳውሎስ የሚናገረው ሁለት የሚቃረኑ ሐሳቦችን ነውን? አይደለም። በቁ. 2 እና 5 ላይ የተጠቀሰው ሸክም የሚለው ቃል የተለያየ ትርጉም አለው። ከቁ. 5 ላይ የተጠቀሰው *ሸክም* የሚለው ቃል ኀላፊነትን የተግባር ግዴታን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የሰጠውን ኀላፊነት መወጣት አለብን። በዚህ ምድር ለሠራነው ሥራ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂዎች ነን (ሮሜ 14፥12፤ 2ቆሮ. 5፥10)።
6 የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩ ሰባኪዎች፣ ወንጌላውያን ወይም መጋቢዎች በኑሮአቸው ድሆች ሊሆኑ ይችላሉ። ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንዲያገኙ በትምህርታቸው የተባረከን እነርሱን ለመርዳት የተዘጋጀንና የምንጓጓ ልንሆን ይገባናል (ሮሜ 15፥26–27፤ 2ቆሮ. 9፥11–12 ይመለከቷል)።
7 *ሰው የሚያጭደው የዘራውን ነው*። ይህ ሕግ በቁሳዊው ዓለም ሆነ በመንፈሳዊው ዓለም የሚሠራ ነው፤ ለሁሉም ሰው የሚሠራ ነው። እግዚአብሔርን ማታለል አንችልም የዘራነውን ያውቃልና።
ለሌሎች እንደ ሰጠን መጠን ከእግዚአብሔር ደግሞ እንቀበላለን። *ለጋሥ ሁን ትበለጽጋለህ፤ ሌሎችን እርዳ አንተም እርዳታ ታገኛለህ* (ምሳሌ 11፥25፤ 2ቆሮ. 9፥6)።
8 *ሥጋውን ለማስደሰት የሚዘራ* ኃጢአተኛ ተፈጥሮውን የሚያገለግል የኃጢአተኛ ተፈጥሮን ዋጋ ያገኛል። እርሱም *ጥፋት* (ሞት) ነው። *መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ* የመንፈስ ስጦታ የሆነውን የዘላለም ሕይወትን ያገኛል (ሮሜ 6፥21–23፤ 1ዮሐ. 2፥17 ይመለከቷል)።
አንድ ሰው መንፈሳዊ ፍሬን ለመሰብሰብ መንፈሳዊ ሥራዎችን መሥራት አለበት፤ የኃጢአተኛ ተፈጥሮ ፍሬን ለማግኘት የሥጋን ሥራ መሥራት ይችላል (ገላ. 5፥19–21)። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ጻድቅ ነው፤ እርሱ እንደ ሥራችን ይከፍለናል።
9 ብዙ ክርስቲያኖች የክርስትና ሕይወታቸውን በትጋትና በብርታት ይጀምራሉ። ነገር ግን ቀስ በቀስ *ይደክማሉ*። እንዲያውም አንዳንዶች መሮጡን ያቆማሉ (ገላ. 5፥7)።
በመካከላችን የደከሙ አሉን? *ለደካማ ኃይልን የሚሰጠውን ጌታ* ይጥሩ (ኢሳ. 40፥29–31)። ደክመው ተስፋ እንዳይቆርጡ ዓይኖቻቸውን በኢየሱስ ላይ ያድርጉ (ዕብ. 12፥3)። በሰማይ የተጠበቀላቸውን ሽልማት ያስታውሱ (1ጴጥ. 1፥3–4)። ካልደከሙ በዚህ ምድርና በሚመጣው ዓለም በዘላለማዊው ሕይወት የጽድቅን ፍሬ ይሰበስባሉ (2ጢሞ. 4፥7–8)።
10 በቁ. 9 ጳውሎስ *መልካም ሥራን ከመሥራት አንሰንፍ* ይላል። «መልካም ሥራን መሥራት» ማለት ለሁሉ ሰው መልካምን ማድረግ ነው፤ በሌላ አገላለጽ ባልንጀራችንን እንደ ራሳችን መውደድ ማለት ነው (ገላ. 5፥14)።
ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ ለሰው ሁሉ መልካም ሥራን መሥራት አለብን፣ ብዙ ያልተጠቀምንባቸው አጋጣሚዎች አልፈውናል። እግዚአብሔር ይቅር ይበለን! ለሁሉ መልካምን ማድረግ አለብን፤ ይልቁንም ለሚያምኑ ቤተ ሰዎች። እነርሱ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች ናቸውና (ዮሐ. 13፥34–35)።

መገረዝ ሳይሆን አዲስ ፍጥረት መሆን (6፥11–18)

11 ከዚህ በታች ያለውን ጳውሎስ በገዛ እጁ የጻፈው ነው 1ቆሮ. 16፥21፤ 2ተሰ. 3፥17።
12 ከኢየሩሳሌም የመጡት ሐሰተኛ አስተማሪዎች (ገላ. 2፥4፡12)፤ በገላትያ በሚኖሩ አይሁዳዊያን ዘንድ *ውጫዊ በሆነ ሥጋዊ ነገር* ትምክህት እንዲኖር የሚሞክሩ ናቸው። ስደት እንዳይደርስባቸው ስለሚፈልጉ በእነዚህ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ይሞክራሉ። በዚህ ምክንያት እነዚህ አስተማሪዎች የገላትያ ሰዎች መዳን ከፈለጉ መገረዝ እንዳለባቸው ያስተምራሉ። አይሁዳውያን በመገረዝና ሕግጋትን በመፈጸም ብቻ ሰው እንደሚድን ያምናሉ። *የክርስቶስ መስቀል* ስብከት ግን ሰው የሚድነው የተሰቀለውን ኢየሱስን በማመን ብቻ እንደ ሆነ ይናገራል። ስለዚህ መስቀሉ አይሁድ እምነት ተከታዮችን ያስቆጣቸዋል፤ ይህንንም የሚሰብኩትንም ያሳድዳሉ (ገላ. 5፥11)።
13 *የተገረዙት* ሐሰተኛ የአይሁድ አስተማሪዎች ራሳቸው የአይሁድን ሕግ አይፈጽሙም። የገላትያ ሰዎችን እንዲገረዙ የሚነግሯቸው ለሕጉ ታዘው ሳይሆን የገላትያ ሰዎችን አይሁድ አደረግን ብለው ለመኩራራት ነው። እነዚህ አስመሳዮች የገላትያ ሰዎችን እንዲገረዙ በማድረግ ከእውነተኛ በጸጋ ከሚገኘው የድኅነት መንገድ እንዳያገኙ እየከለከሏቸው ነው (ማቴ. 23፥13፤ ሉቃ. 11፥46 ይመለከቷል)።
14 አይሁድ በመገረዝና ሕግን በመፈጸም ይመካሉ። ጳውሎስ ግን በክርስቶስ መስቀል ይኸውም በክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሥራ ይመካል።
በሮማውያን አመለካከት መስቀል ኀፍረትን፣ ውርደትን፣ ሽንፈትን፣ ድካምንና ሞትን የሚያመለክት ነው። ሆኖም በዚህ መስቀል ጳውሎስ ይመካል። ምክንያቱም ሰዎች ደኅንነት የሚያገኙት ክርስቶስ በዚህ መስቀል ላይ በመሞቱ ብቻ ስለ ሆነ ነው። ለጳውሎስ ዓለም ተሰቅሏል፤ ማለትም ዓለማዊ ሐሳቦቹና ምኞቶቹ ሞተዋል። ጳውሎስ በዓለም አይመካም። እምነቱን ያደረገው በመስቀሉ ላይ ብቻ ነው (1ቆሮ. 1፥18፤ ፊል. 3፥7–8)። ለጳውሎስ ዓለም ብቻ ሳትሆን እርሱ ራሱም ለዓለም ተሰቅሏል። ይህን ሲል አሮጌው ማንነቱ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል ማለቱ ነው (ገላ. 2፥20)።
15 በገላ. 5፥6 ጳውሎስ ደኅንነት የሚገኝበት ብቸኛ መንገድ እምነት እንደ ሆነ ተናግሯል (ገላ. 5፥6 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። በዚህ ቦታ የሚናገረው ይህንኑ ሐሳብ ነው። በክርስቶስ በማመን *አዲስ ፍጥረት*፣ አዲስ መንፈሳዊ ሰውነትን፣ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንን አግኝተናል (2ቆሮ. 5፥17 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። *ዳግመኛ* ተወልደናል (ዮሐ. 3፥5)። ደኅንነት ማለት *አዲስ ፍጥረት* መሆን ነው፤ ዋጋ ያለውም ይህ ነው።
16 *ይህን መመሪያ የሚከተሉ* ሁሉ የዚህን መልእክት ትምህርት የሚታዘዙ ናቸው። ጳውሎስ የጻፈው እውነተኛውን የክርስቶስን ወንጌል ነው። በዚህ *መመሪያ* የሚሄዱ እውነተኛ *የእግዚአብሔር ወገኖች የሆኑ እስራኤሎች*፣[29] እውነተኛ

---

[29] እስራኤል የአይሁድ ሕዝብ አገር ስም ነው። አሁን ግን በክርስቶስ የሚያምኑ «እውነተኛ እስራኤል» ተብለው ይጠራሉ፤ ምክንያቱም እውነተኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ እነርሱ ናቸውና።

የእግዚአብሔር ቤተሰብ ናቸው። እውነተኛ እስራኤላዊያን ከአብርሃም በሥጋ የተወለዱ ሳይሆኑ እምነታቸውን በክርስቶስ ያደረጉ ናቸው።

17 ጳውሎስ *ከእንግዲህ ወዲህ ማንም አያስቸግረኝ* ይላል። ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ሲል በተቀበለው ግርፋት በሰውነቱ ላይ ምልክት ስለ ወጣ *የክርስቶስ ምልክት* በሰውነቴ ላይ አለ ይላል (2ቆሮ. 11፥23–28)። ጳውሎስን የሚያስቸግረው ሁሉ ክርስቶስን ያስቸግራል። ስለዚህ የገላትያ ክርስቲያኖች ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በመከተል ጳውሎስን ማስቸገር ትተው እውነተኛውን ወንጌል ይከተሉ።

18 ምንም እንኳ ጳውሎስ የገላትያ ሰዎችን በዚህ መልእክቱ ቢገሥጻቸውም በመጨረሻው ቁጥር ላይ *ወንድሞቼ* ብሎ ይጠራቸዋል። ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በመከተላቸው እንደ ጠፉ በጎች ተቆጥረዋል። ሆኖም ጳውሎስ አሁንም ይወዳቸዋል። ከፍተኛ የሆነውን በረከት *የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ* እንዲቀበሉ ይጸልይላቸዋል።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች

መግቢያ

ጳውሎስ በሮም እስር ቤት በነበረበት ዘመን ማለትም፣ ከ60–61 ዓ.ም. ገደማ ይህን መልእክት ለኤፌሶን ሰዎች ጻፈላቸው። ጳውሎስ የፊልጵስዩስን፥ የቆላስይስንና የፊልሞናን መልዕክቶች የጻፈውም በዚያው በእስር ቤት ነበር።

በአዲስ ኪዳን ዘመን፥ ኤፌሶን በመካከለኛው ምሥራቅ በጣም ታዋቂ ከተማና እንዲያውም በሮም መንግስት በኢሲያ ለነበሩት ግዛቶች (የዛሬይቱ ቱርክ ምዕራባዊ ክፍል) ዋና ከተማ ነበረች። ይህችው ከተማ ታዋቂ የንግድ ማዕከል ስለሆነች ብዙ ሰዎች ወደ እርሷ ይሄዱ ነበር (የሐዋ 18፥19)።

ጳውሎስም ከ53–55 ዓ.ም. በኤፌሶን የቆየ ሲሆን፤ በዚያን ዘመን ንግግር በሚደረግበት አንድ አዳራሽ በየቀኑ ያስተምር ነበር። እርሱን ለማድመጥ ከሚሄዱ ሰዎች ጥቂቶቹ በክርስቶስ አመኑ፤ የኤፌሶን ቤተክርስቲያንም ተቋቋመች። የከተማይቱ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ለንግድ ሥራ መጥተው የጳውሎስን ትምህርት የሰሙትም አመኑ። እነዚህ አማኞችም ወንጌልን ወደየራሳቸው ከተማ ይዘው ተመለሱ። በዚህ ሁኔታ የክርስቶስ ወንጌል በኤፌሶን ዙሪያ እስከ ሩቅ ስፍራዎች ተዳርሶ ነበር (የሐዋ 19 ፥ 8–10)።

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚያምኑት፥ ይህ መልእክት ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ብቻ የጻፈው አይደለም፤ ነገር ግን በኤፌሶን ዙሪያ ለነበሩ አብያተክርስቲያናት ጥምር ነው። እነዚህ አብያተክርስቲያናትም የተመሠረቱት፥ ጳውሎስ በኤፌሶን ለሁለት ዓመታት በማስተማሩ ነበር። ጳውሎስ በአዲስ ኪዳን ካቀረባቸው መልእክቶቹ አብዛኛዎቹ ግላዊ የሆነ ጠባይ ያላቸውና ለእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የተጻፉ ነበሩ። ይህኛው መልእክት ግን ለየት ያለነው። ጳውሎስ በዚህኛው መልእክቱ የጻፈው ሰፊና አጠቃላይ ትምህርቶችን የያዘ ሲሆን፤ የኤፌሶንን[1] ሰዎች በተለየ ሁኔታ የሚመለከት ምንም ነገር አልጻፈም። ብዙ ሊቃውንት «ይህ መልእክት ተዘዋዋሪ ደብዳቤ በመሆን ከአንዱ ቤተክርስቲያን ወደ ሌላው ቤተክርስቲያን የሚተላለፍ ነው» በማለት ያምናሉ።

ስለ ጳውሎስ ሕይወት በተጨማሪ ለመረዳት የሮሜን መልእክትና መግቢያውን ይመለከቷል።

---

[1] በጥንት ጽሑፎች በቁጥር አንድ ላይ «በኤፌሶን» የሚል ቃል አልተጻፈም፤ ይህም የሚያመለክተው ይህ መልእክት በኤፌሶን በነበረው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ሊነበብ እንደሚገባው የታቀደ መሆኑን ነው።

አስተዋጽኦ

ሀ. አማኝ በክርስቶስ ውስጥ ያለው ድርሻ (1፥1-3፥21)።
1. በክርስቶስ የሚገኙ መንፈሳዊ በረከቶች (1፥1-14)።
2. የምልጃ ጸሎት (1፥15-23)።
3. በእምነትና በጸጋ የሚገኝ ደኅንነት (2፥1-10)።
4. አይሁዶችና አረማውያን በክርስቶስ መታረቃቸው (2፥11-22)።
5. የምስጢሩ መገለጥ (3፥1-13)።
6. የጳውሎስ ሁለተኛ ጸሎት (3፥14-21)።

ለ. የአማኝ ጠባይ በዓለም ውስጥ (4፥1-6፥24)።
1. የቤተክርስቲያን አንድነት (4፥1-16)።
2. የተለወጠ ሕይወት (4፥17-32)።
3. እንደ ብርሃን ልጆች መኖር (5፥1-21)
4. የክርስቲያን ጋብቻ (5፥22-33)።
5. የክርስቲያን ቤተሰብ (6፥1-4)።
6. ክርስቲያን ተቀጥሮ ሲሠራ (6፥5-9)።
7. «የክርስቲያን ጦርነት» (6፥10-24)።

ምዕራፍ 1

በክርስቶስ የሚገኙ መንፈሳዊ በረከቶች (1፥1–14)

1 ጳውሎስ ይህን መልእክት ሲጽፍ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ እንደመሆኑ መጠን፥ በክርስቶስ ሙሉ ሥልጣን ነው። ጳውሎስ ሐዋርያ ለመሆን የበቃው በሰው ፈቃድ ሳይሆን፥ በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ይህን መልእክት በምናጠናበት ወቅት ራሱ እግዚአብሔር በሐዋርያው[2] በኩል እንደሚያናግረን ማስተዋል ይኖርብናል።

ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በኤፌሶን ለሚኖሩ ቅዱሳን ሲሆን፤ ቅዱሳን የተባሉበትም ምክንያት በክርስቶስ ኢየሱስ የነበራቸው እምነት ብርቱ በመሆኑ ነው። በአዲስ ኪዳን ዘመን በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ ብዙውን ጊዜ "ቅዱሳን" ተብለው ይጠራሉ። ማንኛውም ሰው በክርስቶስ አምኖ ይቅርታን ከተቀበለና ከኃጢአቱም ንጹሕ ከሆነ፥ "ቅዱስ" ሊባል ይችላል (ሮሜ 1፥7፤ ፊል. 1፥1)።

ይህ መልእክት የተጻፈው ለኤፌሶንና በዙሪያዋ ለነበሩ አብያተክርስቲያናት ብቻ ሳይሆን፥ ዛሬም ለራሳችን ቤተ ክርስቲያን ጥምር መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል። ይህ ሕያው መልእክት ነው፤ አስፈላጊነቱም በጳውሎስ ዘመን ለነበሩ አማኞች ብቻ ሳይሆን፥ ዛሬም ለምንገኝ አማኞች ጥምር ነው። መልዕክቱን ስናነብ እግዚአብሔር የሚናገረንን እንስማ።

2 ይህን መልእክት የሚያነቡ ሁሉ የእግዚአብሔርን ጸጋና ሰላም በማግኘት የሚደሰቱ እንዲሆኑ ጳውሎስ ይጸልያል።

ፀጋ የእግዚአብሔር ምሕረትና ፍቅር ነው። ሰው የእግዚአብሔርን ፀጋ ለመቀበል የሚገባው ባይሆንም እግዚአብሔር ግን ለሰዎች በነፃ ይሰጣቸዋል። ሰው ይሄ ፀጋ እንኳንስ በነፃ ሊሰጠው ይቅርና መልካም ሥራ በመሥራት እንደ ዋጋ ሊቀበለው አይችልም። እግዚአብሔር በወንዶችና በሴቶች ላይ ፀጋውን የሚያፈስው ስለሚወዳቸው ብቻ ነው።

ይህን የእግዚአብሔር ጸጋ በመቀበል ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋርና እንዲሁም እርስበርሳቸው በሰላም መኖር ይችላሉ፤ ስለሆነም ይህ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈላቸው መልእክት «በጸጋ ሰላምን ማግኘት» የሚል ስያሜ ሊሰጠው ይችላል፤ ምክንያቱም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የመልእክቱ ዋና ቁም ነገር ይህ ስለሆነ ነው።

3 እግዚአብሔር መንፈሳዊ በረከቶችን ሁሉ በመስጠት አማኞችን ባርኮአል። ጳውሎስም ቢሆን «እግዚአብሔር ወደፊት ይባርከናል» አላለም፤ ነገር ግን *«እግዚአብሔር አሁኑኑ ባርኮናል»* ነው የሚለው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ባርኮናል፤ ማንኛውም መንፈሳዊ በረከት ወደ እኛ ሊመጣ የሚችለው በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው።

በክርስቶስ ስለሆንን ብቻ የዚህ ሁሉ በረከት ተካፋዮች መሆን እንችላለን፤ በክርስቶስ ካልሆንን ግን እነዚህን በረከቶች መቀበል አንችልም። «በክርስቶስ መሆን» ማለት ክርስቶስን «እንደ ጌታና እንደ አዳኝ» አድርጎ መቀበልና፤ በእምነት ከእርሱ ጋር ተቆራኝተን ሕይወታችንን በሥልጣኑ ሥር ማስገዛት ማለት ነው።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር እነዚህን በረከቶች ሁሉ እኛ ልናገኛቸው እንደምንችል አድርጎ ቢያዘጋጅልንም፥ እኛ ወደ እግዚአብሔር በእምነት በመጠጋት ልንቀበላቸው ይገባናል። በሌላ አነጋገር፥ የተሰጠን በእምነት የእኛ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን፤ እምነትን የማንለማመድ ከሆንን ግን ምንም ልንቀበል አንችልም።

እነዚህ «መንፈሳዊ በረከቶች» ብለን የምንጠራቸው የትኞቹ ናቸው? የመጀመሪያው በረከት እግዚአብሔር *መረጠን* (ቁ. 4)፥ ልጆቹ እንድንሆንም ወሰነን የሚለው ነው (ቁ. 5)። ሁተኛው በረከት እግዚአብሔር ጸጋውን በነፃ ሰጠን (ቁ. 6)፥ በዚህም ጸጋ አማካይነት በልጁ ደም ተዋጅተን የኃጢአታችንን ይቅርታ አገኘን (ቁ. 7)። ሦስተኛው በረከት እግዚአብሔር የፈቃዱን ምስጢር እንድናውቅ አደረገ (ቁ. 9)፥ አራተኛም የደኅንነታችን መልካም ዜና የሆነውን የእውነት ቃል ሰማን (ቁ. 13)፤ አምስተኛ በመንፈስ ቅዱስ ታተምን (ቁ. 13)። ይህም መንፈስ እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን በሙሉ እስኪዋጅ ድረስ የርስታችን መያዣ ነው (ቁ. 14)። እንግዲህ በክርስቶስ ባለን እምነት የምንቀበላቸው በሰማይ ያሉን መንፈሳዊ በረከቶች እነዚህ ናቸው።

4 እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠን። እስቲ ስለዚህ እናስብ፤ በዚያን ጊዜ ምድር አልነበረም፤ እግዚአብሔር ብቻ ነበር። በዚያን ጊዜ *እግዚአብሔር በጎ ፈቃዱ ሆኖ* (ቁ. 5) ዘላለማዊ እቅድ አወጣ፤ ከዚህም እቅድ ከፊሉ እኛን በክርስቶስ የምናምነውን መምረጥ ነበር። በቁ. 5 መሠረት እግዚአብሔር ልጆቹ እንድንሆን አስቀድሞ ወሰነን፤ «መመረጥ» የሚለውም ሐሳብ ይህንኑ ያመለክታል። ይህም መጣም አስፈላጊ የሆነ እውነት ነው። በመጀመሪያ ምንም ነገር ከመሆኑ በፊት እግዚአብሔር መረጠን። አንዳንድ ጊዜ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን የመረጥነው እኛ እንደሆን አድርገን እናስባለን፤ ነገር ግን እውነቱ ይህ አይደለም። በመጀመሪያ የመረጠን እግዚአብሔር ነው። በዚህ ምክንያት ብቻ እኛም ፈታችንን መልሰን እርሱን መምረጥ እንችላለን። እግዚአብሔር እኛን የመረጠን በፍቅሩ ስለሆነ ልንኮራበት የምንችል ምንም ምክንያት አይኖረንም፤ ለመመረጥ የሚያበቃን ምንም ነገር አላደረግንም። እግዚአብሔር የመረጠን ከመወለዳችን በፊት አስቀድሞ ነው። በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ለመገኘት እኛ ያደረግነው ምንም ነገር የለም። ይህ ሊሆን የቻለው የእግዚአብሔር ደስታና በጎ ፈቃድ ስለሆነ ብቻ ነው። እንደ (ቁ. 5) ደግሞ መመረጥ ብቻ ሳይሆን ልጆቹ እንድንሆንም አስቀድሞ ወሰነን። ከዚህም የተነሣ እኛ ለእግዚአብሔር «ባለ ዕዳዎች» ነን፤ በራሳችን ድርጊት መኩራትን ትተን እግዚአብሔር ላሳየን ትልቅ ጸጋ በትሕትና ልናመሰግነው ይገባናል።

አንዳንድ ሃይማኖቶች «ሕፃን ሲወለድ አንድ መንፈስ መጥቶ ሕፃኑ የወደፊት ሕይወቱ ምን መሆን እንዳለበት ይወስንለታል» በማለት ያምናሉ። ነገር ግን ይህ ፈጽሞ እውነት አይደለም፤ ዓለም ሳይፈጠር በፊት እውነተኛው አንድ አምላክ የእያንዳንዱን ሰው የወደፊት ሕይወት ወስኖለታል።

ብዙ ክርስቲያኖች ይህን ጥቅስ በመውሰድ «እግዚአብሔር አንዳንዶችን ልጆቹ አድርጎ ይመርጣል፤ ሌሎችን ግን ሳይመርጥ ይተዋቸዋል» ብለው ያስባሉ። እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለምን እንደሚመርጥና ሌሎችን ደግሞ ለምን እንደማይመርጥ ምክንያቱን ለይቶ ማወቁ ስለሚከብድ፤ ብዙ ሰዎች አሳቡን ለመቀበልና ለመረዳት ያስቸግራቸዋል። በ1ጢሞ. 2፥4 ላይ ጳውሎስ "ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው" በማለት ጽፎአል። ይሁን እንጂ፥ ሰዎች ሁሉ ወዲያውኑ ሊድኑ እንደማይችሉ የሚያስረዱ ሌሎች ብዙ ጥቅሶች ይገኛሉ። እዚህ ላይ በጣም ልናስታውሰው የሚገባን ነገር በክርስቶስ የሚያምን እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር የተመረጠ መሆኑን ነው (ሮሜ 9፥14–21 እና ማብራሪያውን እንዲሁም ከአስተምህሮ ዳሰሳው፥ ደኅንነት የእግዚአብሄር ምርጫ ወይስ የሰው? የሚለውን ይመለከቷል)።

«እግዚአብሔር ለምን መረጠን?» የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ «ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለብን ሆነን በፊቱ እንድንገኝ መረጠን» የሚል ነው። «በእግዚአብሔር የተመረጥን ስለሆነ አሁን የፈለግነውን ነገር ማድረግ እንችላለን» ብለን ግን ቅንጣት ታህል ማሰብ አይገባንም። እግዚአብሔር የጠራን ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለብን ሆነን በፊቱ እንድንገኝ ስለሆነ፥ በሕይወታችን ምንም ዐይነት ኃጢአት ወይም ርኩሰት ሊኖር አይገባም (1ጴጥ. 1፥15–16)።

5 እግዚአብሔር ልጆቹ[3] አድርጎ እንደሚወስደን አስቀድሞ ወሰነን፤ በክርስቶስ የሚያምን ወንድም ሆነ ሴት በመንፈሳዊ ረገድ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖአል።

---

2 በእርግጥ ይህ አጠቃላይ አሳብ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ስናጠና የምንጠቀምበት ዘዴ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ስለሆነም እርሱ በእያንዳንዱ ጥቅስ ይናገረናል።

3 እንደ ልጆች፥ የሚለው ቃል በተለምዶ አነባቡ የሚሰጠው ትርጉም፤ አንድ ሰው ያልወለደውን ልጅ በሕግ በኩል ልጅ አድርጎ እንደሚወስደው ማለት ነው። ይህ የማደጎ ልጅ በተፈጥሮ ወልዶ ከሆነው ልጅ ጋር ልዩ [illegible] ሥልጣን አኩል ይካፈላል። በመንፈሳዊው መንገድ [illegible] ልጅ መሆን የሚገኙ በረከቶችን ሁሉ [illegible] [illegible] [illegible]

በአንድ መልኩ የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን መጠን ይቅርታን፥ ደኅንነትን፥ በሰማይ ርስት ማግኘትንና ሌሎችንም ታላላቅ በረከቶች ተቀብለናል። በሌላ በኩል ግን እንደ ልጆች ታላቅ ኃላፊነት ተሰጥቶናል፤ ይኸውም ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለብን በመሆን እንድንኖር ነው (ቁ. 4)።

የልጅነትን መብት ለማግኘት የበቃነው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስን እንደ ጌታ አድርገን ስንቀበልና በስሙም ስናምን፥ እግዚአብሔር ልጆቹ አድርጎ ይቀበለናል፤ የቤተሰቡም አባሎች እንሆናለን (ዮሐ. 1፥12፤ ገላ. 3፥26፤ 4፥5 እና ማብራሪያዎችን ይመለከቷል)።

6 እግዚአብሔር አስደናቂ ጸጋውን በመግለጥ እንዴት ልጆቹ እንዳደረገን ጳውሎስ በሚያስብበት ጊዜ በምስጋና ይሞላል። እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ያደረገው *«ክቡር ጸጋው እንዲመሰገን ነው»* በማለትም አሳቡን ይገልጣል። እግዚአብሔር ይህን ክቡር ጸጋ በነፃ ሰጥቶናል፤ እርሱን ለመቀበል ምንም ዋጋ አልከፈልንም፤ እግዚአብሔር ይህን ጸጋ የሰጠን በተወደደው ልጁ በክርስቶስ አማካይነት ነው።

7 እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ምድር የላከበት ዋናው ምክንያት እኛን ለመዋጀት[4] ወይም ለማዳን ነው። ኢየሱስ ወደ ምድር የተላከው ብዙ ወንዶችንና ሴቶችን ለማዳን ነው። ቤዛነት ሳናገኝ የእግዚአብሔር ልጆች ልንሆን አንችልም። የእግዚአብሔር የመዋጀት ሥራ ከፍጥረት ሥራ ይልቅ እጅግ ታላቅ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ያደረገው ትልቅ ነገር በአንደበቱ «ይሁን» ብሎ መናገር ነበር፤ ሰውን ሲዋጅ ግን እግዚአብሔር ራሱ በሞት ሸለቆ ማለፍ ነበረበት፤ ማለትም የራሱን ውድና አንድያ ልጅ ኢየሱስን ለቤዛነት *መሥዋዕት* አድርጎ መስጠት ነበረበት።

ጳውሎስ፥ «በእርሱ ቤዛነታችንን አገኘን» ይላል። በዚህ ምዕራፍ «በእርሱ» ወይም «በክርስቶስ» ወይም «በሚወደው በልጁ» በማለት ምን ያህል በመደጋገም እንደሚናገር (2፤3፤ 4፤6፤ 7፤8፤ 10፤11፤ 13 እነዚህን ቁጥሮች ይመለከቷል)። እንግዲህ ይህ ከጳውሎስ ትምህርቶች ዋናው መሆኑ ነው፤ ይህም ሕይወታችን «በክርስቶስ» ላይ መመሥረቱ ነው። ማንኛውም ዐይነት መንፈሳዊ በረከትና ኃይል ሁሉ የሚገኘው «በክርስቶስ» ነው። በቁ. 7 ላይ እንደተመለከተው ደግሞ የተዋጀነውም ቢሆን በክርስቶስ ነው። በደሙ ማለትም በሞቱ መሥዋዕት በመሆን ያስገኘልን ቤዛነት ነው። በእኛ ኃጢአት ምክንያት ቅጣትን በሥጋ ለመቀበል ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለሞተ ቤዛነታችንን በደሙ መሥዋዕትነት ተቀበልን። የእኛን ኃጢአት በሥጋው ለመክፈል ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተልን፤ ማለትም ለኃጢአታችን ዕዳ የማስተሰረያ መሥዋዕት ሆነልን (ማር. 10፥45፤ ሮሜ 3፥23–25፤ 1ጴጥ. 1፥18–19)።

በአንድ አቅጣጫ ስንመለከት መዋጀት (ደኅንነት) የኃጢአት ይቅርታን ማግኘት እንደሆነ እናያለን። ይቅርታን የምንቀበለውም በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት እንደሆነ ከዚሁ ከቁ. 7 እንረዳለን። ይሁን እንጂ በራሳችን ምንም ዋጋ ለመክፈል የበቃን አይደለንም።

8 እግዚአብሔር ጸጋውን በሰዎች ላይ ሲያፈስ ትንንሽ ጠብታዎች በመፈንጠቅ አይደለም፤ ይልቁንም ከጸጋው ባለጠግነት በሙላት ወይም አብዝቶ ያፈስልናል፤ ስለ ክቡር ጸጋው ሳንቆጠብ ዘወትር ማመስገን ይኖርብናል (ቁ. 6)።

9–10 እግዚአብሔር የፈቃዱን ምስጢር በክርስቶስ ትምህርት እንድናውቅ አድርጎናል። የእግዚአብሔር ፈቃድ፥ ሁሉም ነገሮች ተጠቃለው በአንዱ ራስ ማለትም በክርስቶስ ሥር እንዲሆኑ ማድረግ ነው (ቁ. 10)። የእግዚአብሔር ዕቅድ በሰማይና በምድር ያሉትን ነገሮች አጠቃሎ በክርስቶስ ጌትነትና ሥልጣን ሥር ማድረግ ነው (ፊል. 2፥9–11፤ ቆላ. 1፥15–20 ይመለከቷል)።

ይህ የሚሆነው መቼ ነው? ይህ የሚሆነው በዘመኑ ፍፃሜ ወይም እግዚአብሔር በመረጠው በራሱ ጊዜ ነው። ያም ጊዜ መቼ ሊሆን እንደሚችል ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ሊያውቀው የሚችል ማንም የለም።

የጳውሎስ ራእይ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ መገመት አያስቸግርም። ይህ ራእይ፥ ዓለም ሳይፈጠር በፊት አንሥቶ (ቁ. 4)፤ እስከ ዘመኑ ፍፃሜ ይደርሳል። በሰማይና በምድር ያሉት ነገሮች በሙሉ በጳውሎስ ራእይ ውስጥ ተጠቃልለዋል። ይሁን እንጂ፥ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በአንድ ትንሽ የወህኒ ቤት ክፍል ውስጥ ተጥሎ በነበረበት ጊዜ ነው። በሥጋ ዐይኖቹ ሊያይ የሚችለው የትንሿን ክፍል አራት ግድግዳዎች ብቻ ነበር፤ በመንፈሳዊ ዐይኑ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ዕቅድ አጠቃሎ ማየት ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ የራሳችን ሕይወት እንደ እስረኛ ሕይወት ሊሆን ይችላል። በዚህን ጊዜ እኛም መንፈሳዊ ዐይኖቻችንን ከፍተን ምስጢራዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መመልከት ይኖርብናል። ምስጢሩም ይህ ነው፤ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ዓለም የላከው፤ እኛን ለመዋጀት፥ ለእኛ የኃጢአት ይቅርታ ሊሰጠንና እኛን ቅዱሳንና ነውር የሌለብን የእግዚአብሔር ልጆች ለማድረግ ነው። እንግዲህ ፍጹም ደካሞችና ኃጢአተኞች የነበርነው ሕዝብ ይህን ክቡር የጸጋ በረከት በመቀበል ልጆቹ ሲያደረገን በርግጥም ምስጢራዊ ነው!

11–12 ጳውሎስ ራሱ አይሁዳዊ ቢሆንም፥ በነዚህ በሁለት ጥቅሶች ስለ አይሁዳውያን[5] የሚናገረው ነገር አለው። በቁ. 11 ላይ «በእርሱ ማለትም *በክርስቶስ* እኛ (አይሁዳውያን) *ተመረጥን[6]»* ይላል። በቁ 12 . ላይ ደግሞ «አይሁዳውያን የተመረጡት ለክብሩ ምስጋና እንዲሆኑ ነው» በማለት ያስረዳል። ክርስቶስ ከመምጣቱ ከብዙ ጊዜ በፊት ጀምረው አይሁዳውያን «አዳኝ ይመጣልናል» በማለት ይጠባበቁ ነበር። የአዳኙን መምጣት የአይሁዳውያን ነቢያት ቀደም ሲል በትንቢት ቃል ተናግረው ነበር፤ ስለሆነም ጳውሎስ በቁ. 12 ላይ በመጀመሪያ በክርስቶስ ተስፋ ያደረጉት አይሁዳውያን እንደሆኑ ይናገራል።

13 አሁን ደግሞ ጳውሎስ አመለካከቱን ዞር በማድረግ አይሁዳውያን ወዳልሆኑት ወደ ኤፌሶን ሰዎች ያተኩራል። «እናንተም ደግሞ በክርስቶስ ውስጥ ትታያላችሁ» ይላቸዋል፤ ማለትም ኤፌሶናውያን ጭምር በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት ደኅንነትን ለመቀበል እንደቻሉ ያስረዳል። የኤፌሶን አማኞች የደኅንነታቸው መሠረት የሆነውን የእውነትን ቃል ሰምተው ስላመኑበት በክርስቶስ ውስጥ መታየት ችለዋል።

ኤፌሶናውያን በክርስቶስ ውስጥ ለመታየት መቻላቸውን የሚያስረዳው ዋናው ምክንያት በክርስቶስ በማኅተም መታተማቸው ነው። ያም ማኅተም በተስፋ የተሰጣቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ «እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ይልክላችኋል» በማለት የሰጠውን ተስፋ (ዮሐ. 14፥26) ጳውሎስ በማስታወስ የተስፋ መንፈስ ቅዱስ ይለዋል።

ታዲያ የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም የሚባለው ምንድን ነው? በአዲስ ኪዳን ዘመን አንድ ንጉሥ በመልእክቶቹ ላይ ማኅተሙን ያደርጋል፤ ከዚህም የተነሣ መልእክቱን የሚቀበለው ሰው ያለ ጥርጥር ከንጉሡ የተላከ መሆኑን ያውቃል። በንጉሡ ማኅተም የታተመ ደብዳቤ የንጉሡን ሥልጣን ይይዛል ማለት ነው። በዚሁ ዐይነት በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም የሚታተም ማንኛውም ሰው የክርስቶስ እንደሆነና የክርስቶስ ሥልጣን እንዳለው እናውቃለን።

እዚህ ላይ በተጨማሪ ልናስታውስ የሚገባን፥ አንድ ሰው ክርስቲያን ለመሆንና መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል፥

የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ሆኖ ይገኛል። ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት «ማደጎ» የሚለውን ቃል በመዝገበ ቃላት ውስጥ ይመለከቷል።

4 መዋጀት፥ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው ትርጉም ቤዛ ወይም መሥዋዕት በመክፈል አንድን ሰው ከኃጢአቱ ነፃ ማውጣትን ያመለክታል።

5 አይሁዳውያን በመካከለኛው ምሥራቅ የሚኖሩ አንድ የሕዝብ ነገድ ናቸው። ከመጀመሪያው አንሥቶ አንዱን እውነተኛ አምላክ ሲያመልኩ ቆይተዋል፤ እግዚአብሔርም ለራሱ የተለዩ ሕዝብ እንዲሆኑ መርጦአቸዋል። ራሱም ኢየሱስ አይሁዳዊ ነበር። ተጨማሪ ማስረጃ ለማግኘት አይሁዳዊ የሚለውን ቃል ከመዝገበ ቃላት ውስጥ ይመለከቷል።

6 እኛ ተመረጥን በሚለው ቃል ፈንታ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች «ኢኛ ወራሾች ሆንን» ብለውታል። ትርጉሙ ተመሳሳይ ነው። አይሁዳውያን የተመረጡት ወራሾች እንዲሆኑ ነው።

ማለትም በማኅተሙ ለመታተም ቢፈልግ ሁለት ነገሮችን ማድረግ ይጠበቅበታል። በመጀመሪያ የወጌልን ቃል የሰማ ሊሆን ይገባዋል፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በክርስቶስ ማመን ይኖርበታል።

14 መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ እንዲሁም የክርስቶስ መንፈስ ነው። በቀላል አነጋገር መንፈስ ቅዱስ ከመለኮት አንዱ[7] ነው። እግዚአብሔር በልባችን የሚገባውና ሕይወታችንን የሚለውጠው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የመንግሥተ ሰማይን ኑሮ አሁን መለማመድ እንጀምራለን። በመንግሥተ ሰማይ በሙሉ የምንወርሰውን ርስት አሁን በመያዣ መልክ የምንይዘውም በመንፈስ ቅዱስ ነው። በመንግሥተ ሰማይ የምንቀበለውን ርስት በዚህ ዓለም በሙሉ ልንወርስ አንችልም፤ ቀሪውን ወደ ፊት በመንግሥተ ሰማይ ስለምንወርስ አሁን መያዣ ተሰጥቶናል። አሁን መያዣ ሆኖ የተሰጠን መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ወደ ፊት ሙሉ ርስታችንን እንደምንቀበል ምንም ጥርጥር የለንም (ሮሜ 8፥16–17፤ 2ቆሮ. 1፥22 ይመለከቷል)።

እስከ አሁን የተቀበልናቸውና ወደፊትም በመንግሥተ ሰማይ የምንቀበላቸው በረከቶች የእግዚአብሔር ክብር እንዲመሰገን እንደሆነ ጳውሎስ በመደጋገም ያስታውሰናል። ስለዚህ ጉዳይ በዚህ ምዕራፍ ብቻ ሦስት ጊዜ ተናግሮአል (ቁ. 6፤ 12፤ 14)። እንዲሁም «እንደ እግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ወይም ዕቅድ» የሚለውን ሦስት ጊዜ ጠቅሶአል (ቁ. 5፤ 9፤ 11)። በዚህም ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ተጀምሮ፤ ለእግዚአብሔር ክብር ፍጻሜ እንደሚያስገኝ አብራርቶ ያመለክታል። እንግዲህ እዚህም ላይ ለሕይወታችን የተሰጠውን ሙሉ ትርጉምና ዓላማ ማየት እንችላለን። በክርስቶስ ለማመንና የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባሎች ለመሆን የበቃነው ከእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ የተነሳ ነው። ስለዚህ አሁን ለክብሩ ምስጋና ለመስጠት መኖር ይገባናል።

ዓለማውያን ሰዎች[8] «ሕይወቴን በራሴ ፈቃድና ለራሴ ክብር ስል እኖራለሁ» ይላሉ። በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ግን «እኔ ሕይወቴን የምኖረው በእግዚአብሔር ፈቃድና ለእግዚአብሔር ክብር ነው» ይላሉ። የዓለማዊ ሰው አስተሳሰብና የክርስቲያን አስተሳሰብ ምን ያህል የተለያየ እንደሆነ በዚህ መገመት እንችላለን።

ምስጋናና ጸሎት (1፥15–23)

15–16 ምንም እንኳ ጳውሎስ ይህን መልእክት ከሁለት ሺ ዓመት በፊት ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈው ቢሆንም፥ ዛሬም ላለነው ሰዎች ጭምር የተጻፈ ነው። እዚህ ላይ ጳውሎስ ወደ እግዚአብሔር ጸሎቱን የሚያቀርበው ለኤፌሶን ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጭምር ነው።

ጳውሎስ ዛሬም በሕይወት ቢኖር ስለእምነታችንና ለቅዱሳን ሁሉ ስለሚኖረን ፍቅር ምን ይሰማ ነበር? ስለ እምነታችንና ፍቅራችን እግዚአብሔርን ሊያመሰግን ይችል ይሆን?

17 እዚህ ላይ ለኤፌሶን ሰዎችና ለእኛም ጭምር ባቀረበው ጸሎት ጳውሎስ ስለምንድን ነው የጸለየው? እኛና የኤፌሶን ሰዎች የጥበብና የመገለጥ መንፈስ[9] እንዲሰጠን ነው። ይህም ጥበብ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ደግሞ እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ ለማወቅ እንድንችል ነው። መንፈሳዊ ጥበብና መገለጥ ዘወትር ሊመጣ የሚችለው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ ከሰው አይደለም።

ጳውሎስ በጸሎቱ ላይ በዚህ በሚሰጠን ጥበብ እኛና የኤፌሶን ሰዎች ሦስት ነገሮችን እንድናውቅ ይማልድልናል። አንደኛ በእግዚአብሔር በመጠራታችን ስላለን ተስፋ (ቁ. 18)፥ ሁለተኛ በተከበረው ርስታችን ምን ያህል ባለጠጎች እንደምንሆን (ቁ. 18)፥ ሦስተኛ ወደር የሌለውን የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል እንድናውቅ ነው (ቁ. 19)።

18 እኛ የተጠራነው ለምን ዐይነት ተስፋ ነው? እኛ ተስፋ የምናደርገው ጳውሎስ ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ የዘረዘራቸውን ነገሮች ነው። ከኃጢአት ነፃ ለመውጣት ተስፋ እናደርጋለን፥ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ተስፋ እናደርጋለን፥ ቅዱሳን ሆነን በክርስቶስ ጸንተን ለመኖር ተስፋ እናደርጋለን። ለእነዚህ ሁሉ ነገሮች የተጠራን ስለሆነ ተስፋችንን በእነርሱ ልናደርግ እንችላለን።

እግዚአብሔር ለእኛ ተስፋ የገባልን ክቡር ርስት ምን ዐይነት ነው? ለዚህ ርስት መያዣ የሆነውን መንፈስ ቅዱሱን አስቀድመን ተቀብለናል (ቁ. 14)። ቀሪው ርስታችን በመንግሥተ ሰማይ ይጠብቀናል፤ በመንግሥተ ሰማይ ካለን ርስት በጣም አስደናቂ የሆነው ክፍል ደግሞ ለዘላለም ከእግዚአብሔርና ከክርስቶስ ጋር መኖራችን ነው። ከዚያም በተጨማሪ ራሱን ክርስቶስን መስለን እንገኛለን ሲሆን (1ዮሐ. 3፥2)፥ ከክርስቶስም ጋር አብረን እንነግሣለን (2ጢሞ. 2፥12)።

19 የክርስትናን ሕይወት ስንጀምር ተጠርተን እንደ ነበረ ሁሉ በክርስትና ሕይወታችን መደምደሚያ ላይ ደግሞ ክቡር ርስትን እንወርሳለን። በመጀመሪያውና በመጨረሻው መካከል እግዚአብሔር ንጽጽር በማይገኝለት፣ ታላቅና ወሰን በሌለው ኃይሉ ሕይወታችንን ይጠብቃል። የእግዚአብሔር ኃይል ወሰን የለውም፤ ይህንንም ኃይል በክርስትና ሕይወታችን ሁሉ ልናገኘው እንችላለን።

20–21 ይህ የእግዚአብሔር ኃይል ምን ይህል ታላቅ ነው! እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ከሞት ያስነሣው በዚህ ኃይል ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ በአባቱ ቀኝ በሰማይ ነግሦ ሊኖር የቻለው በዚህ ኃይል ነው፤ በንጉሥነቱም ማንኛውም አለቅነት፥ ሥልጣን፥ ኃይልና ጌትነት ተገዝተውለት ይኖራሉ (ቁ. 21)። እንዲሁም ሰይጣንና መናፍስቱ ሁሉ አጋንንቱም ጭምር ለእርሱ ይገዛሉ። በክፉትና በሞትም ላይ ሁሉ ሥልጣን አለው። አሁንና ወደፊትም በሰማይና በምድር በሚገኙ በማናቸውም ነገሮች ላይ ሥልጣን አለው። እንግዲህ በእግዚአብሔር ኃይል አማካይነት ዛሬም ነግሦ ይኖራል። ወደፊትም ቢሆን ለዘላለም ይነግሣል።

የሞተን ሰው አሥነስቶ እንደ ገና በሕይወት ለማኖር የሚችል ማንም ሰው የለም። የእግዚአብሔር ኃይል ግን ይህን ማድረግ ይቻለዋል። ለእግዚአብሔር ምንም የሚያስቸግረው ነገር የለም (ማር. 10፥27)። ክርስቶስን ከሞት ያስነሣው ያው ኃይል፥ ለእኛ ለምናምነው ሁሉ ዛሬም ይገኝልናል። እኛ በኃጢአታችን ሞተን የነበርነው (ኤፌ. 2፥1) በዚያው ኃይል ከክርስቶስ ጋር ተነሥተናል (ኤፌ. 2፥4–5)። እንዲሁም ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጠናል (ኤፌ. 2፥6)። ያም ኃይል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ዛሬም በየቀኑ ሊገኝልን ይችላል። ስለሆነም ይህን እንዲሰጠን በየቀኑ መጸለይ ይኖርብናል።

22–23 ሁሉ ነገር በክርስቶስ እግር ሥር ማለትም በሥልጣኑ ሥር እንደተቀመጠ እናያለን (ቁ. 22)። ብዙ ኃጢአት፥ ብዙ ድካም፥ ብዙ ፍርሃትና፣ ብዙ የኑሮ ስጋት እንደተጫነን ሲሰማን፥ ሁሉ ነገር ተጠቃሎ በክርስቶስ እግር ሥር መሆኑን እናስታውስ። በክርስቶስ እግር ሥር የሆነ ነገር ሁሉ በእኛም እግር ሥር ውሎአል።

ጳውሎስ በዚህ አሳብ ላይ ሲናገር፥ ክርስቶስን በቤተ ክርስቲያን ከሁሉ በላይ እንዲሆን ራስ አደረገው ይላል። በኤፌሶን 5፥23 ላይ ጳውሎስ «ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው» ይላል። ክርስቶስ ራስ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን አካሉ ነች ማለት ነው (ቁ. 23)። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ከሆነች እኛ አማኞች ደግሞ የአካሉ ክፍሎች (ብልቶች) ነን ማለት ነው (ሮሜ 12፥4–5፤ 1ቆሮ. 12፥12፤27 እና ማብራሪያዎችን ይመለከቷል)።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙላት ናት፤ አንድ መንግሥት የንጉሡ ሙላት ሊሆን እንደሚችለው ሁሉ፥ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስ ሙላት ናት ማለት ነው። ሙላቱን የምትፈጽመው ቤተ ክርስቲያን አይደለችም።

---

[7] አንዱ የሚለው ቃል «የሕላዌነት ዘርፍ» ማለት ይቻላል፤ ስለ መንፈስ ቅዱስ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ቃል ከአጠቃላይ መግለጫ ይመለከቷል።

[8] ዓለማውያን ሰዎች ዓለምንና በውስጡ ያሉትን ነገሮች ከእግዚአብሔር አብልጠው የሚወዱ ናቸው።

[9] እዚህ ላይ ጳውሎስ የሚጠቅሰው ስለ መንፈስ ቅዱስ ይሁን ወይም የራሱን የሰውን የጥበብና የመግለጥ መንፈስ የቱን እንደሚናገር ማወቅ አይቻልም።

ነገር ግን ሁሉን ነገር በሁሉ መንገድ ሊያሟላ የሚችል ክርስቶስ ራሱ ብቻ ነው (ቁ. 23)። ከክርስቶስ የጸጋ ሙላት የተነሣ እኛ ሁላችን በረከት በበረከት ላይ ተትረፍረፎ ተሰጥቶናል (ዮሐ. 1፥16)። ክርስቶስ ራሱ አምላክ ስለሆነ ይህ ነገር ሊያስደንቀን አይገባም (ዮሐ. 10፥30፤ ቆላ. 1፥15–20፤ አስተምህሮ ዳሰሳው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለውን ይመለከቷል)።

ምዕራፍ 2

በክርስቶስ ሕያው መሆን (2፥1–10)

1 «በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ምክንያት የሞታችሁ ነበራችሁ» በማለት ጳውሎስ የኤፌሶንን ሰዎች ያስታውሳቸዋል። እነርሱ የሞቱት በምን መንገድ ነበር? በመንፈሳዊ ህይወታቸው የሞቱ ነበሩ። ከእግዚአብሔርም ተለይተዋል (ኤፌ. 4፥18)። ኃጢአታችን ከእግዚአብሔር ይለየናል፤ ኃጢአተኛ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ ፍጹም ያስቸግረዋል። ከእግዚአብሔር ተለይቶ መኖር መንፈሳዊ ሞት ነው።

2 የኤፌሶን ሰዎች በክርስቶስ ከማመናቸው በፊት እጅግ አስከፊና በመከራ የተሞላ ሕይወት ነበራቸው። መላ አፈጣጠራቸው በከፋት ላይ የተመሠረተና የሚከተሉትም የዓለምን መንገድ ነበር። በአጠቃላይ አኗኗራቸው የራሳቸውን ፈቃድ በማስቀደምና ለራሳቸው ክብር በመቆም ነበር (ኤፌ. 1፥14)። ዓለማውያን የሆኑ ሰዎች የሚኖሩት ራሳቸውን ለማስደሰት ብቻ ነው። ሰው ግን መኖር የሚገባው እግዚአብሔርን ለማስደሰት ነው፤ የዓለምን መንገድ ተከትለን ለመኖር የምንፈልግ ሰዎች ከሆንን እግዚአብሔርን አንታዘዝም ማለት ነው። እንዲያውም የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነን እንገኛለን።

እዚህ ላይ ጳውሎስ፥ በአየር ላይ ስልጣን ያለው አለቃ የሚለው፥ የርኩሳን መናፍስት ሁሉ አለቃ የሆነውን ሰይጣንን ነው። ኢየሱስም ሰይጣንን «የዚህ ዓለም ገዥ» ነው ይላል (ዮሐ. 12፥31)። በዚህም ሰይጣን የዚህን ዓለም መንገድ በሚከተሉና ለእግዚአብሔርም በማይታዘዙ ሰዎች ሕይወት ላይ ሥልጣን እንዳለው ያስረዳል።

3 እኛም ክርስቲያኖች ብንሆን በክርስቶስ ከማመናችን በፊት በኃጢአት ኖረናል፤ በተፈጥሮአችንም የቁጣ ልጆች ነበርን። የእግዚአብሔርን መዓትና ቅጣት ልንቀበል ይገባን ነበር። የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሰው ቁጣ አይደለም። እግዚአብሔር በኃጢአት አንድ ቀን ተቆጥቶ በሌላው ቀን የሚረሳ አይደለም፤ እግዚአብሔር በፍጹም ቅዱስ ነው። ቅዱስ ያልሆነ ነገርን መታገሥ አይችልም፤ ስለሆነም ክፋትንና ክፋት በመሥራት የሚጸኑትን ሰዎች ለማጥፋት ወስኖአል።

ከዚህ ሁኔታ ልንረዳ የምንችለው በተፈጥሮአቸው[10] ያሉና ዓለማውያን የሆኑ ሰዎች፤ ክርስቶስን አንቀበልም ብለው በመጽናታቸው እጅግ አደገኛና አስፈሪ በሆነ ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን ነው። ወዳጆቻችን፥ ጎረቤቶቻችንና እንዲሁም ዘመዶቻችን ሁሉ ክርስቶስን ባለመቀበላቸው በመንፈሳዊ አንፃር የሞቱ ናቸው። ከእግዚአብሔር ተለይተው ቁጣውን ለመቀበል ተዘጋጅተዋል። አዎ! በሕይወት ያሉ ይመስላሉ፤ በሥጋዊ አኗኗራቸውም ህያዋን ናቸው፤ በመንፈሳዊ አቋማቸው ግን ሞተዋል። በመንግሥተ ሰማይ ዘላለማዊ ሕይወትን አይወርሱም፤ ይሁን እንጂ፥ ከሞት ለመነሣትና የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ የደኅንነት መልካም ዜና የሆነውን የእውነት ቃል መስማት ይኖርባቸዋል (ኤፌ. 1፥13)። ቃሉንም ሰምተው መቀበል ወይም ማመን ይገባቸዋል። እኛም እስከ አሁን ያመንነው ላልሰሙት እንዲሰሙ የማድረግ ኃላፊነት አለብን። እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፤ ያላመኑና የዚህን ዓለም መንገድ የሚከተሉ ሰዎች ሁሉ ፍጹም ክፉዎች ናቸው ማለት ነውን? ሰው ሲባል በተፈጥሮው ፍጹም መጥፎ ነው ማለት ነውን? መልሱ አይደለም የሚል ነው። ሰዎች ሁሉ የተፈጠሩት በእግዚአብሔር አምሳል ነው (ዘፍ. 1፥27)። ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን በታላቅ ትጋት ይከተላሉ፤ እርሱን ለማስደሰት ይጥራሉ። ይሁን እንጂ፥ የሰዎችን ኃጢአት ለማስወገድ በመስቀል ላይ የሞተውን ክርስቶስን ሳይቀበል ማንም ሰው የቱንም ያህል ቢጥር እግዚአብሔርን ሊያስደስት አይችልም (ዮሐ. 3፥18፤ 36፤ 14፥6፤ የሐዋ. 4፥12 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

4–5 የሰው ልጅ በተፈጥሮው ምን ያህል ክፉና የረከሰ እንደሆነ አይተናል (ሮሜ 3፥10–12)። በመንፈሳዊ አቋሙም ምን ይህል ሕመምተኛ እንደሆነ ተመልክተናል። በእርግጥም ገና ድሮ ሞቶአል! እንደዚህ ዐይነቱን ተስፋ ቢስ በሽተኛ ምንም ዐይነት መድኀኒትና ምንም ዐይነት ሐኪም ጭርሶ ሊረዳው አይችልም። የሞተን በሽተኛ ሊረዳ የሚችል ሐኪም አንድ ብቻ ነው፤ ይህም ሐኪም እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔርም መድኀኒት ፍቅር ነው፤ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ እግዚአብሔር ጸጋውንና ምሕረቱን በኃጢአተኛው ላይ ያፈስሰዋል። እነዚህ «ፍቅር፥ ጸጋና ምሕረት» የተባሉ ሦስት ቃላት ሁል ጊዜ በአንድነት ይገኛሉ። እነርሱም ልክ እንደ አንድ ትልቅ የግዚአብሔር የፍቅር ስራ ናቸው። አቤት! አንዱ እውነተኛው አምላክ ከሌሎች አማልክቶች ምን ያህል ልዩ ነው! እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ስለወደደ አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮ ስለ ኃጢአታችን እንዲሞት ፈቀደ (ዮሐ. 3፥16 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

6 እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ ብቻ ሕያው እንድንሆን አላደረገንም፤ ነገር ግን በመንግሥተ ሰማይም ከክርስቶስ ጋር አብረን እንድንቀመጥ ፈቀደ። እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ከተቀመጥን፥ የተቀመጥነው በምን ላይ ነው? በዙፋን ላይ! (ራእ. 3፥21)። ጳውሎስ አማኝ በመንግሥተ ሰማይ ስላለው ቦታ እርግጠኛ በመሆኑ «እግዚአብሔር በሰማያዊ ስፍራ ከክርስቶስ ጋር አስቀመጠን» በማለት አስቀድመን እዚያ እንደተቀመጥን በኃላፊ ጊዜ ይናገራል (ሮሜ 8፥30 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

7 እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር አስነሥቶን በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አብረን እንድንቀመጥ ለምን አደረገ? ይህንንም ያደረገው በሚመጡት ዘመናት ለሚመጡት ትውልዶች ወሰን የለሽ ፍቅሩንና የጸጋውን ባለጠግነት በምሕረት ለመግለጥ ፈልጎ ነው።

8 ይህ ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ጥቅሶች አንዱ ነው። በዚህ ጥቅስ ሁለት ዋና ቃላት አሉ። እነርሱም «ጸጋና እምነት» የተባሉት ናቸው። እነዚህን ቃላት በቀላሉ ለመተርጎም፥ ጸጋ ስንል እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን ደኅንነት በነጻ መስጠቱን የሚያመለክት ሲሆን፤ እምነት ደግሞ ያንን ስጦታ መቀበላችንን የሚያመለክት ነው። እምነት ሥራን ሳይሆን መቀበልን የሚያሳይ ነው። እዚህ ላይ ማየት የሚገባን እምነትም ራሱ ከእግዚአብሔር የሚሰጠን ስጦታ እንደሆነ ነው። እምነት ሊመጣ የሚችለው የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ነው (ሮሜ 10፥17)። ስለሆነም እዚህ ላይ ልንረዳ የምንችለው ደኅንነት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ነው። ደኅንነትን ለማግኘት ምንም የምንከፍለው ዋጋ የለንም፤ ለመዳን የሚገባን ሆነን ለመገኘትም ምንም የምናደርገው ነገር የለም።

በዚህም ክርስትና ከሌሎች ሃይማኖቶች በጣም የተለየ እንደሆነ እናያለን። ሌሎች ሃይማኖቶች «ሰው ለመዳን ብዙ መልካም ሥራዎችን በመሥራት ለመመስገን መብቃት አለበት» በማለት ያስተምራሉ። እንዲሁም «ሰው ልዩ ልዩ ሕጎችንና ሥርዓቶችን በመፈጸም ከኃጢአተኝነቱ ሊነፃ ይችላል» በማለት ያስተምራሉ። እነዚህ ትምህርቶች ሁሉ ልክ አይደሉም። በውጫያዊ ሥራ ውስጣዊ ሰውነታችንን ማንፃት አንችልም። የቱንም ያህል ምልካም ሥራ ብንሠራ ውስጣዊ ሰውነታችን ካልነፃ ወይም ካልጸደቀ እግዚአብሔርን ማስደሰትም ሆነ ደኅንነትን ማግኘት አንችልም (ገላ. 2፥15–16 እና ማብራሪያውን፤ ከአስተምህሮ ዳሰሳው የደኅንነት መንገድ የሚለውን ይመለከቷል)።

---

10 ተፈጥሯዊው ሰው የሚከተለው በልቡ ያለውን የስስት ምኞትና የተፈጥሮ ጉዳዮችን ብቻ ነው። ሌላ ተጨማሪ ሕግ አያውቅም፤ እርሱ የሚያውቀው የራሱን የኃጢአት ምኞት መፈጸሙን ብቻ ነው። ሰው ሁሉ በተፈጥሮ ኃጢአተኛ ነው (ሮሜ 3፥10–12 ይመለከቷል)።

9 በራሳችን ሥራ ወይም ጥረት ደኅንነትን ማግኘት እንደማንችል ጳውሎስ እዚህ ላይ እንደገና ያወሳል። ማንም ሰው ቢሆን «በራሴ ሥራ መንግሥተ ሰማይ ልገባ ችያለሁ» ማለት አይችልም። ሰው ደኅንነትን ማግኘት የሚችለው በክርስቶስ ላይ ባለው እምነት ብቻ ነው። አዳኛችን ሊሆን የሚችለውም ክርስቶስ ብቻ ነው። እርሱ እኛን ያዳነን በኃጢአታችን ምክንያት ሊደርስብን የሚችለውን የሞት ቅጣት በመቀበል ነው። በእኛ ምትክ ሆኖ ሞተ፤ በክርስቶስ ስናምን ለኃጢአታችን ይቅርታን እንቀበላለን። በእግዚአብሔርም ፊት ጻድቅን ሆነን እንገኛለን (ሮሜ. 3፥22–24፤ 8፥1 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ከኃጢአታችን ስንነፃና ቅዱሳን ስንሆን፥ እግዚአብሔር ልጆቹ አድርጎ ይቀበለናል። ታዲያ ልንነፃና ቅዱሳንስ ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን ብቻ ነው።

10 በዚህ ጥቅስ ላይ እግዚአብሔር እኛን ያዳነበትን ሁለተኛ ዓላማ እናገኛለን (የመጀመሪያው ዓላማ በቁ. 7 ላይ እንደተገለጠው በሚመጡት ዘመናት ለሚመጡት ትውልዶች የጸጋውን ባለጠግነት ለማሳየት እንደነበረ አይተናል)። በደኅንነታችን ሁለተኛ ዓላማ እንደምናየው ደግሞ አንድ ጊዜ ከዳንን በኋላ መልካም ሥራን መሥራት ይኖርብናል። እዚህ ላይ ማስታወስ ያለብን ለመዳን ምንም ዐይነት መልካም ሥራ መሥራት እንደማይኖርብን ነው። ከዚህም ይልቅ እኛ የምንድነው መልካም ሥራን ለመሥራት ነው። ማለትም በመልካም ሥራችን ምክንያት አልዳንም፤ ይልቁንም እኛ መልካም ሥራን የምንሠራው ስለዳንን ነው።

እያንዳንዱ ክርስቲያን የሚሰራውን መልካም ሥራ እግዚአብሔር በቅድሚያ አዘጋጅቶአል። ስለዚህም ክርስቲያን የሆነ ሁሉ «በጸጋ ድኛለሁ ከእንግዲህ ወዲህ መልካም ሥራ እንድሠራ አይጠበቅብኝም» ብሎ ማሰብ አይገባውም። አዎ በመጀመሪያ መምጣት ያለበት ደኅንነት ነው፤ ከደኅንነት በኋላ ግን መልካም ሥራ ሊመጣ ይገባዋል። ከሁሉ በፊት በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ሊኖረን ያስፈልጋል፤ ከዚያን በኋላ በአዲስ ሕይወት ልንኖር ይገባናል (2ቆሮ. 5፥17፤ ኤፌ. 4፥1 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

በክርስቶስ አንድ ስለመሆናችን (2፥11–22)

11 አይሁዳውያን ያልነበሩ ሕዝቦች ሁሉ «አረማውያን» ይባሉ ነበር። በጳውሎስ ዘመን የነበሩ አይሁዳውያን አረማውያንን «ያልተገረዙ» በማለት ይሰድቡአቸው ነበር። አረማውያን እንደ አይሁዳውያን የግዝረት ሥርዓት አልነበራቸውም። በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት አይሁዳዊ ሆኖ የሚወለድ እያንዳንዱ ወንድ ልጅ በስምንተኛ ቀን ከሽንት መሽኛው ብልት ጫፍ ላይ ሸለፈቱ ይቆረጥለታል። ይህም «ግዝረት» በመባል ይታወቃል (ዘፍ. 17፥9–14)። እንግዲህ ግዝረት ውጫዊ የሆነ አይሁዳዊ የመሆን ምልክት ነው። ስለዚህ በጳውሎስ ዘመን የነበሩ አይሁዳውያን ራሳቸውን «የተገረዙ» በማለት ይጠሩ ነበር።

12 በዚህ ጥቅስ ጳውሎስ ከዚህ በፊት ስለነበራቸው ሁኔታ ኤፌሶናውያንን ያሳስባቸዋል። በመጀመሪያ ስለ ክርስቶስ ምንም ነገር አልሰሙም ነበር። በሁለተኛ ደረጃ የእስራኤላዊ ዜግነት አልነበራቸውም ማለትም፤ አይሁዳውያን አልነበሩም። ሦስተኛም ደረጃ እግዚአብሔር ከአይሁዳውያን ጋር የገባው የቃል ኪዳን ተስፋ ተካፋዮች አልነበሩም። እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን የሰጣቸው ታላቅ ተስፋ አንድ አዳኝ እንደሚልክላቸው ነበር። በእነዚህ ሦስት ምክንያቶች የተነሣ አይሁዳውያን እነዚህን የኤፌሶን አረማውያን «ተስፋም ሆነ ምንም አምላክ የላችሁም» ይሉአቸው ነበር። አንዱን እውነተኛ አምላክ ስለማያውቁ በጣም ርቀው ነበር (ቁ. 13)።

13 ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ምንም እንኳን ራሱ አይሁዳዊ ቢሆንም፥ እርሱ የመጣው አይሁዳውያንን ብቻ ለማዳን ሳይሆን፥ አረማውያንንም ጭምር ለማዳን ነው። ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣው አይሁዳውያንንና አረማውያንን ጨምሮ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን ነው። በክርስቶስ ደም (በክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሞት) ምክንያት አማኞች ሁሉ ቀርበዋል። ማለትም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባሎች ሆነዋል። ስለሆነም አይሁዳውያንም ሆኑ አረማውያን በኢየሱስ ከማመናቸው የተነሣ የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባሎች ናቸው (ገላ. 3፥24 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

14 ክርስቶስ ሰላማችን ነው። ክርስቶስ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሰላምን ይፈጥራል፤ እንዲሁም በሰውና በሰው መካከልም ሰላምን ያስገኛል። ስለሆነም በአይሁዳዊና በአረማዊ መካከል ሰላምን ይፈጥራል፤ ለያይቶን የነበረውን የጥል ግድግዳ[11] አፍርሶአል። በአይሁድና በአረማዊያን፥ በሃብታምና በድሃ፥ በብሔርና በብሔረሰቦች መካከል የነበረውን መከፋፈልና ጠላትነትን አጥፍቷል። በዚህ ጥቅስ ላይ ጳውሎስ የሚያስበው ስለ አይሁዳውያንና ስለ አረማውያን ጥላቻ ነው። አይሁዳውያን ከአረማውያን እንደሚበልጡ ስለሚያስቡና በፊታቸውም ንጹሕ ሆነው ስለማይታዩአቸው፥ አይሁዳውያን ከእነርሱ ጋር ኅብረት አያደርጉም ነበር።

15 አይሁዳውያን ሕግን በመፈጸም ደኅንነትን እናገኛለን ብለው ስለሚያስቡ በሕግ መጽሐፋቸው ላይ የሠፈሩትን ብዙ ትእዛዛትና ደንቦች ይፈጽሙ ነበር። የአይሁዳውያን ሕግ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን አንደኛው ዐሥርቱን ትእዛዛት የያዘው የሞራል ሕግ ነው (ዘጸ. 20፥1–17)። ሁለተኛው ደግሞ የሥርዓት ሕግ ነው። በዚህም ውስጥ ስለ መብልና ስለ መታጠብ እንዲሁም ልዩ ልዩ መስዋእቶችን ስለ ማቅረብ የሚያስረዱ ደንቦች ይገኙበታል። በሥርዓቱ ሕግ መመዘኛ መሠረት አረማውያን የነጹ አልነበሩም፤ ስለሆነም መቅደሱን ያረክሳሉ ስለሚባል በአይሁዳውያን ቤተ መቅደስ ወደ ውስጠኛው ክፍል መግባት አይፈቀድላቸውም። የአይሁዳውያን ሕግ ራሱ እንደ ማገጃ ወይም እንደ ጥል ግድግዳ እንደነበረ እናያለን (ቁ. 14)።

ክርስቶስ የሥርዓትን ሕግ[12] በማፍረስ የጥል ግድግዳን አስወግዶአል። ክርስቶስ «ሰው ሊድን የሚችለው ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን በእርሱ በማመን ብቻ ነው» በማለት አስተምሮአል (ገላ. 2፥15–16 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)፤ ስለዚህ የሥርዓትን ሕግ በማፍረስና በአይሁዳውያንና በአረማውያን መካከል የነበረውን ማገጃ በማስወገድ፥ ክርስቶስ ከሁለቱ ወገኖች አንድ አዲስ ሰው ፈጥሮአል። ከሁለቱ ሕዝቦች ማለትም ከአይሁዳውያንና ከአረማውያን መካከል አንድ አዲስ ሕዝብ ማለትም አማኞችን ፈጠረ። በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ አይሁዳውያንም ሆኑ አረማውያን፥ ሀብታሞችም ሆኑ ድኾች፥ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሁሉ በእርሱ አንድ ሆነዋል (ገላ. 3፥28)። ክርስቶስ ራስ የሆነለት የአንድ አካል (ቁ. 16) ክፍሎች ሆነዋል ማለት ነው (1ቆሮ. 12፥13፤ 27፤ ኤፌ. 5፥23)።

16 ክርስቶስ በአይሁዳዊና በአረማዊ መካከል ብቻ ሰላም እንዲወርድ አላደረገም፤ ነገር ግን ሁለቱንም ወገኖች ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ ሰላም እንዲወርድ አደረገ (ሮሜ 1፥18–20፤ 5፥1 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ክርስቶስ በመስቀሉ (በመስቀል ላይ በመሞቱ) አማኞችን ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ማለትም ቤተክርስቲያን እንዲሆኑ አደረገ። እግዚአብሔር ልጆችን በሙሉ በእኩል ደረጃ ይመለከታል። አንዱን ከሌላው ለይቶ አድሎ

[11] በኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ መቅደስ ውስጣዊ ክፍል ዙሪያ አረማውያን እንዳይገቡበት ለመከልከል ግድግዳ ወይም ማገጃ ነገር ነበረው። ጳውሎስ በዚህ ጥቅስ ላይ የጥላቻና የመለያ ማገጃ ብሎታል፤ ምክንያቱም ያ ማገጃ ወይም ግድግዳ በአይሁዳውያንና በአረማውያን መካከል ያለውን ጥላቻ የሚያሳይ ምልክት ነበር። አንዳንድ አረማውያን በሩቅ ተጥለው መቀመጣቸውንና (ቁ. 13) ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የማይችሉ መሆናቸውን የሚያሳይ ምልክት ነበር።
ጳውሎስ ያንን ግድግዳ ክርስቶስ አፈራርሶታል ሲል፥ ክርስቶስ ያፈረሰው ራሱን ግድግዳውን ሳይሆን በግድግዳው የተመሰለውን ጥላቻ ማለቱ ነው። በመጀመሪያ ግድግዳው ያስፈለገበት ምክንያት ንጹህ ያልሆኑትን አረማውያን ወደ ቅዱሱ እግዚአብሔር መቅረብ እንዳይችሉ ለማድረግ ነበር። አሁን ግን ክርስቶስ አረማውያን በእምነት ንጹሕ እንዲሆኑ አስችሎአቸዋልና ወደ እግዚአብሔር ፊት እንዲቀርቡ ሆነዋል። ግድግዳው ከእንግዲህ ወዲህ አስፈላጊ አይደለም፤ ስለሆነም ክርስቶስ አረማውያን ከእግዚአብሔር የተለዩበትን ማገጃ አስወግዶታል፤ በሞቱም በኩል አረማውያን አሁን ወደ እግዚአብሔር ቀርበዋል (ቁ. 13)።

[12] ይሁን እንጂ ክርስቶስ የሞራልን ሕግ አልደመሰሰም፤ ለተጨማሪ ማብራሪያ ማቴ. 5፥17–20 ይመለከቷል።

አያደርግም። ምንም ዐይነት ማገኛ ወይም የጠላትነት ግድግዳ በመካከለቸው እንዲኖር አይፈልግም።

ስለዚህም በቤተክርስቲያናችን ምንም ዐይነት የሚለያይ ግድግዳ እንዳይኖር እርግጠኞች መሆን አለብን። ምናልባት ቢፈጠሩ እንኳ፥ በፍጥነት ልናፈራርሳቸው ይገባናል። ጠንቃቆች ካልሆንን ይህን የመሰለ የጥል ግድግዳ በሀብታምና በድኻ፥ በተማረና ባልተማረ፥ በሴቶችና በወንዶች፥ በውጭ አገር ሰውና በአገሬው ሰው፥ በበላይና በበታች መካከል ሊገነባ ይችላል፤ ነገር ግን ይህ እንዲሆን መፍቀድ የለብንም።

17–18 ከዚህ በፊት በጣም ርቀው የነበሩትና (አረማውያን) በጣም ቀርበው የነበሩት (አይሁዳውያን) አሁን በኩል ደረጃ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይችላሉ። ሁለቱም በእኩል ደረጃ ወደ እግዚአብሔር መድረስ ይችላሉ።

በቁ. 18 ላይ እግዚአብሔር በሦስት አካል ተገልጦ እንደሚኖር ጳውሎስ ያወሳል፤ በእርሱ (በክርስቶስ፥ ልጅ በሆነው አምላክ)፥ ወደ አብ (አባት በሆነው አምላክ)፥ በአንድ መንፈስ (መንፈስ ቅዱስ በሆነው አምላክ) መድረስ እንችላለን። ይሁን እንጂ፥ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሦስት አካል ማለትም አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ቢሆንም አንድ አምላክ ነው። ክርስቲያኖች ይህን የአምላክን ሦስት አካል አንድ በማድረግ «ሥላሴ» ይሉታል።

19 እዚህ ላይ ጳውሎስ የኤፌሶንን አረማውያን ከእግዚአብሔር ሕዝብ (አይሁዳውያን) ጋር የአንድ አገር ዜጎች ሆናችኋል፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባሎች (ቤተ ክርስቲያን) ሆናችኋል ይላቸዋል። ዛሬም ቢሆን ጳውሎስ ለእኛ የሚሰጠን መልእክት ይህንኑ ነው። እኛም ራሳችን ብንሆን የውጭ አገር ሰዎች ወይም ባዕዳን ነበርን፤ እኛም ክርስቶስን የምናውቅ አልነበርንም፤ አሁን ግን በእርሱ በማመናችን የተነሣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባሎች ሆነናል። በመንግሥቱም የአገር ዜጋዎች ሆነናል (ሉቃ. 12፥32)።

20 በዚህ ጥቅስ ላይ ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ቤተሰብ ማለትም ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚናገረው በጣም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች አሉት። ቤተ ክርስቲያን የታነጸችው በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ነው። ይህም ማለት በአዲስ ኪዳን ሐዋርያትና በብሉይ ኪዳን ነቢያት ላይ ነው። በሌላ አነጋገር ቤተ ክርስቲያን የታነጸችው በብሉይና በአዲስ ኪዳን መሠረት ላይ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው። በቀላል አነጋገር ለቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህም ቃል (መሠረቱ) በሐዋርያትና በነቢያት የተጻፈልን ነው። በመቀጠልም ጳውሎስ «ለቤተ ክርስቲያን ዋናው የማዕዘን ራስ[13] ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ይላል። ይህን የመሰለ የማዕዘን ራስ ባይኖር ሕንፃው ሊፈርስና ሊወድቅ ይችላል።

21 የአይሁዳውያን ቤተ መቅደስ በኢየሩሳሌም የለም። በአሁኑ ጊዜ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቤተ ክርስቲያን ነች። ይህም ቤተ መቅደስ በአንድነት ተያይዞ ያለው በክርስቶስ ነው። ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን የማዕዘን ድንጋይ ብቻ ሳይሆን፥ የቤተክርስቲያን ራስም ነው።

22 እኛ አማኞች እንደ ድንጋይ የምንቆጠር ነን፤ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን የሠራውም በእኛ ነው። እኛ በአንድነት ሆነን አንድ ሕንፃ ማለትም አንድ ቤተ ክርስቲያን ሆነን ተሠርተናል። እርስበሳችን ተያይዘናል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እኛ ድንጋዮች ሆነን በተሠራንበት ቤተ መቅደስ ውስጥ ይኖራል (1ቆሮ. 3፥16፤ 1ጴጥ. 2፥5 እና. ማብራሪያውን ይመለከቷል)። እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን የሠራው ራሱ ሊኖርበት ስለፈለገ ነው።

ዛሬ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ምን ይመስላል? አባሎቹ በአንድነት ተጣምረዋልን? በቤተክርስቲያናችን ሰላም ይኖራልን? በአንድ ቤተሰብ ውስጥ እንደሚኖሩ ሰዎች እርስበርሳችን በፍቅር እንተያያለንን? ሌሎች ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ቢመለከቱ ምን ሊያዩ ይችላሉ? እግዚአብሔርስ ምን ሊያይ ይችላል?

ምዕራፍ 3

ለአረማውያን የተላከው፥ ሰባኪው ጳውሎስ (3፥1–13)

1–2 ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በሮም እስር ቤት ውስጥ ሆኖ ስለነበር ራሱን «እስረኛ» በማለት ይጠራል። «እስረኛነቴም ለእናንተ ለአረማውያን ነው» በማለት ለኤፌሶን ሰዎች ያስረዳቸዋል፤ ጳውሎስ ታስሮ የነበረው ለአረማውያን ይሰብክ ስለነበር ነው።

በሌላ መልኩ ጳውሎስ በእስር ቤት ቢሆንም ባይሆንም፥ የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ነበር። እርሱ በሁሉ ቦታና በሁሉ ጊዜ ኢየሱስን የሕይወቱ ገዢና ጌታ አድርጎታል።

የጳውሎስ ልዩ ሥራ ለአረማውያን መስበክ ሲሆን (የሐዋ. 22፥21፤ ሮሜ 15፥15–16)፤ ይህን ሥራ የሚሰራውም የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመመገብ በተቀበለው ልዩ ችሎታ ነበር (ቁ. 2)።

3 እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለተገለጠለት ልዩ ምስጢር ይናገራል። ቀደም ብሎም ቢሆን፥ በኤፌ. 1፥9–10 ላይ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በክርስቶስ አንድ እንደሚያደርግ ስለሚያስረዳው ምስጢር ጠቅሶአል። በምዕራፍ 2 ላይ ደግሞ አይሁዳውያንና አረማውያን በክርስቶስ እንዴት አንድ ሊሆኑ እንደቻሉ አስረድቶአል። ጳውሎስ ይህን ምስጢር ከሰው አልተማረውም፤ ይልቁንም እርሱ ስለዚህ ምስጢር ሊያውቅ የቻለው በቀጥታ ከእግዚአብሔር ስለተገለጠለት ነው።

4 የኤፌሶን ሰዎች፥ ከምዕራፍ 1–2 ካነበቡ በኋላ ጳውሎስ ይህ ምስጢር ምን እንደሆነ ማስተዋሉን ተረድተዋል። ምስጢሩም የክርስቶስ ምስጢር ነው። ይህም ክርስቶስ በሁሉ ነገር ላይ ራስ እንደሆነና (ኤፌ. 1፥22)፥ በክርስቶስም አንድ አካል ማለትም በቤተ ክርስቲያን አይሁዳውያንና አረማውያን አሁን አንድ እንደሆኑ የሚያስረዳ ነው (1ቆሮ. 12፥12–13፤ 27፤ ኤፌ. 2፥16–17፤ 3፥6)።

5 ይህ ምስጢር በሌሎች ዘመናት ለነበሩ ሰዎች እንዲያውቁት አልተደረገም ይህም ማለት ከክርስቶስ ዘመን በፊት ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች፥ ስለዚህ ምስጢር ምንም ዐይነት መገለጥ አልተሰጣቸውም፤ ክርስቶስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ብቻ ለእግዚአብሔር ቅዱሳን ሐዋርያትና ነቢያት[14] ምስጢሩ በሙሉ ተገለጠላቸው። ምስጢሩ የተገለጠላቸውም በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነበር።

6 እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ ምስጢሩ እንደገና ማብራሪያ ይሰጣል። አረማውያን አማኞች በአንድነት ወራሾች ሆነዋል፥ በአንድነት አባሎች ሆነዋል፥ ከእስራኤልም ጋር ማለትም ከአይሁዳውያን ጋር ርስት ተካፋዮች ሆነዋል (ኤፌ. 2፥19 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። አይሁዳውያንና አረማውያን አማኞች ከእንግዲህ በክርስቶስ አንድ ሆነዋልና በእግዚአብሔር ፊት ሁለቱም በእኩል ይታያሉ። ይህም ማለት በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅና ታናሽ ዘር፥ የበላይና የበታች ወይም ሀብታምና ድኻ በመሆን ላይ የተመሠረተ ምንም ልዩነት የለም። አይሁዳውያን በአስተሳሰባቸው፥ አረማውያን በዘራቸው ዝቅተኞች እንደሆኑና ራሳቸው ግን ከፍተኞች እንደሆኑ አድርገው ይገምቱ ነበር፤ አሁን ግን በክርስቶስ በዘር መበላለጥ የለም፤ ሁሉም አንድ ሆነዋል።

አረማውያን ከእስራኤል ጋር በአንድነት ወራሾች ሆነዋል። ይህም ማለት አረማውያን ከአይሁዳውያን ጋር በአንድነት የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ተደርገዋል። አሁን አረማውያን እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባው ቃል ኪዳን ተካፋዮች ናቸው። በዚያ ቃል ኪዳን መሠረት፥ አይሁዳውያን እግዚአብሔርን ማምለክና መታዘዝ ነበረባቸው። በበኩሉም እግዚአብሔር አይሁዳውያንን የራሱ ልዩ ሕዝብ ያደርጋቸው ነበር። አሁን ግን አይሁዳዊም ሆነ አረማዊ በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የእግዚአብሔር ልዩ ሕዝብ ሆኗል።

አረማውያንም የአንድ አካል ክፍሎች ሆነዋል፤ ይህም. ማለት አረማውያን አማኞች ከአይሁዳውያን አማኞች ጋር አንድ በመሆን የክርስቶስ አካል ክፍሎች ሆነዋል (1ቆሮ. 12፥27)።

---

[13] ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚጠቅሰው የማዕዘን ራስ ሁለት ግንቦች የሚገናኙበትን ማዕዘን የሚያገናኘውን የቆብ ድንጋይ ነው። ያለ እንደዚህ ዓይነቱ የቆብ ድንጋይ ግንቦቹ ይፈራርሳሉ።

[14] እነዚህ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ሳይሆኑ የአዲስ ኪዳን ነቢያት ናቸው።

አረማውያን በአንድነት የተስፋው ተካፋዮች ሆነዋል። ይህም ማለት በክርስቶስ በማመን የሚገኘው ተስፋ ተካፋዮች ሆነዋል። እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን አንድ አዳኝ እንደሚልክላቸው የተስፋ ቃል ገብቶላቸው ነበር። ነገር ግን አዳኝ የሆነው ክርስቶስ በመጨረሻ ወደ እነርሱ በመጣ ጊዜ ብዙ አይሁዳውያን አልተቀበሉትም። ስለዚህ እግዚአብሔር በክርስቶስ የአዳኝነት ሥራ አረማውያን በእምነት እንዲቀበሉት አደረገ። በዚህም መንገድ አረማውያን ይህን ደኅንነት በመቀበል የተስፋው ተካፋዮች ሊሆኑ ቻሉ።

7 ጳውሎስ በእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታና በእግዚአብሔር ኃይል ሥራ፥ የወንጌል አገልጋይ ሆነ። እኛም በክርስቶስ ያመንንና የምንታዘዘውም ሁሉ በእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል እንደ ጳውሎስ የወንጌል አገልጋዮች ሆነናል። አገልጋዮቹ እንድንሆንም እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ጸጋ ሰጥቶናል። ስለሆነም፥ እነዚህን ጥያቄዎች ለራሳችን ማቅረብ ይገባናል። «እኔ የማን አገልጋይ ነኝ? ከጊዜዬ አብዛኛውን ክፍል የማጠፋው ማንን በማገልገል ነው? ጌታዬን ክርስቶስንና የእርሱን ወንጌል ምን ያህል እወዳቸዋለሁ?»

8 ጳውሎስ ራሱን ከፍ ከፍ አላደረገም፤ ዛሬ በእኛ መካከል ቢገኝ ኖሮ «ከእናንተ መካከል መጨረሻ ከሆነው ሰው ይልቅ የማንስ ነኝ» ይል ነበር።

እግዚአብሔር ለጳውሎስ እንዲሠራ የሰጠው ልዩ አገልግሎት፤ ወሰን የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአረማውያን መስበክ ነበር። የክርስቶስ መንፈሳዊ ሀብቶች ወሰን የላቸውም። እነዚህ ወሰን የሌላቸው ባለጠግነቶች ጳውሎስ በኤፌ. 1፥3 ላይ ከገለጣቸው መንፈሳዊ በረከቶች ጋር ተመሳሳዮች ናቸው (ቆላ. 1፥24–27 ይመለከቷል)።

ከወዳጆቻችንና ከጎረቤቶቻችን ጋር በምንጫወትበት ጊዜ፥ ስለዚህ ወሰን ስለሌለው የክርስቶስ ባለጸግነት አውርተንላቸው እናውቃለንን? ስለ ርስቱ ክብር ባለጠግነትስ ነግረናቸው እናውቅለንን? (ኤፌ. 1፥18)። ወደር ስለሌለው ታላቅ ኃይሉስ አውርተንላቸዋለን? (ኤፌ. 1፥19)። እኛ ለራሳችንስ የእነዚህ ሀብቶች ወራሾች ሆነናልን? ወይስ በአንድ ትልቅ ግብዣ ላይ ተጠርቶ በጠረጴዛው ጥግ ላይ ወንበር ይዞ ከተቀመጠ በኋላ ምንም እንዳልተመገበው ሰው ነን?

የዓለም ሰዎች የሚጠፋ ሀብት ለማግኘት ይሯሯጣሉ፤ እኛ ግን ለዘላለም የሚኖረውን ሀብት አግኝተናል። ታዲያ ስለዚህ ሀብት ለሌሎች መንገር የለብንምን?

አንዳንድ ጊዜ ምንም ዐይነት መንፈሳዊ ሀብት እንደሌለን ሰዎች ሆነን እንታያለን። «ቤተ ክርስቲያናችን በጣም ደኻና ደካማ ነች፤ ታዲያ ምን ማድረግ እንችላለን» ብለን እንጠይቃለን። ደኻና ደካማ? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እያንዳንዱ ቤተክርስቶያን ወሰን የሌለውን የክርስቶስ ባለጠግነት ተቀብሎአል። ወደር የማይገኝለትን የክርስቶስ ኃይል ይዞአል። በቂ የሆነ መንፈሳዊ ሀብትና ኃይል ስላለን፥ ለሌሎች ማካፈል እንችላለን። ያለንና ልናካፍለው የምንችለው ነገር ወሰን የለውም።

ለሌሎች ማካፈል የሚገባን የክርስቶስ ሀብት ምንድን ነው? ጸጋውንና ስጦታዎቹን በመጨመር ብዙ መንፈሳዊ በረከቶችን ሰጥቶናል (ኤፌ. 1፥3)። የእግዚአብሔር ኃይል የሆነውን የደኅንነት ወንጌልም ጨምሮ ሰጥቶናል (1ቆሮ. 1፥18)። ከሁሉ በላይ ግን ማካፈል የሚገባን ራሱን ክርስቶስን ነው። እርሱ የመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ ማጠቃለያ ነው (ሮሜ 8፥32)።

9 ጳውሎስ በአንድ በኩል ለአረማውያን ወንጌልን የሚሰብክ ሲሆን፥ በሌላ በኩል ይህን ተሠውሮ የነበረውን ምስጢር ለመግለጥ በእግዚአብሔር የተሾመ ነበር። ከክርስቶስ ዘመን በፊት ይህ ምስጢር ተሠውሮ ኖሯል። አሁን ግን በመጨረሻ ተገለጠ (ቁ. 5)። ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው፥ ምስጢሩ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ጠቅልሎ በክርስቶስ ሥር የሚያደርገው መሆኑን የሚያሳይ ነው (ኤፌ. 1፥10)። ይህንንም ለማድረግ አንድ መንፈሳዊ ሕዝብ መፍጠር አስፈለገ፤ ማለትም በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ በማመን አባል ሊሆኑባት የሚችሉ ቤተ ክርስቲያንን ፈጠረ። ይህም እግዚአብሔር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የፈፀመው የዘላለም እቅዱ ነው (ቁ. 11)።

10 እግዚአብሔር ይህን ምስጢር ሲገልጥ ሐሳቡ ምን ነበር? ሐሳቡ በሰማይ ያሉት አለቆችና ባለሥልጣኖች ጥበቡን *በየመልኩ* እንዲያውቁ ለማድረግ ነው። እነዚህም አለቆችና ባለሥልጣኖች መላእክትንና ርኩሳን መናፍስትን የሚጨምሩ ናቸው (ኤፌ. 2፥2)።

ታዲያ እግዚአብሔር ለእነዚህ አለቆችና ባለሥልጣኖች እንዴት ጥበቡን ሊያሳያቸው ይችላል? ይህን የሚያደርገው በቤተ ክርስቲያን በኩል ነው። እስቲ አስቡት! በእየንዳንዱ ትንንሽ ቤተ ክርስቲያን በኩል እግዚአብሔር እጅግ ብዙ የሆነ ጥበቡን ለእነዚህ በሰማያዊ ስፍራ ለሚኖሩ አለቆችና ባለሥልጣናት ሲገልጥላቸው ማየት በጣም አስገራሚ ነገር ነው! በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ጥበብ ሊታይ የሚችለው በሰዎች ብቻ ሳይሆን፥ በመላእክትና በመናፍስት እንዲያውም በራሱ በሰይጣን ጭምር ነው። የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን የሰይጣንን ሥልጣን ድል ነሥታለች።

11–12 የእግዚአብሔር *ዘላለማዊ ዓላማ* ሰዎች ሁሉ አይሁዳውያንና አረማውያን በአንድነት፥ በድፍረት በፊቱ ቀርበው የቤተሰቡ ማለትም የቤተ ክርስቲያን አባሎች እንዲሆኑ ለማድረግ ነው (ዕብ. 4፥16፤ 10፥19–22 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

እስቲ ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን እናስብ፤ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማውን የሚፈጽምባት ስለሆነች ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ በጣም አስፈላጊ ናት። ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በመቀጠል በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነው፤ የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን መመሥረቷ ነው። የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ስለ ነገሥታት፥ ስለ ሚኒስተሮች፥ ስለ መኳንንቶችና ስለ ሌሎችም ዝና ስላተረፉ ሰዎች ጽፈዋል፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ[15] ዘጋቢዎች ግን እንደኛው ተራ ስለሆኑ ሰዎች ጽፈዋል።

የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ስለ ጦርነት፥ ስለ ሰላም ውሎች፥ ከዚያም መልሰው ማብቂያ ስለሌለው ጦርነት ይጽፋሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጸሐፊዎች ግን በክርስቶስ አሸናፊነት ላይ ስለተመሠረተው በክርስቶስና በሰይጣን መካከል ማለትም በክፋና በደግ መካከል ስለተደረገው ጦርነት ጽፈዋል። እጅግ በጣም ታላቅ ስለሆነውም «የሰላም ውል» በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን። ይህም የሰላም ውል በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረገው የእርቅ ውል ሲሆን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛነት የተፈጸመ ነው።

የዓለም ባለታሪኮች እንደ ፀሐይ ብቅ ጥልቅ ስለሚሉ መንግሥታት ይጽፋሉ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ፀሐፊዎች ግን ሁል ጊዜ ስለሚወጣውና ጨርሶ መጥለቅ ስለማያውቀው መንፈሳዊ መንግሥት ይጽፋሉ። ይህም መንግሥት ወሰን የለሽና ዓለምን በሙሉ የሚያዳርስ መንግሥት፥ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ነው።

13 ምንም እንኳ ጳውሎስ በእስር ቤት ቢሆንም፥ የኤፌሶን ሰዎች ተስፋ መቁረጥ የለባቸውም፤ ይልቁንም ክብራቸው ስለሆነው ወሰን ስለማይገኝለት ስለ ክርስቶስ ብልጥግና ዘወትር ማሰብ ይገባቸዋል።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ያቀረበው ጸሎት (3፥14–21)

14–15 በሰማይና በምድር ያለ ቤተሰብ ሁሉ፥ ይኸውም አጠቃላይ የአማኞች ቤተሰብ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ስሟን የምታገኘው ከእግዚአብሔር አብ ነው። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተሰብ በመሆን የወሰደችው የእግዚአብሔርን ስም ነው።

ቤተ ስክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተሰብ በመሆንዋ፥ ጳውሎስ ለቤተሰቡ አባት ለእግዚአብሔር አብ ጸሎት ያቀርባል። የጳውሎስም ጸሎት እግዚአብሔር ኤፌሶናውያንን በመንፈሱ ውስጣዊ ሰውነታቸውን እንዲያጠነክርላቸውና (ቁ. 16) በእምነትም ክርስቶስ በልባቸው እንዲኖር እንዲያደርግላቸው ነው (ቁ. 17)። በእርግጥም ይህን መልእክት የምናነብ ሁሉ መልእክቱ የተጻፈው ለኤፌሶን

[15] መጽሐፍ ቅዱስ የሕግና የነቢያት መጽሐፍ ብቻ እንዳልሆነ ማስታወስ አለብን፤ ነገር ግን የታሪክ መጽሐፍም ነው፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው ታሪክ በፍጹም ትክክል ነው።

ሰዎች ብቻ ሳይሆን፥ ለእኛም ጭምር እንደሆነ ማሰብ ይኖርብናል።

16 እዚህ ላይ ጳውሎስ የሚጸልየው ስለ መንፈሳዊ ጥንካሬ ነው። ይህ ዓይነት ጥንካሬ በሰው ልብ ውስጥ ማለትም በውስጣዊ ሰውነቱ የሚገለጥ ሲሆን፥ እርሱም ሊገኝ የሚችለው በእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው። ይህ ጥንካሬ (ኃይል) ጳውሎስ ከዚህ በፊት በምዕራፍ 1፥19 ላይ የጠቀሰው ታላቅ ኃይል ሲሆን፤ ይህን ኃይል ጳውሎስ ራሱ ባለማቋረጥ ተለማምዶታል (ፊል. 4፥13)።

17 በሁለተኛ ደረጃ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች፥ ክርስቶስ (የክርስቶስ መንፈስ ማለትም መንፈስ ቅዱስ) በልባቸው እንዲኖር ጸልዮላቸዋል። ክርስቶስ በልባችን ሲኖር በይበልጥ እርሱን እየመሰልን እንሄዳለን፤ በውስጣችን በሚኖር የክርስቶስ መንፈስ ልባችን በፍቅሩ እየተሞላ ይሄዳል (ሮሜ 5፥5 ይመለከቷል)።

18 ክርስቶስ በእኛ ውስጥ መኖር ሲጀምር በፍቅር ልንመሠረትና ሥር ልንሰድ፤ ሥሮቹ በፍቅር ላይ እንደተተከሉ ዛፍ ልንሆን እንችላለን። ወይም ደግሞ መሠረቱ በፍቅር ላይ እንደተጣለ ቤት እንሆናለን። ጳውሎስ የክርስቶስ ፍቅር ስፋቱና ርዝመቱ፥ ቁመቱና ጥልቀቱ ምን ይህል እንደሆነ ማስተዋል ይችሉ ዘንድ፥ ለኤፌሶን ሰዎች ጸልዮላቸዋል። የክርስቶስ ፍቅር ሰዎችን ሁሉ ለማቀፍ እስከሚችል ድረስ በጣም ሰፊ ነው። የእርሱ ፍቅር በጣም ረዥም ከመሆኑ የተነሣ ለዘላለም የሚኖር ነው። የእርሱ ፍቅር ዝቅተኛ ወደሆነው ኃጢአተኛ እስከሚደርስ በጣም ጥልቅ ነው። ኃጢአተኛውን መንግሥተ ሰማይ እስከሚያደረስ ድረስ እጅግ ወደ ላይ የመጠቀ ነው።

መስቀል የክርስቶስ ፍቅር ታላቅ ምልክት ነው። ለምሳሌ የመስቀሉ አግዳሚ ቅርንጫፍ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ይደርሳል፤ የመስቀሉ ምሰሶ ከምድር እስከ ሰማይ ይደርሳል። የክርስቶስ ፍቅር የትም ቦታ ያሉትን ሰዎች እስከሚደርስ ድረስ እጅግ ታላቅ ነው።

19 ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የሚጸልይላቸው፤ ይህን ታላቅ የሆነውን የክርስቶስ ፍቅር ማስተዋል እንዲችሉ ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን ይህን ፍቅር ከማወቃቸው የተነሣ በሕይወታቸው እንዲለማመዱት ጭምር ነው። የክርስቶስ ፍቅር (የእግዚአብሔር ፍቅር) እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ *ለማወቅ የሚያዳግት* ነው። ይሁን እንጂ፥ እያንዳንዳችን ይህን ፍቅር በልባችን ልንለማመደው እንችላለን፤ ከተለማመድነውም በኋላ *በእግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ለመምላት* እንችላለን። በእግዚአብሔር ፍጹም ሙላት መሞላት ማለት ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ፍጹም ሙላት፤ በሰማያዊ ስፍራ ያሉትን መንፈሳዊ በረከቶች (ኤፌ 1፥3)፥ የርስቱን ክብር ባለጠግነት (ኤፌ. 1፥18)፥ ወደር የሌለውን የክርስቶስ ኃይል (ኤፌ. 1፥19) ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነትና (ቁ. 8) በመንፈስ ቅዱስ በልባችን ያፈሰውን ታላቅ ፍቅሩን ሮሜ. 5፥5 ያካትታል። ክርስቶስ በእምነት በልባችን የሚኖር ከሆነ፤ ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ሙላት የራሳችን ይሆናል።

ቤተ ክርስቲያናችንና እያንዳንዳችንም በዚህ ፍጹም በሆነው በእግዚአብሔር ሙላት ዘወትር እየተሞላን እንድንኖር የማያቋርጥ ጸሎታችን ይሁን። ጸሎታችንን ትንንሽ ነገሮችን በማግኘት አንወስነው፤ ይልቁንም እንደ ጳውሎስ ታላላቅ ነገሮችን ለማግኘት እንጸልይ፤ *የእግዚአብሔርን ፍጹም ሙላት ለማግኘት መጸለይ እንደምንችል አንዘንጋ*።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎችና ለእኛም ጭምር ምን ዐይነት አስደናቂ ጸሎት እንደጸለየ እንመልከት። ኃይል፥ ፍቅር፥ እውቀት እንዲያገኙና ፍጹም በሆነው በእግዚአብሔር ሙላት እንዲሞሉ ጸለየላቸው። ይህን የመሰለ ጸሎት እግዚአብሔር ይመልሳልን? እግዚአብሔር ይህን የመሰለ ጸሎት ለመፈጸም የሚያበቃው ኃይል አለውን? በእርግጥ አለው! (ቁ. 20 ይመለከቷል)።

20–21 እግዚአብሔር እኛ የምንጠይቀውን ሁሉ ለመፈጸም የሚያስችል ታላቅ ኃይል አለው። ይህም ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር እኛ ከምንለምነውና ከምናስበው በላይ የሆነውን ነገር ለማድረግ የሚያስችል ኃይል አለው። ይህም የእግዚአብሔር ኃይል፥ በእኛ ውስጥ *ሥራውን ይሠራል* (ቁ. 20)። ልክ የእግዚአብሔር ፍቅር ከእኛ ማስተዋል በላይ እንደሆነው ሁሉ (ቁ. 19)፥ የእግዚአብሔር ኃይል እኛም ለመገመት ከምንችለው በላይ ነው። መጨረሻ የሌለው ፍቅርና ወሰን የማይገኝለት ኃይል አለው ማለት ነው። አምላካችን ምን ያህል ታላቅ ነው? መጨረሻ የሌለው እጅግ ብዙ ምስጋና የሚገባው አምላክ ነው፤ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያንና በኢየሱስ ክርስቶስ በዘመናት ሁሉ ለዘላለም ክብር ይሁን!

ምዕራፍ 4

በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለው ኅብረት (4፥1–16)

1 በዚህ መልእክት በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች፥ ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ (ኤፌ. 3፥11)፥ ስለ እንዱ አዲስ ሰው ማለትም እግዚአብሔር ስለመሠረተው ቤተ ክርስቲያንና (ኤፌ. 2፥15)፥ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ስለመጠራታችን (ኤፌ፡ 1፥5) ጽፍዋል። አሁን ደግሞ በመጨረሻዎቹ ሦስት ምዕራፎች፥ በዕለታዊ ኑሮአችን ምን ማድረግ እንደሚገባን ይጽፋል። የተጠራነው የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን ስለሆነ፥ የእግዚአብሔር ልጆች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ማወቅ ይገባናል። የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን፥ ልክ እንደ እግዚአብሔር ልጆች መኖር አለበን።

ስለሆነም በ4፥1 ላይ ጳውሎስ፥ *መጠራታችሁን የሚያስመሰግን ኑሮ ኣሳዩ* በማለት ይመክረናል። እግዚአብሔር የጠራን ልጆቹ ሊያደርገን ስለሆነ፥ እኛም በኑሮአችን ይህንን ማሳየት አለብን (ፊል. 1፥27፤ ቆላ. 1፥10)። ደግሞም ከቁ. 2–16 ባለው ክፍል አንድ አዲስ ሕዝብ ማለትም የአንድ ቤተሰብ (ቤተክርስቲያን) አባሎች ለመሆን እንደተጠራን ጳውሎስ ያስታውሰናል። ይህን ጥሪያችንን ለማስመስገን በኅብረታችን መጽናት ያስፈልገናል።

2 እኛ ክርስቲያኖች እርስበርሳችን ኅብረት ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው? በመጀመሪያ ትሑት[16] መሆን ያስፈልገናል። በየቤተክርስቲያናችን መከፋፈል የሚመጣው በምን ምክንያት ነው? መከፋፈል የሚመጣው ብዙውን ጊዜ በትዕቢት ምክንያት ነው። ከትዕቢት ሁለት መጥፎ ነገሮች ይፈልቃሉ። በመጀመሪያ ከትዕቢታችን የተነሣ አንዳንዶቻችን መሪዎች ለመሆን እንፈልጋለን፤ መሪነት ሳይሰጠን ሲቀር ተቆጥተን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈል እንዲፈጠር እናደርጋለን። በሁለተኛ ደረጃ፥ አንድ ሰው በአንድ መንገድ ወይም በሌላ ሊቃወመን ወይም ሊከደን ቢነሣ ክብራችን ተነካ በማለት በዚያ ሰው ላይ ተቆጥተን ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ እናቆማለን። በዚህ ሁኔታ ጉዳት የሚደርስብን ከትዕቢታችን የተነሣና ትሕትና ስለሚጎድለን ነው። ስለዚህ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኅብረት እንዲኖርና እርስበርሳችንም በሰላም መኖር እንድንችል በመጀመሪያ ማግኘት የሚገባን ነገር ትሕትና እንደሆነ ያሳስበናል።

አንዳንድ ሰዎች ትሑት የሚሆን ሰው ደካማ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። ነገር ግን እንዲህ ዐይነቱ አሳብ ፍጹም ስህተት ነው። እንዲያውም ትሑት ሰው በጣም ብርቱ ነው። የራሱም ገዥ ነው። ይሁን እንጂ፥ በደስታ ራሱን ለሌሎች አገልጋይ ያደርጋል።

እኛ ትሑት መሆናችንን እንዴት ልናስረዳ እንችላለን? የራሳችንንስ ትሕትና በምን እንፈትነዋለን? በምንጸልይበት ጊዜ ራሳችንን (ኃጢኣተኞች) ብለን መጥራታችን ቀላል ነው። ነገር ግን ይህ ትሑት መሆናችንን እንድንፈተን አያስችለንም። ፈተና ሊሆን የሚችለው ሌላ ሰው (አንተ ኃጢአተኛ ነህ) ብሎ ሲጠራን በተለይ ሌሎች ሰዎች ፊት እንዲህ ብሎ ሲጠራን ምን እንመልሳለን? የሚለው ጥያቄ ነው። በደስታና በጸጋ እንቀበለዋለንን? የማንቀበለው ከሆነ ትሑቶች አይደለንም፤ ፈተናውንም ወድቀናል ማለት ነው።

በቤተክርስቲያን፥ ኅብረት ጠንክሮ እንዲቆይ የሚያስፈልገው ሁለተኛው ነገር ትዕግሥት ነው። እርስበርሳችን በኅብረት ለመኖር፥ እርስበርሳችን ትዕግሥት ማድረግ

---

[16] ጳውሎስ ትሑትና ጨዋ መሆን እንዳለብን ይነግረናል። ጨዋነት ብዙ ጊዜ አብሮ የሚሄደው ከትሕትና ጋር ነው፤ የመንፈስ ቅዱስ ስምንተኛው ፍሬ ጨዋነት ነው ገላ. 5፥23። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ስምንተኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ፍሬ ከጨዋነት ይልቅ ትሕትና ብለውታል።

ይኖርብናል። እያንዳንዳችን ስሕተትና ድካም ስለአለብን፤ ሌሎች የእኛን ስሕተት እንዲታገሡን እንፈልጋለን። ነቀፌታ ቢኖርብንም ሌሎች ከነነውራችን እንዲቀበሉን እንሻለን። እንደዚህ ከሆነ እኛም ሌሎችን መታገሥና ከነ ነውራቸው ልንቀበላቸው መሞከር ይኖርብናል። ከትዕቢት ቀጥሎ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለያየት የሚያመጣ ሁለተኛው ዋና ነገር እርስበርስ መከራከርና መሰዳደብ ነው። ሰይጣን ኅብረታችንን ለማጥፋት ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ዋናዎቹ እነዚህ ናቸው። በእኛ ላይ ክፉ ነገር እንኳ ቢናገሩ ሌሎችን መታገሥ ይኖርብናል። ልዩ ልዩ ተቃውሞዎችን ልናሸንፍ የምንችለው በትዕግሥት ነው።

ኅብረትን ለማጠንከር ከሚረዱን ነገሮች ሦስተኛው ፍቅር ነው። ልክ ክርስቶስ እኛን በፍቅር እንደታገሰን ሁሉ፥ እኛም እርስበርሳችን በፍቅር ልንታገሥ ያስፈልገናል። ክርስቶስ ይቅር እንዳለን ሁሉ፥ እኛም እርስበርሳችን ይቅር ልንባባል ይገባናል (ኤፌ. 4፥32)።

እንግዲህ ኅብረታችን ጠንክሮ እንዲጸና ሦስት ነገሮች ያስፈልጉናል። እነሱም ትሕትና፥ ትዕግሥትና ፍቅር ናቸው። አማኞች በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ እንዳሉ ድንጋዮች መሆናቸውን ቀደም ሲል ጳውሎስ ጽፎልናል (ኤፌ፣ 2፥2)። እኛ ድንጋዮች ከሆንን እንደ ሲሚንቶ በአንድነት የሚያያይዙን ትሕትና፥ ትዕግሥትና ፍቅር ናቸው (ቆላ. 3፥12–14 ይመለከቷል)።

3 ኅብረታችን ከመንፈሱ ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አለ (ኤፌ፣ 2፥22)። ስለዚህ አንድ የሚያደርገን ይኸው መንፈስ ነው፤ አንድነታችንም መንፈሳዊ አንድነት ነው። ሥራችንና ጠባያችን እንዲሁም ልምዳችን ልዩ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን በመንፈሱ በውስጥ በልባችንና በአእምሮአችን በፍጹም አንድ መሆን ይገባናል።

እርግጥ ነው በቅጽበት አንድ መሆን አይቻልም፤ በአንድነት ለመጽናት በየበኩላችን ብዙ ሥራ የጠይቀናል። ሰይጣን ሁል ጊዜ እንድንለያይ ይጥራል። አንድነታችንን ለመጠበቅ እኛም በተቻለ መጠን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል (1ቆሮ. 1፥10 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

በአንድነት ተጣምረን ለመኖር በሰላም ማሠሪያ እርስበርሳችን መያያዝ ይገባናል። ሰላማችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ኤፌ፣ 2፥14)። እርሱ በአንድነት ያያይዘናል፤ ስለዚህ በክርስቶስ እርስበርሳችን ተያይዘን እንኑር።

4 እኛ የተጠራነው *ለአንድ ተስፋ ነው።* ተስፋችንም፥ የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን መጠን በሰማይ ርስትን መውረስና ከእርሱ ጋር ለዘላለም አብረን መኖር ነው። የእያንዳንዱ አማኝ ተስፋ ይህ ነው። አንድ መንፈስ አለ አንድም አካል። በሁላችንም አንድ መንፈስ ስላለ አንድ አካል ሆነናል። በመጀመሪያ አንድ መንፈስ አለ፤ ቀጥሎም በመንፈሱ በኩል አንድ አካል አለ (1ቆሮ. 12፥13 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

5 አንድ ጌታ ስላለን አንድ እምነት አለን። እምነታችንም በአንዱ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አንድ ጌታ ስላለንም አንድ ጥምቀት አለን፤ የምንጠመቀውም በአንዱ ጌታ ስም ነው።

6 አንድ እውነተኛ አምላክ አለ (1ቆሮ. 8፥5–6 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። እግዚአብሔር አባታችን ነው፤ ከአንድም አባት አንድ ቤተሰብ ማለትም አንድ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም መካከል ፍጹም የሆነ አንድነት አለ። እግዚአብሔር አንድ ስለሆነ በቤተክርስቲያንም ውስጥ አንድነት ሊኖር ይገባል።

እውነተኛይቱ መንፈሳዊ ቤተ ክርስቲያን ልትከፋፈል አትችልም። ይሁን እንጂ፥ ወደራሳችን ቤተ ክርስቲያን ስንመለከት መለያየት መኖሩን እንረዳለን። በአንድ በኩል ቤተክርስቲያናችን መለያየት የሌለባት አንድ መንፈሳዊ አካል እንደሆነች እናያለን። በሌላ በኩል ስንመለከታት የመለያየት መልክ እንዳላት እናያለን፤ ታዲያ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

አባትና እናት እንዲሁም ልጆቻቸው ያሉበትን አንድ ተራ ቤተሰብ በምሳሌ ወስደን ስለዚህ ጉዳይ ልንረዳ እንችላለን። አባትና እናት ይሩታሉ እንበል፤ ልጆችም እርስበርስ በመደባደብ እያንዳንዱ የራሱን መንገድ ይዞ ይሄዳል እንበል፤ በዚህም ምክንያት ያ ቤተሰብ ጨርሶ ይለያያል። ታዲያ አሁን እነርሱ አንድ ቤተሰብ ናቸው ወይስ አይደሉም? እነዚያ ልጆችስ አሁንም የእናታቸውና የአባታቸው ልጆች ናቸውን? አዎ! በእርግጥም የእነርሱ ልጆች ናቸው፤ ያምቤተሰብ አሁንም አንድ ቤተሰብ ነው፤ ይሁን እንጂ ተለያይተዋል።

የእኛም ቤተክርስቲያን እንደ ሰብአዊ ቤተሰብ ነው፤ ዘወትር ጠብና መለያየት ቢኖርም እኛ ግን አንድ ቤተክርስቲያን ነን። አንዳንድ ጊዜ በአንድ ማኅበረ ምዕመናን መካከል መለያየት ይፈጠራል፤ በተለያዩ ማኅበረ ምዕመናን መካከልም እንዲሁም መለያየት ሊፈጠር ይችላል። አንዳንድ ጊዜም በአንድ ቦታ የሚገኙ አብያተክርስቲያናት በሌላ ቦታ የሚገኙትን አብያተክርስቲያናት መቀበል ያስቸግራቸዋል። ምንም ዐይነት መለያየት ቢፈጠር በነዚህ በተለያየ ሁኔታ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አንድ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ናቸው።

ስለሆነም ልክ የአንድ ሰብአዊ ቤተሰብ አባል ማድረግ እንደሚገባው ሁሉ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባሎችም በሰላም ተሳስረው ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን አንድነት ለመጠበቅ መትጋት ይኖርባቸዋል (ቁ. 3)። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ መከፋፈል ሲኖር በሰብአዊ አባት ላይ ጭንቅና ሐዘን እንደሚያስከትልበት ሁሉ፥ በቤተክርስቲያንም ውስጥ የሚኖረው መከፋፈል በሰማይ ባለው አባታችን ላይ ታላቅ ሐዘን ያስከትልበታል። ምንጊዜም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልን የሚያመጣ ሰይጣን ነው። ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን አባሎች መካከል ትሕትና፥ ትዕግሥትና ፍቅር ጎድሎ ሲያገኝ መለያየትን ለመፍጠር ምቹ አጋጣሚ ያገኛል።

በተለያየ ስፍራ የተለያዩ ማኅበረ ምዕመናን መመሥረት ትክክለኛ አሠራር ነው። እያንዳንዱ ወረዳ የራሱ የሆነ ቤተ ክርስቲያን ሊኖረው ይገባል። ከተማው ትልቅ ከሆነም በተለያየ ስፍራ ልዩ ልዩ ምኅበረ ምዕመናን ሊኖሩ ያስፈልጋል። በዚህ ዐይነት አማኞች በአጠገባቸው በሚገኝ በአንድ ቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን ሊያመልኩ ይችላሉ። በአንድ አካባቢ የሚገኙ የተለያዩ አብያተክርስቲያናት አንዳንድ አጋጣሚ ሁኔታዎችን በመጠቀም በአንድነት ሊያገለግሉ ይችላሉ። ይህን ሊያደርጉ የሚችሉት መለያየትንና ቅራኔን በመካከላቸው ሲያርቁ ብቻ ነው።

በአንድ አካባቢ የሚገኙ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ማኅበረ ምዕመናን እርስበርሳቸው ኅብረት ወይም ተራድኦ ማድረግ ሲያቅሙ፥ በመካከላቸው ልዩነት ወይም መከፋፈል ተፈጥሮአል፤ በነገሩም እግዚአብሔርን አሳዝነነዋል። እግዚአብሔር ይቅር ይበለን፥ ከኃጢአታችንም ያንጻን፤ ይፈውሰንም!

7 ነገር ግን ክርስቶስ *ለመስጠት በወሰነው መጠን* ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል። ጸጋ የሚለውን ቃል ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይጠቀምበታል። ጸጋ የሚለው ቃል የተለመደ ትርጉሙ በኤፌ. 2፥8 ላይ እንደተጠቀሰው “የመዳን ጸጋ” ሲሆን፥ ይህንንም ጸጋ እያንዳንዱ አማኝ በእኩል ደረጃ የሚቀበለው ነው። በሁለተኛ ደረጃ ጸጋ ለሚለው ቃል የተሰጠው ትርጉም “የጸጋ ስጦታዎች” በመባል የሚታወቀው ሲሆን (ቁ. 8)፤ ይህም ጸጋ እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዱ አማኝ ይሰጠዋል። ይህን ጸጋ አማኞች ሁሉ በኩል ደረጃ የሚቀበሉት አይደለም። በዚህ ላይ ስጦታዎች በመባል የተጠቀሱት የተለዩ ክህሎቶችና ችሎታዎች ሲሆኑ፤ እነዚህም የመስበክና የማስተማር ስጦታ፥ የመፈወስ ስጦታ፥ የማስተናገድ ስጦታና የመሳሰሉትን ስጦታዎች ናቸው። እኛ ሌሎችን ማገልገል ይቻለን ዘንድ ክርስቶስ እነዚህን ስጦታዎች ለእያንዳንዳችን ይሰጠናል።

«በመዳን ጸጋ” ምክንያት እኛ አማኞች የእግዚአብሔር ልጆች የመሆንን ሥልጣን በእኩል ደረጃ አግኝተናል። «በጸጋ ስጦታዎች” ወይም «በአገልግሎት ጸጋ” ምክንያት ለእያንዳንዳችን የተለያየ ስጦታ ወይም የተለያየ ሥራ ተሰጥቶናል። ይህም በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙ ልጆች የተለያየ ስጦታና ችሎታ እንደሚኖራቸው ነው።

እነዚህን ሁለት የተለያዩ ጸጋዎች ማለትም «የመዳን ጸጋ» እና «የጸጋ ስጦታዎች» ለእኛ የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው። በዚህም ከስጦታዎች ሁሉ የሚበልጠውን ስጦታ ማለትም ራሱን መንፈስ ቅዱስን ክርስቶስ እንደሚሰጠን እናያለን፤ ምክንያቱም ሌሎች ስጦታዎች ሁሉ የሚከፋፈሉት

በመንፈስ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር ክርስቶስን ሰጠን፥ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን ሰጠን፤ ሦስቱም በአንድነት፥ ማለትም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሌሎቹን እነዚህን ስጦታዎች ሁሉ ይሰጡናል።

8 እዚህ ላይ ጳውሎስ ከመዝ. 68፥18 ይጠቅሳል፤ በዚህ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር በመዝሙር ጸሐፊው በኩል ክርስቶስ ወደ ሰማይ እንደሚያርግ ትንቢት ይናገራል።

ክርስቶስ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ ብዙ ምርኮኞችን ይዞ ሄደ። ይህም ማለት ከዚህ በፊት እኛን ምርኮኞች አድርገው ከነበሩት ብዙዎቹን ነገሮች ክርስቶስ ጠቅልሎ ምርኮኞች አደረጋቸው። ከእነርሱም መካከል ኃጢአት፥ ሞትና ሰይጣን ይገኙባቸዋል። ክርስቶስ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ድል ነስቶ ምርኮኞች አደረጋቸው። በመንግሥተ ሰማይም በደረሰ ጊዜ፥ ለሰዎች ሁሉ ማለትም ለቤተ ክርስቲያን *ስጦታን ሰጠ።*

9–10 ክርስቶስ በሞተ ጊዜ በመጀመሪያ ወደ ምድር በታች ወርደ (ቁ. 9)፥ ከሦስት ቀን በኋላም ከሰማያት ሁሉ በላይ ወጣ (ቁ. 10)። በዚያም በሰማይና በምድር ባሉት ነገሮች ሁሉ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ይገዛል (ኤፌ. 1፥22–23)።

11–12 በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ጳውሎስ ስለ አምስት ስጦታዎች ወይም የሥራ ማዕረጎች ይናገራል። እነርሱንም ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተለያዩ ግለሰቦች ይሰጣቸዋል። ለአንዳንዶች ሐዋሪያ የመሆን የሥራ ማዕረግ ሰጠ፤ ለሌሎች ነቢያት የመሆን፥ ለአንዳንዶች ወንጌላዊያን የመሆን፥ ለሌሎች መጋቢዎችና መምህራን የመሆን የሥራ ማዕረግ ሰጠ። በእርግጥ ከነዚህ ከአምስቱ በላይ የበዙ ስጦታዎች አሉ። እነዚህ ግን ለምሳሌ ያህል የተወሰዱ ናቸው (1ቆሮ. 12፥27–28፤ ሮሜ 12፥4–8 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ነገር ግን ጳውሎስ የጠቀሳቸው እነዚህ አምስት የሥራ ማዕረጎች ለቤተ ክርስቲያን በጣም አስፈላጊዎች ናቸው።

እዚህ የተዘረዘሩት አምስት ስጦታዎች አምስት የተለያዩ መሪዎችን የሚወክሉ ናቸው። እነርሱንም ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሠርቱና እንዲገነቡ ክርስቶስ መርጠ የሚሰጣቸው ናቸው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እነዚህ አምስት ስጦታዎች በ1ቆሮ. 12፥7–10 ከተጠቀሱት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ጋር ምንም ዝምድና የላቸውም ይላሉ። ሆኖም ዝምድና ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ስጦታዎችና የሥራ ማዕረጎች ሁሉ የሚሰጡት በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ነው። ሁሉም የሚሰጡት ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ወይም ለማሳደግ ነው።

እዚህ ላይ ጥያቄ ሊነሣ ችላል፤ በዚህ ቦታ የተጠቀሱት ስጦታዎች የተፈጥሮ ስጦታዎች ወይም ስንወለድ ጀምሮ የተሰጡን ስጦታዎች ናቸውን? ወይስ ከተፈጥሮ ስጦታዎች በላይ ከተወለድን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጡን ናቸው? መልሱ እነዚህ ስጦታዎች የተፈጥሮና ከተፈጥሮም በላይ የሆነ ክፍል አላቸው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው በሚወለድበት ጊዜ የተፈጥሮ ስጦታዎችና ችሎታዎች ሰጥቶአል። ይሁን እንጂ፥ አንድ ሰው ክርስቲያን በሚሆንበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእነዚያ የተፈጥሮ ስጦታዎች መጠቀም ይጀምራል። በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እነዚያን ስጦታዎች ወስዶ ያሳድጋቸዋል፤ ያጠራቸዋል። ለእግዚአብሔር አገልግሎት ይውሉም ዘንድ ይቀድሳቸዋልም።

ይሁን እንጂ፥ ሌሎች ስጦታዎችም አሉ፤ በተለይ በ1ቆሮ. 12፥8–10 የተጠቀሱት ከፍጥረታዊ ችሎታዎች በላይ የሆኑና አንድ ሰው ክርስቲያን ከሆነ በኋላ የሚሰጡ ናቸው (1ቆሮ. 12፥7–11 እና ማብራሪያውንና ከአስተምህሮ ዳሰሳው፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚለውን ይመለከቷል)።

እነዚህ ስጦታዎች የሚሰጡት ለምንድነው? ስጦታዎቹ የሚሰጡት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት እንዲዘጋጁ ለማድረግ ነው (ቁ. 12)። በዚህም መንገድ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን ትታነጻለች። እነዚህ ስጦታዎች ከሁሉ በፊት ለራሳችን የግል ጥቅም እንድናውላቸው አይሰጡንም። ይልቁንም እነዚህን ስጦታዎች የምንቀበለው ቤተክርስቲያንን እንድናንጽና ለጋራ ጥቅም ነው (1ቆሮ. 12፥7)። እንዚህ ስጦታዎች ለእኛ የሚሰጡትም ሌሎችን ለማገልገል እንድንጠቀምባቸው ነው። ለምሳሌ አንድ መጋቢ ለራሱ ቤተክርስቲያን የበላይ ገዥ ወይም ባለሥልጣን ነው ማለት አይደለም። ይልቁንም ለቤተክርስቲያኒቱ አገልጋይዋ ነው። አንድ መምህርም የተማሪዎቹ የበላይ ገዥ ሳይሆን፥ ይልቁንም አገልጋያቸው ነው። ለዚህም ክርስቶስ ጥሩ ምሳሌያችን ነው፤ እርሱ ምንም እንኳን ጌታችን ቢሆንም ወደ መሬት የወረደው ሊያገለግል እንጂ ሊገለገል አይደለም (ማር. 10፥43–45 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

የተቀበልነውን ስጦታ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የማንጠቀምበት ከሆነ፥ ስጦታውን ያለ ቦታው አውለነዋል ማለት ነው፤ በዚህም እግዚአብሔርን አሳዝነነዋል።

13 በዚህ ጥቅስ የምንመለከተው እነዚህ ስጦታዎች ለቤተ ምርስቲያን ያላቸውን ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎችን ነው። የመጀመሪያው ዓላማ እኛ እያንዳንዳችን የቤተክርስቲያኒቱ አባሎች በእምነትና የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ ወደ ሙሉ አንድነት መድረሳችን ነው። ሁለተኛው ዓላማ ክርስቶስ ፍጹምና ሙሉ ሰው እንደሆነው እኛም ሙሉ ሰው እንድንሆን ነው። ይህ ሁለተኛው ግብ እግዚአብሔር ለልጆቹ ለእያንዳንዳቸው የመደበላቸው የመጨረሻውና ታላቁ ግብ ነው። ኢየሱስን እስክንመስል ድረስ ፍጹም ሆኖ መገኘት የመጨረሻው የሕይወታችን ዓላማ ነው (ሮሜ 8፥29 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

በዚህ ሕይወታችን የቱንም ያህል ብንጣጣር ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙሉነት ለመድረስ አንችልም። ነገር ግን ዘወትር ባለማቋረጥ እያደግን እንሄዳለን። ምንም እንኳን በዚህ ምድር ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ለመድረስ ባንችልም፥ ወደዚያ ሙላት ለመድረስ መጣጣር ያስፈልገናል። ዘወትር እየጨመርን ማደግ ይኖርብናል፤ በመንፈሳዊ ሕይወት ዘወትር ሕፃናት መሆን አይገባንም (ቁ. 14)።

14 ልጆች በዓላማ የጸኑ አይደሉም፤ የሚሰሙትን ሁሉ ያምናሉ፤ በቀላሉም ይታለላሉ። በነፋስ ወዲህና ወዲያ እንደሚገፉ ቅጠሎች ናቸው። ጳውሎስ «በአዕምሮአቸው እንዳልበሰሉ ሕፃናት አትሁኑ»[17] በማለት የሚመክረን ለዚህ ነው።

15 *እውነት ጽኑ ያደርገናል፤ ይሁን እንጂ፥ እውነት በፍቅር ሊነገር ይገባል።* አንዳንድ ሰዎች እውነትን ያለፍቅር ይናገራሉ፤ እንደዚህ ዐይነት ሰዎች የጠብ ምክንያት ስለሚሆኑ ቤተ ክርስቲያንን ይከፋፍላሉ። ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ ከዚህ ተቃራኒ የሆነውን ስሕተት ይፈጽማሉ። እነርሱ የሚያምኑት «እውነት የፍቅርን ያህል አስፈላጊ አይደለም» የሚለውን አሳብ ነው። ከዚህም የተነሣ የሌላውን ሰው ስሜት ላለመጉዳት ሲሉ እውነትን ከመናገር መቆጠብ ይፈልጋሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ እውነትና ፍቅር በእኩል ደረጃ አስፈላጊዎች ናቸው። ፍቅር የሌለው እውነት በጣም ጠንካራ ሲሆን፤ ፍቅር ያለ እውነት ደግሞ በጣም ለስላሳ ነው። በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ እውነትም ፍቅርም የሚገኙ ከሆነ ያች ቤተ ክርስቲያንና አባልዎችዋ በክርስቶስ ውስጥ ለማደግ ይችላሉ።

አንዳንድ ሰዎች ሌሎችን ላለመጉዳት ሲባል አንዳንድ ጊዜ ትንንሽ ውሸቶችን መናገር አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አላቸው። ነገር ግን ይህ እምነት ትክክል አይደለም፤ ስለ አንድ ጎጂ ነገር ምንም ሳይናገሩ ዝም ማለት ይቻላል፤ ስለ እርሱ መናገር ካለብን ግን እውነቱን ብቻ መናገር ይገባናል።

16 ጳውሎስ እዚህ ላይ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ከአንድ አካል ጋር ያወዳድራል፤ የአካሉም ራስ ክርስቶስ እንድሆነ ይናገራል። የአካሉንም "ብልቶች" በሙሉ ራስ የሆነው ክርስቶስ ይቆጣጥራቸዋል (ቁ. 15)። ቤተ ክርስቲያን የምታድገው ልክ አንድ ሕፃን ልጅ እንደሚያድገው ነው። እያንዳንዱም ክፍል በአንድነት በፍቅር ያድጋል። የተለያዩትን የአካል ክፍሎች በመገጣጠም የሚያገናኘው የማያያዣ ገመድ አካሉ በጥሩ ሁኔታ እንዲያድግ ይረዳል። እያንዳንዱ ገመድ እንደ ሰላም ማሰሪያ (ቁ. 3) በመሆን የአካልን ክፍሎች ያያይዛል። እንደ አንድ ተራ አካል የቤተክርስቲያን አባሎች የማይገጣጠሙና በሰላም ማሰሪያ የማይተሳሰሩ ከሆነ፥ ቤተክርስቲያኒቱ ሥራዋን በደንብ አትሠራም፤ ማደግዋንም ታቆማለች ማለት ነው።

---

[17] በሌላ መልኩ ክርስቲያኖች እንደ ሕፃናት መሆን አለባቸው፤ በተለይም እንደ ሕፃናት ብሩህና መተማመን የተሞላበት ይዞታ ሊኖረን ይገባል፤ የሕፃን ልጅ እምነት ሊኖረን ይገባል (ማር. 10፥15 ይመለከቷል)።

አሮጌው ሰውና አዲሱ ሰው (4፥17–32)

17 በዚህ ክፍል ጳውሎስ አዲስ ርዕሰ ጉዳይ ይጀምራል። ከቁ. 1–16 በነበረው ክፍል ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ተናግሮአል፤ አሁን ደግሞ ከቁ. 17 አንስቶ እስከ 5፥21 ድረስ ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ንጽሕና ይናገራል። ለቤተ ክርስቲያን ከሁሉ ነገር ይበልጥ በጣም አስገላጊ የሆኑት ሁለት ነገሮች አንድነትና ንጽሕና ናቸው።

ጳውሎስ የኤፌሶንን ክርስቲያኖች «ከእንግዲህ ወዲህ *እንደ አረማዊያን አትኑሩ»* በማለት ይመክራቸዋል። በእርሱ ዘመን የነበሩት ብዙዎቹ አረማውያን እውነተኛ በሆነው በአንድ አምላክ አያምኑም ነበር። ይልቁንም ጣኦታትን የሚያመልኩና ርኩሰትን የሚፈጽሙ ነበሩ። አእምሮአቸውም የሚሞላው በከንቱና ዋጋ ቢስ በሆነ አሳብ ነበር። በእርግጥም በየዘመናቱ የሚኖሩ ዓለማዊያን ሰዎች በጳውሎስ ዘመን እንደነበሩት አረማውያን ናቸው፤ ስለዚህም እንደ ዓለማዊያን አንሁን። እኛ ከእንግዲህ ወዲህ የዓለም ልጆች አይደለንም፤ ይልቁንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን። ከዚህም የተነሣ ልክ የእግዚአብሔር ልጆች የሚያደርጉትን ማድረግ አለብን። እኛ አዲስ ሕዝብ ነን፤ አዲስ ሕዝብ ደግሞ አዲስ ሕይወት መኖር ይገባዋል (ገላ. 3፥27 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

18–19 በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ደግሞ በዓለማውያን ሰዎች ላይ በመጨረሻ የሚደርስባቸውን ነገር እናያለን። በይበልጥ ከእግዚአብሔር እየራቁ ይሄዳሉ፤ ልባቸውም ከምን ጊዜውም ይልቅ እየጠነከረ ይሄዳል (ቁ. 18)። ከዚህም ከልባቸው ድንዳኔ የተነሣ ስሜታቸው እየጠፋ ይመጣል። ትክክል የሆነውን ትክክል ካልሆነ ነገር ለመለየት ግድ አይኖራቸውም። ንጽሕና ከሌለው ነገር ሁሉ ደስታ ለማግኘት ይጥራሉ። ይሁን እንጂ፥ ምንም እርካታ አያገኙም፤ ስለሆነም ከፉ ምኞታቸው የማያቋርጥ ይሆናል (ቁ. 19)።

20–21 እናንተ ግን ክርስቶስን ለማወቅ የበቃችሁት በዚህ መንገድ በመሄድ አይደለም። ኤፌሶናውያን ከክርስቶስ ትምህርት ወይም ከክርስቶስ ምሳሌንት ይህን የመሰለ ጠባይ አልተማሩም። ይህን የመሰለ ጠባይ በሐሰት ላይ የተመሠረተና የክርስቶስ ትምህርት የሚሰጠውን እውነት በመካድ ላይ የተመሠረተ ነው። የኤፌሶን ሰዎችም ይህን የመሰለውን እውነት አጥብቀው መያዝ ይገባቸዋል፤ የዓለምን የሐሰት መንገድ መከተል አይኖርባቸውም።

22 የኤፌሶን ክርስቲያኖች ከክርስቶስ የተማሩት ምን ነበር? አሮጌውን ሰውነት አውልቆ መጣል እንዳለባቸው ነበር። ማለትም ከአሮጌው ኃጢአተኛ ሰውነታቸው ከንቱ የሆነ አሳቦችንና ምኞቶችን እንዲሁም ከፉ ሥራን ሁሉ አውልቀው መጣል ይገባቸዋል። እያንዳንዳችን የተወለድነው ኃጢአተኛ ሰውነትን ይዘን ነው፤ ክርስቶስንም እስክንቀበል ድረስ ያ ኃጢአተኛ ሥጋችን ይቆጣጠረን ነበር። አሮጌው ሰውነት ማለት እንደ እውነቱ ከሆነ በኃጢአተኛው ሥጋ ቁጥጥር ውስጥ የነበረው ሰውነታችን ማለት ነው። ስለዚህ አዲሱን ሰውነት ከመልበሳችን በፊት (ቁ. 24)፥ አሮጌውን ሰውነት አውልቀን መጣል ወይም አሮጌውን ሰውነት መግደል ይኖርብናል ማለት ነው (ሮሜ 6፥6፤ 8፥13 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

23 ጳውሎስ የኤፌሶንን ክርስቲያኖች በአእምሮአቸው ይዘታ[18] ወይም በመንፈሳቸው አዲስ እንዲሆኑ ያሳስባቸዋል (ሮሜ 12፥2)። ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚጽፈው አስቀድመው ክርስቲያን ስለነበሩ ሰዎች ነው። እነዚህ የኤፌሶን አማኞች አዲስ የሆነውን መንፈሳዊ ሕይወት በክርስቶስ በማመናቸው ጀምረዋል፥ ዳግመኛ ከተወለዱም ቆይተዋል (ዮሐ. 3፥3–5)። ዳግመኛ ያልተወለዱትን ሰዎች *«በአእምሮአችሁ ይዘታ ወይም በመንፈሳችሁ አዲስ ሁኑ»* ማለት ምንም ጥቅም የለውም፤ ምክንያቱም በጭራሽ የማይቻል ነገር ስለሆነ ነው። በራሳቸው አዲስ አእምሮ መፍጠር አይችሉም፤ በመጀመሪያ በኢየሱስ ማመንና አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት መቀበል ያስፈልጋቸዋል፤ ከዚያ በኋላ አዲስ አእምሮ ሊያገኙ ይችላሉ።

እነዚህ የኤፌሶን ክርስቲያኖች አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ስላገኙ አሁን ደግሞ አዲስ አእምሮ አስፈልጎአቸዋል። አዲስ ልደት፥ አዲስ ሕይወት፥ አዲስ አእምሮ ማለት ነው። አዲስ አእምሮ ካለን የእግዚአብሔርን ቃል ልንረዳና በብርሃን ልንመላለስ የቻለናል፤ በጨለማ ግን እንሄድም። በእውነት እንመላለሳለን እንጂ ባለማስተዋል መሄድ አይሆንልንም።

24 እንግዲህ አሮጌውን ኃጢአተኛ ሰውነት አውልቀን ከጣልን፥ *አዲሱን ሰውነት መልበስ* ይገባናል። ይህም ማለት በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር የሚውለውን አዲሱን መንፈሳዊ ሰውነት መልበስ ይኖርብናል። ስለሆነም አስተሳሰባችን፥ ምኞታችንና ሥራችን ሁሉ ተለውጦ አዲስ መልክ መያዝ ይገባዋል። አሮጌውን አውልቀን አዲሱን ሳንለብስ ብንቀር እርቃናችንን እንቀራለን። ብዙ ሰዎች አሮጌውን አውልቀው አዲሱን ሳይለብሱ ይቀራሉ። አሮጌ ሃይማኖታቸውን አሮጌ እምነታቸውን አሮጌ መንገዳቸውን ይተዋሉ። ይሁን እንጂ፥ አዲሱን መንገድ አይከተሉም። እዚህ ወይም እዚያ እያሉ ያለ ዓላማ ሲዋልሉ ይታያሉ። ውለው አድረውም ወደ ቀድሞው ሕይወታቸው ገብተው ይገኛሉ፤ የመጨረሻ ሁኔታቸው ከመጀመሪያው ይልቅ የባሰ ይሆናል (ማቴ. 12፥43–45፤ 2ጴጥ 2፥20 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

እኛም ሁላችን ብንሆን በክርስቶስ ባመንንባ ዳግመኛ በተወለድን ጊዜ «አዲስ ፍጥረት» ሆንናል (2ቆሮ. 5፥17)። ስለሆነም፥ አሁን እንደ አዲስ ሕዝብ መኖር አለብን። በእውነተኛ ጽድቅና ቅድስና እግዚአብሔርን ለመምሰል የተፈጠረ አዲስ ሕዝብ ሆነን ለመገኘት አዲሱን ሰውነት መልበስ ይገባናል።

ጳውሎስም አዲሱን *ሰውነት ልበሱ* ይለናል። ይህን «አዲስ ሰውነት» ከአዲስ መለዮ ልብስ ጋር ማወዳደር ይኖርብናል። በሆስፒታል ውስጥ የሚሠሩ ነርሶች የራሳቸውን ልዩ የሆነ መለዮ ልስብ ይለብሳሉ። ፖሊሶችና በወኅኒቤት የሚገኙ እስረኞችም የየራሳቸው የሆነ መለዮ ልብስ አላቸው። እንዲሁም ክርስቲያኖች የራሳቸው የሆነ መለዮ ልብስ አላቸው፤ ለክርስቲያኖች መለዮ የሆነ ልብሳቸው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። «የክርስቶስ አእምሮና የክርስቶስ ጠባይ ይኑራችሁ» የተባልነውም ለዚህ ነው። ክርስቲያኖች ክርስቶስን «ለብሰው» መገኘት ይኖርባቸዋል።

የአንድ ሰው መለዮ ልብስ ከሞያው ጋር መመሳሰል እንዳለበት ሁሉ፥ የክርስቲያን ጠባይም ከሞያው ጋር መመሳሰል ይኖርበታል። ይህም ማለት እንደ እግዚአብሔር ልጅ መኖር ይገባዋል ማለት ነው። የአንድን ሰው ሞያ ልናውቅ የምንችለው፥ በመለዮ ልብሱ ነው። እኛም ክርስቲያኖች የክርስቲያናዊ መለዮ ልብሳችንን የማንለብስ ከሆነ፥ ሰዎች ክርስቲያን መሆናችንን እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? ክርስቲያኖች መሆናችንን ሊያውቁ አይችሉም። አዲስ ሰው አዳዲስ ልብሶችን መልበስ ይገባዋል፤ አንድ እስረኛ ከወህኒ ቤት በሚለቀቅበት ጊዜ በመጀመሪያ ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል? የወህኒ ቤት ልብሶቹን አውልቆ በመጣል አዳዲስ የሆኑ ልብሶችን ይለብሳል። በዚህ ዐይነት እኛም አማኞች ከኃጢአትና ከሰይጣን ወህኒቤት ነፃ ስለወጣን የወህኒቤት ልብሳችንን አውልቀን በመጣል፥ አዲሱን ልብሳችንን ክርስቶስን መልበስ ይኖርብናል (ሮሜ 13፥14 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

25 እዚህ ላይ ጳውሎስ አውልቀን መጣል ስለሚገባን አሮጌ ጠባይና በምትኩ መልበስ ስለሚገባን አዲስ ጠባይ አንዳንድ ምሳሌዎችን ይሰጠናል።

በመጀመሪያ ውሸት አትናገሩ፤ ይልቁንም እውነትን ተናገሩ ይለናል። በማንኛውም መልክ ቢሆን፥ ሁልጊዜ እውነትን መናገር ይገባናል። ስሕተታችንንና ኃጢአታችንን ለመደበቅ ስንል ምን ያህል ጊዜ እውነትን እናጣምማለን? ይህን ማድረግ ፍጹም አይገባንም። እውነትን ስናጣምም ውሸት እንናገራለን።

«ውሸት አልናገርም» ብለን ዝም ማለት በቂ አይደለም። እውነትን በሙሉ መናገር አለብን። ከእውነት ከፍለን ብንናገር ምንም እንኳን ውሸት ያልተናገርን ቢሆንም፥ ሌሎችን ውሸት እንዲያምኑ እንመራቸዋለን። ከእውነት ከፍለን በመደበቅ ሌሎችን እናታልላለን። በዚህ መንገድ ሌሎችን ማታለል ልክ ውሸት እንደመናገር ይቆጠራል።

---

[18] ይዘታ በሚለው ቃል ፈንታ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች «መንፈስ» ይሉታል፤ በዚህ ክፍል ትርጉም ተመሳሳይ ነው።

እውነትን መናገር ሌላ ትርጉም አለው፤ ቃላችንን ወይም የሰጠነውን ተስፋ መጠበቅ ነው። በእኛና ቃል በገባንለት ሰው መካከል ፍጹም መተማመን ሊኖር ይገባል።

26 *ምንም ያህል ብትቆጡ፥ ኃጢአት አትሥሩ።* ይህ እውነት ከመዝ. 4፥4 የተጠቀሰ ነው፤ በምንቆጣበት ጊዜ የምንቆጣው ከሰውየው ጋር ሳይሆን፥ ከተፈጠረው ስሕተት ጋር መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል። ምንም ያህል ጥፋት ቢያጠፋም ቁጣችን ከሰውየው ጋር ከሆነ በበኩላችን[19] ኃጢአት ሠርተናል ማለት ነው። ጥፋተኛውን መቆጣት ሳይሆን፥ ጥፋቱን ይቅር ማለት ይገባናል። ዘወትር ኃጢአትን የምንጠላ ሆነን ኃጢአተኛውን ግን የምንወድ መሆን አለብን፤ ክርስቶስ እኛን የተመለከተን በዚህ ሁኔታ ነበር።

በሌላው ሰው ኃጢአት ወይም ስሕተት እንደሚገባን የተቆጣን ቢሆንም፥ ለብዙ ጊዜ ተቆጥተን መቆየት አይገባንም። ፀሐይ በምትጠልቅበት ጊዜ የእኛም ቁጣ ማብቃት ይኖርበታል። አለበለዚያ ሰይጣን ወደ ልባችን ገብቶ ቅዱስ ቁጣችንን ወደ ኃጢአት ቁጣ ለመለወጥ ዕድል ያገኛል። ታዲያ ቁጣችንን እንዴት መተው እንችላለን? ስሕተት የሠራውን ሰው ከልባችን በፍጹም ይቅር ማለት ስንችል ነው።

27 *ሰይጣን* ሁል ጊዜ የእኛን ቁጣ ለራሱ ዓላማ ለማዋል ጥሩ አጋጣሚ ለማግኘት በመጣጣር ላይ ይገኛል። እኛ በምንቆጣበት ጊዜ ያስቆጣንን ሰው የመናገር ልምድ አለን። እኛ የምንለውን ሌሎች ሰዎች ሰምተው በዚያ ሰው ላይ ክፉ ወሬ ማውራት ይጀምራሉ። ይህም በሚሆንበት ጊዜ ሰይጣን ደስ ይለዋል፤ ምክንያቱም ወዲያውኑ ክርስቲያኖች እርስበርሳቸው ክፉ ነገር ማውራት ይጀምራሉና። ሰይጣን ቤተክርስቲያንን ለመከፋፈል ወይም የክርስቲያናዊ ኅብረትን ለማጥፋት የሚጠቀምበት ዐይነተኛ ዘዴው ይህ ነው።

በሌሎች ሰዎች ላይ ክፉ ነገር መናገር ይቅርና ይህን የመሰለ ንግግር መስማትም ቢሆን ጨርሶ ስህተት ነው። ምንም እንኳ እውነት ቢሆን፥ ሌላውን ሰው በክፉ ማንሳት የሰውን ስም ማጥፋት ነው፤ የሰውን ስም ማጥፋት ደግሞ ከባድ ኃጢአት ነው (ሮሜ 1፥30፤ 1ቆሮ. 5፥11፤ ኤፌ. 4፥31)። ሰይጣን ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት ከሚጠቀምባቸው የጦር መሣሪያዎች አንዱ ስም ማጥፋት ነው።

28 ጳውሎስ ከሰጠው የአሮጌው ጠባይ ሁለተኛው ምሳሌ *«ስርቆት»* ነው። አዲሱ ጠባይ ጠቃሚ *ሥራን መሥራት* ነው፤ ስርቆትን መተው ብቻ በቂ አይደለም። ነገር ግን *ሥራን* ለመሥራት መጀመር ያስፈልጋል። ለስንፍና ምንም ስፍራ መስጠት አይገባም። ቤተሰቦቻችን የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙ ብቻ ሳይሆን፥ ሌሎችንም በችግራቸው ለመርዳት ስንል መሥራት ይኖርብናል። በአንድ ወቅት ይሰርቅ የነበረን፥ ሌላ ጊዜ እንዲሰጥ አድርጎ ጨርሶ ሊለውጠው የሚችል ኃይል ክርስቶስ ብቻ ነው።

29 ሦስተኛው የአሮጌ ጠባይ ምሳሌ «ጤናማ ያልሆነ *ክፉ ንግግር»* ነው። በአዲሱ ጠባይ ግን *«ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን» ቃል* ብቻ መናገር ነው። የምንናገረው ነገር ሁሉ በዚህ መለኪያ የሚመዘን ይሁን። የምንናገረው ነገር ሌሎች ሊታነጹበት ይችላሉን? ሊበረታቱበት ወይም ጥቅም ሊያገኙበት ይችላሉን? ብለን እንጠይቅ። ለጥያቄው የአዎንታ መልስ የምናገኝበት ከሆነ እንናገር፤ እንደዚህ ካልሆነ ግን ዝም እንበል።

30 የሚቀጥለው የአሮጌ ጠባይ ምሳሌ በጣም ሰፊ የሆነና፤ እንደ እውነቱ ከሆነ አሮጌ ጠባዮቻችንን በሙሉ በአንድነት የሚያያይዝ ነው። ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን «ማሳዘን» ብሎታል። *«ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ»* በማለትም ጽፎታል። እኛ ኃጢአት በምንሠራበት ጊዜ መንፈስን እናሳዝናለን፤ ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስን እናውከዋለን፥ እናስጨንቀዋለን፥ እንደገናም እንሰድበዋለን ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ቅድስና በጎደለው በማናቸውም ነገር ሊያዝን ይችላል።

መንፈስ ቅዱስን ስናሳዝነው ከእኛ ርቆ ይሄዳል፤ እኛ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለብ እያልን ስንሄድ ትጋታችን ወይም ደስታችን እየቀነሰ ሲሄድ በአንድ በኩል መንፈስ ቅዱስን አሳዝነነዋል ማለት ነው (ኢሳ. 63፥10)። በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም የታተምን መሆናችንን ጨርሶ አንርሳ (ኤፌ. 1፥13)። እዚህ ላይ ጳውሎስ «በመንፈስ ታትማችኋል» ይለናል። በመንፈስ የታተምነውም ለመዋጀት[20] ወይም ለመዳን ቀን ነው፤ በመንፈስ መታተማችንም ወደ መንግሥተ ሰማይ መግቢያችን ነው። ስለዚህ ጨርሶ ልንጥለው አይገባንም።

31–32 በቁ. 31 ጳውሎስ ሌሎች የአሮጌው ጠባይ ምሳሌዎችን ይሰጠናል። በቁ. 32 ደግሞ የአዲሱን ጠባይ ምሳሌዎችን ይነግረናል (ቆላ. 3፥12–13 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

ገና ኃጢአተኞች ሳለንም እግዚአብሔር ይወደን ነበር (ሮሜ 5፥8 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)፤ ኃጢአታችንንም ስለ ክርስቶስ ሲል ይቅር ብሎናል። እኛም ሌሎችን ይቅር ባንል እግዚአብሔር ይቅር እንደማይለን ኢየሱስ አስጠንቅቆናል (ማቴ. 6፥12፤ 14፥15 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ይህን ማስጠንቀቂያ ዘወትር ልብልንለው ይኖርብናል።

ምዕራፍ 5

እንደ ብርሃን ልጆች መኖር (5፥1–21)

1–2 እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገው ነገር በጸጋ እንደሆነ ሁሉ፥ እኛም እግዚአብሔርን በመምሰል ለሌሎች የምናደርገው ነገር ሁሉ በጸጋ መሆን አለበት። እኛ ሌሎች ሰዎችን የምንወደው ልክ ክርስቶስ እኛን እንደወደደን ሊሆን ይገባል። ለክርስቶስ ፍቅር ታላቅ ምስክር የሚሆነው፤ *እርሱ ራሱን መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእኛ አሳልፎ መስጠቱ* ነው። እኛም ልክ እርሱ እንዳደረገው ራሳችንን ለሌሎች አሳልፈን መስጠት ይገባናል። ይህም ማለት ሕይወታችንና ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር መባና መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ ማለት ነው (ሮሜ 12፥1 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

3 በዚህ ጥቅስ ጳውሎስ ግብረ ገብነት ስለጎደለው የግብረ *ሥጋ* ግንኙነት፥ ስለ ልዩ ልዩ ርኩሰትና ስለ ስግብግብነት ይናገራል። የኤፌሶን ሰዎች ከነዚህ ክፉ ነገሮች እንዲለዩ ብቻ አልነገራቸውም። ነገር ግን እነዚህን ክፉ ነገሮች ማድረግ ይቅርና ወሬው እንኳ እንዲሰማባቸው አልፈለግም ይላቸዋል። እነዚህ ክፉ ነገሮች ስማቸው እንኳን በመካከላችሁ እንዳይነሳ ብሎ ይነግራቸዋል።

የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን ቅዱሳን ተደርገናል፤ ስለሆነም ቅዱስ ኑሮ መኖር ይገባናል። ቅዱስ ያልሆነ ነገር ለማድረግ በምንፈተንበት ጊዜ ወዲያውኑ የእኛን ማንነት ማስታወስ ይኖርብናል። እኛ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ ነን፤ እኛ የእግዚአብሔር ልጆቹ ነን፤ ይህን አሳብ ሁል ጊዜ ከአእምሮአችን የማናጠፋው ከሆነ፥ ፈተናን ለመቋቋም እርዳታ እናገኛለን። እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን «አንተ ልጄ ነህ፤ ስለዚህ እንደ ልጅ መኖር ይገባሃል» ይለናል (2ቆሮ. 6፥17–18 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

4 ክርስቲያኖች የብልግናና *ረብ የሌለው ወይም ጸያፍ ነገር መናገር አይገባቸውም፤* ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚጠቅሰው የቀልድ ዐይነት ብልግና የተሞላበት፥ ሊጎዳ የሚችልና ሌሎችንም መቀለጃ የሚያደርግ ነው። ይሁን እንጂ «ክርስቲያኖች ጨርሶ ምንም ዐይነት ቀልድ መቀለድ የለባቸውም» ማለቱ አይደለም። ብዙዎችንና ጨርሶ የማይስቀውን ሰው እንኳ ሊያስቅ የሚያስችል ዐይነት ቀልድ አለ። ክርስቲያኖች ሁል ጊዜ ጭፍግ ያሉና ኮስታራዎች መሆን አይገባቸውም። ክርስቲያኖች ቢስቁና ጥሩ ጊዜ ቢኖራቸው፤ እንዲሁም እርስበርሳቸው ቢቀላለዱ ምንም ክፉ

[19] በተፈጠረው ስሕተት ላይ ቁጣችንን ስንገልጽ ቁጣችንን ያንን ስሕተት የፈጸመውን ሰው ለመጥቀም እንጠቀምበታለን፤ . . . ስሕተት በፈጸመው ሰው ላይ የምንቆጣ ከሆነ ግን እርሱን ለመጥቀም ሳይሆን እርሱን ለመጉዳት እንመኛለን፤ ኃጢአትም ይሆናል።

[20] ስለ ቤዛነት ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት የኤፌሶን 1፥7 መግለጫ ከነ ግርጌ ማስታወሻው ይመለከቷል።

ነገር የለበትም፤ እዚህ ላይ የተሰጠው ትእዛዝ «ቀልዳችን ኮስኳሳና ሌሎችን የሚጎዳ መሆን የለበትም» የሚል ነው።

በዚህ ጥቅስ ጳውሎስ «ክርስቲያኖች መንፈሳዊነት የጎደለው ንግግር መናገር የለባቸውም» የሚል ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ነው የወደደው። እያንዳንዱን ጥንቃቄ የጎደለውን ንግግራችንን እግዚአብሔር ሆን ብሎ ይመለከተዋል (ማቴ. 12፥36–37 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ዓላማ የሌለውን ዓለማዊ ንግግር ከምንናገር ይልቅ፥ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ስላሳየን ታላቅ ፍቅርና ጸጋ በደስታ ልናመሰግነው ይገባናል።

5 ጳውሎስ *«ንፉግ ሰው ጣዖት አምላኪ ነው!»* ይለናል። ንፉግ ሰው እግዚአብሔርን በማምለክ ፈንታ ገንዘብንና ሌላውንም ንብረት ያመልካል። ለንፉግ ገንዘብና ንብረት ልክ እንደ ጣዖት ነው (1ዮሐ. 5፥21 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ባለጌ ርኩስና ንፉግ የሆነ ሰው በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሊገባ አይችልም (1ቆር. 6፥9–11፤ ገላ. 5፥19–21 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። በእርግጥ እኛ አማኞች ይህን የመሰለ ርኩሰት ማድረግ የለብንም። ይህን የምናደርግ ከሆነ በመንግሥተ ሰማይ ያለንን ርስት እናጣለን (ማቴ. 7፥21፤ 1ዮሐ. 2፥15–17 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

6–7 ሰዎች ብዙ ጊዜ በከንቱ ንግግር ሊያታልሉን ይሞክራሉ (ቁ. 6)። «የምትፈልገውን ብታደርግ ምንም አይደለም፤ አንተን ደስ ይበልህ እንጂ፥ የፈለግኸውን ነገር ማድረግ ትችላለህ። ታዲያ በትንሹ ኃጢአት ብትሠራስ ምን አለበት በዚህ ጉዳይ ምንም ልትጨነቅ አይገባህም፤ ምንም ነገር ሊደርስብህ አይችልም፤ አይዞህ! አትፍራ!» ይሉናል።

ነገር ግን ይህ ሁሉ ረብ የሌለው ከንቱ ንግግር ነው። ኃጢአት ከሠራን አንድ ነገር መሆኑ የማይቀር ነው። የእግዚአብሔር ቁጣ በላያችን ይወድቃል፤ ኃጢአታችን ዘላለማዊ የሆነ ውጤት አለው። እግዚአብሔር በሰዎች ሁሉ ላይ ይፈርዳል። አማኞች በሆኑም ባልሆኑም ላይ በሠሩት በማንኛውም ኃጢትር ላይ ይፈርዳል (ሮሜ 14፥12፤ 2ቆሮ. 5፥10 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ስለዚህ ከንቱ በሆነ ንግግር አንታለል።

ይህም ሆኖ ክርስቲያኖች በየጊዜው ኃጢአት መሥራታቸው የማይቀር ነው። ማንኛችንም ብንሆን ያለ ኃጢአት መሆን አንችልም (1ዮሐ. 1፥8)። ነገር ግን ወዲያው በኃጢአታችን ንስሐ የምንገባ ብንሆን ይቅርታ እናገኛለን። ከኃጢአታችንም እንነጻለን። የእግዚአብሔር ቁጣ በእኛ ላይ ሳይወርድ ይቀራል (ምሳ. 28፥13፤ 1ዮሐ. 1፥9)። በኃጢአታቸው ንስሓ ሳይገቡ የሚቀሩና ባለመታዘዝ ጸንተው የሚቆዩ ግን በእርግጥም የእግዚአብሔር ቁጣ በላያቸው ይወርዳል።

ክፉ የሚያደርጉ ሰዎች፥ ክርስቲያኖችም እነርሱን በመከተል እንደነርሱ ክፉ እንዲያደርጉ ይገፋፉአቸዋል። በክርስቶስ ከማመናችን በፊት እኛም ራሳችን ብንሆን ክፉ አድራጊዎች ነበርን። በተለይ የቀድሞ ጓደኞቻችን ከዚህ በፊት ከእነርሱ ጋር ያደረግነውን ክፉ ነገር መልሰን እንድናደርግ ይመክሩናል። እኛ ግን «ይህንንስ አላደርገውም» ብለን እምቢ ማለት ይገባናል። ክፉ በማድረግ ከእነርሱ ጋር ተባባሪዎች መሆን የለብንም (ቁ. 7)።

8–9 *እናንተ ራሳችሁ ቀድሞ በጨለማ ውስጥ ትኖሩ ነበር።* ጳውሎስ ቀደም ሲል የኤፌሶን ሰዎች በአእምሮአቸው የጨለሙ እንደነበሩ ነግሮአቸዋል (ኤፌ. 4፥18)።

ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነው፤ ስለሆነም እርሱን የሚከተሉ ሁሉ የሚመላለሱት በብርሃን ነው (ዮሐ. 8፥12 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ይህም ብቻ ሳይሆን እኛ ክርስቶስን ስንከተል የእርሱ ብርሃን በእኛ ውስጥ ይበራል፤ ሌሎች ሰዎች የሚሄዱበትንም መንገድ ያሳያቸዋል። ስለዚህ ጳውሎስ እዚህ ክፍል ላይ «እኛ በጌታ ብርሃን እንደሆንን» ይናገራል (ቁ. 8)። እኛ የብርሃን ልጆች ነን (ዮሐ. 12፥35–36፤ 1ተሰ. 5፥5፤ 1ጴጥ. 2፥9 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

10 ክርስቲያኖች ዘወትር መልካም ያደርጋሉ፤ ታዲያ መልካም የሚያደርጉት ከመፍራት ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማስደሰት ካላቸው ምኞት የተነሣ ነው። ወላጆቻቸውን ለማስደሰት ካላቸው ምኞት የተነሣ ታዛዥ እንደሚሆኑ ልጆች ናቸው። ስለዚህም ጳውሎስ፥ *ጌታን ደስ የሚያሰኘው ነገር ምን እንደሆነ መርምሩ* ይለናል። ጌታን ሊያስደስት የሚችለውም ነገር ይህ ነው፤ ልጆቹ በብርሃን እንዲመላለሱ፥ ከጨለማም ሥራ ጋር ጨርሶ እንዳይተባበሩ፥ ይልቁንም በብርሃናቸው የጨለማን ሥራ አውጥተው እንዲያጋልጡ ነው (ቁ. 11)። ክፉ ሰዎች ሥራቸውን የሚሠሩት በጨለማ ውስጥ ነው፤ ክፉ ሥራቸው እንዳይጋለጥባቸውም ወደ ብርሃን መውጣት አይፈልጉም (ዮሐ. 3፥19–20 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

11 ወደ ብርሃን አውጥታችሁ አጋልጡት እንጂ፥ ፍሬቢስ ከሆነ ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፤ የጨለማን ሥራ ለማጋለጥ ምን ማድረግ ይገባናል? ዝም ብለን ብርሃናችን እንዲበራ ማድረግና የጽድቅን ምሳሌነት ማሳየት ነው፤ የጨለማን ሥራ ማለትም ክፉ ነገርን ለማጋለጥ ይህን ማድረግ ብቻ በቂ ነው። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ክፉ ነገርን ፊት ለፊት መቃወም ይኖርብናል። ብዙውን ጊዜ ግን ማድረግ የሚገባን ብርሃናችንን እያበራን መኖር ነው። ክፉውን ነገር ለማጋለጥ የምንጠቀምበት መልካም ዘዴ ይኸው ነው።

ጳውሎስ *ከጨለማ ሥራ ጋር ጨርሶ አትተባበሩ* በማለት እንዳሳሰበን አስታውሱ። እርሱ ይህን በሚልበት ጊዜ ግን የጨለማን ሥራ ከሚሠሩ ሰዎች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊኖራችሁ አይገባም አላለንም። አንዳንድ ክርስቲያኖች ሰዎች የሚያደርጉትን ክፉ ነገር በማየት ከእነርሱ ጋር ጨርሶ መነጋገር አይፈልጉም፤ ጳውሎስ በዚህ ጥቅስ ላይ ይህንን እንድናደርግ አይመክረንም፤ ኢየሱስ እንኳ ከኃጢአተኞች ጋር ተመግቧል (ማር. 2፥15–17፤ 1ቆሮ. 5፥9–11፤ 2ቆሮ. 6፥14–18 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

12 አንዳንድ ሰዎች የሚያደርጉት ክፉ ነገር በጣም መጥፎ ከመሆኑ የተነሣ ስለ እነርሱ ማውራት በጣም ያሳፍራል!

13–14 በቁ. 14 ጳውሎስ በዘመኑ ይኖር ከነበረው አንድ ገጣሚ አንድ አሳብ ወስዶ ይጠቅሳል፤ በግጥሙ ውስጥ የሚያንቀላፋው ሰው ከኃጢአቱ የተነሳ የሞተ ሰው ነው (ሮሜ 13፥11፤ ኤፌ 2፥2)።

15 እንግዲህ እንዴት እንደምትኖሩ በጥንቃቄ አስተውሉ፤ በእርግጥ እንዴት መኖር እንደሚገባን የሚለው አነጋገር በሕይወታችን በጣም ጠቃሚና ዘወትር በተለምዶ በየቀኑ ማድረግ የሚገባንን ነገር የሚያሳይ ነው። በጥበብ ለመኖር ጠንቃቆችና ብልኅተኞች መሆን ይገባናል፤ ሞኝ ሰው ስለ ኑሮው ምንም ዐይነት ጥንቃቄ አያሳይም፤ ጥበበኛ ሰው ግን በሁሉ ነገር ይጠነቀቃል።

16 ጳውሎስ «ጊዜያችሁን በሙሉ ተጠቀሙበት፤ ወደ እናንተ ሊመጣ የሚችለውን ማንኛውንም አጋጣሚ በሥራ ላይ አውሉት» ይለናል። እግዚአብሔርን ለማስደሰትና በፈቃዱም ለመገኘት የቱንም አጋጣሚ ቢሆን ማባከን የለብንም። አንድ ጊዜ አጋጣሚውን የምናጣ ከሆነ ሌላ ጊዜ መልሰን ማግኘት ያስቸግረናል። አንድ ጊዜ ያጣነውን ዕድል መልሰን ልናገኘው አንችልም (ሌላ ዐይነት አጋጣሚ ተመልሶ ሊመጣ ይችል ይሆናል እንጂ ያ የጠፋው አጋጣሚ ተመልሶ ሊመጣ አይችልም)። ጠቢብ ሰው እንዴት አድርጎ በጊዜው እንደሚጠቀም ያስባል፤ ጊዜ በእግዚአብሔር የሚሰጠን ስጦታ ነው። ስለዚህ ጊዜን ማባከን አይገባንም።

እስቲ ለምሳሌ ዛሬ ጊዜያችንን በጥበብ ተጠቅመንበታልን? በዚህኛው ሕይወታችን በጊዜያችን ምን ያህል እንደተጠቀምን እግዚአብሔር አንድ ቀን ይቆጣጠረናል።

ይህ ያለንበት ዘመን በጣም ክፉ ነው፤ በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ቀኖቻችን ሁሉ በሐዘንና በሥቃይ የተሞሉ ናቸው። በተለይ በጳውሎስ ዘመን የሚታሰሩና የሚሞቱ ብዙ ክርስቲያኖች ነበሩ። ስለዚህ እግዚአብሔርን የምናገለግልበት ጊዜ ካገኘን ያንን አጋጣሚ ክርስቲያኖች ሁሉ መጠቀም ይኖርብናል፤ ምክንያቱም ይህንን የመሰለ ዕድል የማናገኝበት ቀን ሊመጣ ይችላል (ዮሐ. 9፥4)።

17 *የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ* ማስተዋል ይገባናል፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለማስተዋል የመጀመሪያ

እርምጃ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው (ምሳ. 1፥7)። ሞኝ ሰው ግን እግዚአብሔርን አይፈራም፥ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድም ምንም ግድ አይኖረውም። ጥበበኛ ሰው ግን እግዚአብሔርንም ይፈራል ፈቃዱንም ለማወቅ ይጣጣራል።

እግዚአብሔር ለእኛ ሕይወት ያለውን ፈቃድ እንዴት ልናስተውልና እለት እለት ፈቃዱን እንዴት ልናውቅ እንችላለን? የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁለት ክፍል አለው። በመጀመሪያ «አጠቃላይ ፈቃዱ» ሲሆን፤ ሁለተኛ «ልዩ የሆነ ፈቃዱ» ነው። የእግዚአብሔር አጠቃላይ ፈቃድ ለክርስቲያኖች ሁሉ አንድ ነው፤ ይህም ቅዱሳን እንድንሆንና ክርስቶስን እንድንመስል ይፈልጋል። የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ፈቃድ ለይተን ማወቅ እንችላለን።

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁለተኛ ክፍል ማለትም ልዩ የሆነውን ፈቃዱን ለክርስቲያኖች ሁሉ አንድ ዐይነት አይደለም፤ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የተለየ ነው። በእያንዳንዱም ሁኔታ ይለያያል። ለምሳሌ አንድ ሰው ማንን ማግባት ይኖርበታል? አንድ ሰውስ ምን ዓይነት ትምህርት መማር ይኖርበታል? አንድ ሰው ዛሬ ምን ሊያደርግ የገባዋል? የት መሄድ ይኖርበታል? ይህን በመሳሰሉ ጉዳዮች የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የተለየ ይሆናል። ለእነዚህ ጥያቄዎች ቀጥተኛ መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማግኘት አይቻልም።

ታዲያ ይህን በመሳሰለ ነገር ላይ «የእግዚአብሔርን ልዩ ፈቃድ» እንዴት ለይተን ማስተዋል እንችላለን? በመጀመሪያ ጸሎት በማድረግ ነው፤ መንፈስ ቅዱስን የምንጠይቀው ከሆነ ሊመራን ይችላል። ሁለተኛም መጋቢያችንን፥ ወላጆቻችንን[21]፥ ክርስቲያን ጓደኞቻችንን ወይም የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን ስለ ጉዳዩ በማማከር ነው። ሦስተኛ መጽሐፍ ቅዱሳችንን በማጥናት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችንን በሚገባ የምናጠና ከሆንን «የእግዚአብሔርን ጠቅላላ ፈቃድ» ማስተዋልና በተዘዋዋሪ መንገድ «ልዩ ፈቃዱንም» ለማወቅ እንችላለን። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ የትኛዋን ልጃገረድ ወይም የትኛውን ወጣት ማግባት እንዳለብን ሊነግረን አይችልም፤ ይሁን እንጂ፥ አማኝ ማግባት እንዳለብን ይነግረናል (2ቆሮ. 6፥14)።

የምንጸልይ፥ ምክር የምንጠይቅና መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠና ብንሆንም በአእምሮአችን ተጠቅመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መለየት ይኖርብናል። እግዚአብሔር አእምሮንና የማሰብ ችሎታን ሰጥቶናል። ምንም ማስተዋል እንደሌላቸው እንደ ፈረስ ወይም እንደ በቅሎ መሆን አይገባንም (መዝ. 32፥8–9)። እግዚአብሔር ጥበብና ምሪት ይሰጠናል። ታዲያ ይህን ስጦታ ለመቀበል በአእምሮአችን መጠቀም ይኖርብናል።

18 ክርስቲያኖች ወይን ጠጅ ወይም ማናቸውንም የሚያሰክር መጠጥ ጠጥተው መስከር አይገባቸውም። ጳውሎስ «ክርስቲያን ምንም ዐይነት የወይን ጠጅ መጠጣት የለበትም» አላለንም (መዝ. 104፥15)። ነገር ግን እርሱ የሚለው «ክርስቲያን ሰካራም[22] መሆን የለበትም ነው፤ ክርስቲያን በትንሹ እንኳን መስከር የለበትም። አንዳንድ ሰዎች ይልቁንም አንዳንድ ጎሳዎች በልማድ ብዙ ይጠጣሉ፤ ለእነርሱም ቢሆን እግዚአብሔር «ሌትስከሩ» ነው የሚላቸው። መስከር ኃጢአት ነው። አንድ ሰው አንድ ጊዜ ከሰከረ ሌሎች የከፉ ኃጢአቶችን በቀላሉ መሥራት ይቻላል። ለመጠጥ ያለው ምኞት እያደገ ይሄድና በመጨረሻም ባርያው ይሆናል።

ሰዎች የሚጠጡት ደስታን ወይም መበረታታትን ለማግኘት ብለው ነው። ይሁን እንጂ የሚያገኙት ደስታም ሆነ መበረታታት የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ነው። ይህን የመሰለ ጊዜያዊ ደስታ ለማግኘትም በጣም ከፍ ያለ ዋጋ ይከፍላሉ። መጠጥ ገንዘባቸውን ብቻ ሳይሆን ጤንነታቸውንም ያጠፋል፤ በመንፈስ ቅዱስ የሚሞሉ ከሆነ ግን የሚያገኙት ደስታ ፍስሐና መበረታታት የማያቋርጥ ይሆናል።

«በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ[23]!» ይህ ትእዛዝ እንጂ ምክር አይደለም። ጳውሎስ እዚህ ላይ የጻፈው «ባለማቋረጥ በመንፈስ ተሞሉ» ብሎ ነው። ዛሬና ነገ ብቻ ሳይሆን ሳምንቱን፥ ውሩን፥ ዓመቱን ሙሉ በሕይወታችን ዘመን በሙሉ ማለቱ ነው።

በመንፈስ መሞላታችንን እንዴት ልናውቅ እንችላለን? በመንፈስ መሞላታችንን ልናውቅ የምንችለው በሕይወታችን የመንፈስን ፍሬ ለማየት የምንችል ከሆነ ነው። ይህም ማለት ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ደግነት፥ በጎነት፥ ታማኝነት፥ ገርነትና ራስን መግዛት ነው (ገላ. 5፥22–23)።

በመጠጥ የተሞላ ሰው የሚገኘው በመጠጥ ቁጥጥር ውስጥ ነው የሚገኘው። በመንፈስ የተሞላ ሰው ግን በመንፈስ ቁጥጥር ውስጥ ነው። በመጠጥ የተሞላ ሰው ራሱን መቆጣጠር አይችልም፤ ምክንያቱም ራስ መግዛት የለውም። በመንፈስ የተሞላ ሰው ግን ራስ መግዛት አለው፤ ይህም ራስ መግዛት ዘጠነኛው የመንፈስ ፍሬ ነው። ብጥብጥ የሚፈጥር የአውሬ ጠባይ ያለው ሰው በመካከላችን ቢገኝ ያ ሰው መንፈስ ቅዱስ የሚቆጣጠረው ሰው አይደለም።

19 መንፈስ በእኛ ውስጥ የሚፈጥረው ደስታን ነው። መንፈስ እኛን የሚመራን እንድንዘምርና ለጌታ ልዩ ልዩ ቅኔ እንድናቀርብ ነው፤ ስለሆነም በመዝሙር በውዳሴ በመንፈሳዊም ዜማም በከንፈሮቻችን ብቻ ሳይሆን በልባችን ጭምር ለጌታ ምስጋና እናቅርብ (ቆላ. 3፥16)።

20 *ስለ ሁሉ ነገር ሁል ጊዜ* ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቅርብ። በእርግጥ ስለ ሁሉ ነገር? አዎ! ስለ ሕመም፥ ስለ ማዕበልና ስለ ጎርፍ፥ ስለ ሐዘንና ስለ ችግር ለእነዚህ ሁሉ መልካምም ሆነ መጥፎ ስለ ሁሉ ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን። ለምን? ምክንያቱም እግዚአብሔር አፍቃሪ የሆነ የሰማይ አባታችን ነው። በምንም ዐይነት ችግር ወይም መከራ ውስጥ እንድናልፍ የሚፈቅድ ቢሆንም በመጨረሻው ላይ ለእኛ መልካም ነገር እንደሚያደርግልን በእርግጥ ለማወቅ እንችላለን። እግዚአብሔር ለሚወዱትና ለሚያገለግሉት ልጆቹ ሁል ጊዜ መልካም ነገርን ያደርግላቸዋል (ሮሜ 8፥28 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ስለ ሁሉ ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን የሚገባን ስለዚህ ነው።

21 ሌሎችን ለመቆጣጠር በምንሞክርበት ጊዜ ክርክርና መለያየት ሊመጣ ይችላል፤ ስለዚህ አንዳችን ሌላውን ለመግዛት ከመሞከራችን በፊት ራሳችንን በሌላው ቁጥጥር ውስጥ ለማስገዛት እንሞክር። በዚህ መንገድ መከራከርንና መለያየትን ለማቆም እንችላለን። ራሳችንን ለሌላው አገልጋይ አድርገን ለማቆም እንሞክር። ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ የሰጠን ምሳሌ ለዚህ የሚጠቅም ነው (ዮሐ. 13፥12–15 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

ባሎችና ሚስቶች (5፥22–33)

22 እግዚአብሔር ሚስቶቻቸውን እንዲያስተዳድሩ ለባሎች ሥልጣን ሰጥቶአል። በዚሁ ዐይነት ልጆቻቸውን እንዲያስተዳድሩ ለወላጆች ሥልጣን ሰጥቶአል (ኤፌ. 6፥1)። እንዲሁም ሠራተኞቻቸውን እንዲያስትዳድሩ ለአሠሪዎች ሥልጣን ሰጥቷል (ኤፌ. 6፥5)። በነዚህ በሦስት ጉዳዮች ማለትም ባሎችና ሚስቶች፥ ወላጆችና ልጆች፥ አሠሪዎችና ሠራተኞች እያንዳንዱ ሰው በግሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ተመሳሳይ ሥልጣን፥ ተመሳሳይ ኃላፊነት፥ ተመሳሳይ ሥራ አልሰጠም። ጳውሎስም ቢሆን «ባል ከሚስት ይሻላል» ብሎ አልተናገረም፤ ያለው «እግዚአብሔር በቤተሰብ ውስጥ ለባል ትልቅ ሥልጣን ሰጥቶታል» ነው (ከአስተምህሮ ዳሰሳው፥ ክርስቲያናዊ ጋብቻን ይመለከቷል)። ባል በሚስቱ ላይ ሥልጣን እንዲኖረው የተደረገው ለራሱ ጥቅም እንዲያገኝበት ሳይሆን፥ ይልቁንም ለቤተሰቡ ጥቅም እንዲያስገኝበት ነው።

---

21 ወላጆቻችን ክርስቲያኖች ያልሆኑ ከሆኑና የሚሰጡን ምክር የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃወም ከሆነ፥ በአንድ አስፈላጊ ነገር ላይ የእነርሱን ምክር መቀበል የለብንም።

22 አንዳንድ ክርስቲያኖችን አልኮልነት ያለው መጠጥ ጨርሶ እንዳይጠጡ እግዚአብሔር ይመክራቸዋል (ሉቃ. 1፥15 ይመለከቷል)። ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት የመጠጥ ችግር ያለበት ቢኖር፥ መጠጥን ጨርሶ ማቆም ይኖርበታል።

23 በግሪኩ መጽሐፍ ተሞሉ የሚለው ቃል በየጊዜው ተሞሉ የሚለውን ትርጉም ይሰጣል።

በተቀበለው ሥልጣን አማካይነት በቤተሰብ ውስጥ መልካም ግብረገብነት ሥርዓትና ሰላም እንዲገኝ ያደርጋል። ባል ሚስቱን እንዲበድል ወይም እንዲያዋርድ ሥልጣን አልተሰጠውም፤ ይልቁንም ባል ልክ ክርስቶስ እኛን በመራበት ዐይነት ብዙ ፍቅርና ምሕረት ለሚስቱ ማሳየት ይገባዋል። እግዚአብሔር ለባሎች ሥልጣን የሰጣቸው መልካም እንዲያደርጉ እንጂ፥ ነውር ሥራ እንዲሠሩ አይደለም።

23–24 ልክ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያንና በእያንዳንዱ አማኝ ላይ ሥልጣን እንዳለው ሁሉ፥ ባሎችም በሚስቶቻቸው ላይ ሥልጣን አላቸው። ልክ ክርስቲያኖች ሁሉ በክርስቶስ ሥልጣን ሥር ሆነው እንደሚታዘዙት ሁሉ፥ ሚስቶችም በባሎቻቸው ሥልጣን ሥር ሆነው መታዘዝ ይገባቸዋል (ቆላ. 3፥18፤ 1ጴጥ. 3፥1–2 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። የባል ሥልጣን ከክርስቶስ የተሰጠው ነው እንጂ፥ ከራሱ የተገኘ አይደለም። ሚስቶች ክርስቶስን፥ ማለትም የክርስቶስን መልካም ጠባይ በባሎቻቸው ማየት ይኖርባቸዋል። አንዲት ሚስት ክርስቶስን በባልዋ ውስጥ ማየት የምትችል ከሆነ በባልዋ ሥልጣን ሥር ታዛዥ ሆና መኖር ምንም አያስቸግራትም።

ሚስቶች በባሎቻቸው ሥልጣን ሥር ናቸው እንጂ፥ በሌሎች ወንዶች ሥልጣን ሥር አይደሉም። ሚስቶች እንደ ባሪያ ሊገዙና ከቤት ዕቃ እንደ አንዱ ሊቆጠሩም አይገባቸውም። ሚስት ከባልዋ ጋር በውበትዋና በዋጋዋ እኩል የሆነች የሕያው እግዚአብሔር ፍጡር ነች። በየትኛውም መንገድ ቢሆን በታናሽነት ልትቆጠር አይገባትም። ይልቁንም ባል የራሱን ሥጋ እንደሚወድና እንደሚደሰትበት ሁሉ፥ ሚስቱንም መውደድና በእርሷም መደሰት አለበት (ኤፌ. 5፥28፤ 1ጴጥ. 3፥7 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

ነገር ግን እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ክፉ ባል ያላት ሚስት ምን ልታደርገው ይገባታል? ለምሳሌ ጠጥቶ ይሰክራል፤ ሚስቱንም ይደበድባታል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል የማይፈቅደውን ነገር እንድታደርግ ያስገድዳታል፤ በዚህ ሁኔታ ትታዘዘዋለች? ወይስ አትታዘዘውም? በጭራሽ! በእግዚአብሔር ቃል ላይ በሚደረግ መተላለፍ ምንም ቢሆን ለባልዋ መታዘዝ አይኖርባትም። ባልዋ በእርሷ ላይ ያለው ሥልጣን ከእግዚአብሔር የተቀበለው ሥልጣን እንደሆነ መዘንጋት የለባትም። ባልዋ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሆነ ነገር እንድታደርግ ሲያዛት በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ሥልጣን እንደሌለው ማወቅ ይኖርባታል። የዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር ሚስት ለባልዋ ሳይሆን ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይኖርባታል። በወላጆችና በልጆች፥ በአሠሪና በሠራተኛ፥ በማንኛውም የመንግሥት ተቋምና በሕዝቡ መካከል ባለው ሁኔታ ሁሉ የምንጠቀመው ይህንኑ ተመሳሳይ ሕግ ነው። በሥልጣን ላይ የሚገኙት ማለትም እንደ ወላጆች፥ አሠሪዎች፥ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት የመሰሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ እስከታዘዙ ድረስ በሁሉ ነገር ለእነርሱ ሥልጣን ልንታዘዝ እንችላለን (ቁ. 24)። ይህም ማለት እግዚአብሔር ለእነርሱ ሥልጣን በሰጣቸው ነገሮች ሁሉ ላይ መታዘዝ ይገባናል፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃወም አንዳች ነገር እንድናደርግ ሲያዙን ያንን ነገር ከማድረግ መቆጠብ ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ሁልጊዜ ከሰው ትእዛዝ ከፍ ያለና የሚበልጥ ነው (የሐዋ. 4፥18–20፤ ሮሜ 13፥1–5 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

25 ከቁ. 22–24 ባለው ክፍል ጳውሎስ ሲጽፍ የነበረው ስለ ሚስቲቱ ሥራ እንደነበር አስታውሱ፤ የሚስቲቱም ሥራ ሁል ጊዜ ለባልዋ መታዘዝ ነው። አሁን ደግሞ ከቁ. 25–28 ባለው ክፍል የሚገልጸው ባል ለሚስቱ የሚፈጽመውን ተግባር ነው፤ ይህም እርሷን መውደድ ነው። ባል ሚስቱን የሚወድደው እንዴት ነው? *ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት ባልም ሚስቱን ሊወድ ይገባዋል።* ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ ባልም ለሚስቱ ራሱን አሳልፎ መስጠት ይጠበቅበታል። እስቲ ስለዚህ ነገር አስቡ እናድርግ፥ ባል ሊያደርገው የሚገባው ነገር ቀላል አይደለም (ቆላ. 3፥19)።

26–27 ክርስቶስና ቤተክርስቲያኑ ከሙሽራና ከሙሽሪት ጋር ሊወዳደሩ ይችላሉ። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን፤ *እንደ ንጽሕት ድንግል ለአንድ ወንድ ሰላጨኋችሁ ነው፤ እርሱም ክርስቶስ ነው* በማለት ይጽፍላቸዋል (2ቆሮ. 11፥2)። ምንም እንኳ ንጹሕ ባትሆንና ያልተስተካከለች ብትሆንም፥ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ይወዳታል። ከዚያም በላይ *በቃሉ አማካይነት በውሃ በማጠብ ቀድሶአታል* (ቁ. 26)። ይህም ማለት በቃሉና በጥምቀት[24] ቀድሷታል (ዮሐ. 15፥3 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑ *ዕድፍ ወይም የፊት መጨማደድ ወይም ይህን የመሰለ ሌላ መጥፎ* ነገር ሳይገኝባት ዘወትር በንጽሕና እንድትኖር ምኞቱ ነው (ቁ. 27)።

28–29 እዚህ ላይ ጳውሎስ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዴት መውደድ እንዳለባቸው ሁለተኛውን መንገድ ይናገራል፤ ይኸውም ልክ እንደራሳቸው ሰውነት አድርገው መውደድ ይገባቸዋል። ከተጋቡ በኋላ ባልና ሚስት ሁለቱም አንድ አካል ናቸው (ቁ. 31)። ስለሆነም ባል ሚስቱን መውደድ የሚገባው ልክ የራሱን አካል ራሱን እንደሚወድድ ነው።

30 ለራሳችን የሰውነት ክፍሎች እንደምንጠነቀቀው ሁሉ ክርስቶስም ለራሱ አካል ክፍሎች ማለትም ለቤተክርስቲያን የሚጠነቀቀው እንደዚሁ ነው።

31–33 ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚጠቅሰው ከዘፍ. 2፥24 ሲሆን፤ ይህም እግዚአብሔር በወንዶችና በሴቶች መካከል የጋብቻን ግንኙነት በሚመሰረትበት ጊዜ የተናገረው ነው። በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት በሁለት ሰብአዊ ፍጥረቶች መካከል ሊኖር የሚገባው በጣም የጠበቀ ግንኙነት ነው። በእናትና በልጅ[25] መካከል ከሚኖረው ግንኙነትም የበለጠ ይጠብቃል።

ልክ አንድ ወንድ ከእናቱና ከአባቱ ተለይቶ ከሙሽሪት ጋር እንደሚጣበቅ ሁሉ፤ በዚሁ ዐይነት ክርስቶስ ሰማያዊ ቤቱን ትቶ ከሙሽሪት ወይም ከቤተክርስቲያን ጋር ለመጣበቅ ወደ መሬት መምጣቱን ያሳያል። ልክ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንደተገናኘ ሁሉ ባልና ሚስትም በዚሁ ዐይነት ሊጣበቁ ይገባቸዋል። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ በምትታዘዘው ዐይነት ሚስትም ለባልዋ መታዘዝ ይገባታል። እንዲሁም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በሚወደው ዐይነት ባልም ሚስቱን ሊወድዳት ይገባል። እንግዲህ በደስታ የተሞላና የተዋጣለት ጋብቻ ለማግኘት ይህን ዋስትና ያለው አስተማማኝ ትእዛዝ መከተል ያስፈልጋል።

በዚህ ቤተክርስቲያንና ሙሽሪትን በማወዳደር ባየነው ሁኔታ፥ ስለ ቤተክርስቲያንም ማንነት ልንማር የምንችለው ነገር አለ፤ ጌታዋን የማትታዘዝ ቤተክርስቲያን በባልዋ ላይ እንደምታመነዝር እምነት እንደጎደላት ክፉ ሴት ናት። እንግዲህ ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያናችን ሊሆን አይገባም።

ምዕራፍ 6

ልጆችና ወላጆች (6፥1–4)

1 በመጀመሪያ ይህ ጥቅስ የሚያሳስበው በዕድሜአቸው ያልበሰሉትን ልጆች እንጂ፥ ያደጉትን ልጆች አይደለም። ጳውሎስ «በዕድሜአቸው ያልበሰሉ ትንንሽ ልጆች ለወላጆቻቸው መታዘዝ ይገባቸዋል» ነው የሚለው (ምሳ. 8፥32–33፤ 15፥5)።

2–3 ይሁን እንጂ በዕድሜአችን የቱንም ያህል ያደግን ብንሆንም ወላጆቻችንን የምናከብር መሆን ይገባናል። ከብሉይ ኪዳን ዐሥር ትእዛዛት መካከል ወላጆችን ስለማክበር የተሰጠው ትእዛዝ አምስተኛው ነው (ዘጸ. 20፥12፤ ዘዳ. 5፥16)። ነገር ግን ከተስፋ ቃል ጋር በመያዙ የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው፤ ይህን ትእዛዝ ለሚያከብር ሰው *«ሁሉ ነገር ይሰምርልሃል፥ ዕድሜህም ይረዝማል»* በማለት እግዚአብሔር ተስፋን ሰጥቷል (ቁ. 3)።

4 ልጆች ማድረግ ስላለባቸው ጉዳዮች ከተናገረ በኋላ ጳውሎስ አሁን ደግሞ ወላጆች ማድረግ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ይናገራል። ይህም ወላጆች ልጆቻቸውን *«በጌታ ኢየሱስ ሥነ ሥርዓትና ምክር»* ማሳደግ ይገባቸዋል። የወላጆች

---

[24] ጥምቀት ከኃጢአት ያነጻን እንደሆነ በተጨማሪ ለመረዳት አጠቃላይ መረጃ ውስጥ የውሃ ጥምቀት የሚለውን ቃል ይመለከቷል።

[25] ከልደት በኋላ ሁለት ሥጋ ናቸው እንጂ አንድ አይደሉም።

ዓላማ ልጆቻቸው ታዛዥ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። በዚህ ዐይነት በሕፃንነታቸው ጊዜ ለወላጆቻቸው እንደታዘዙት ሁሉ፥ ልጆቹ በሚያድጉበት ጊዜ ክርስቶስን ይታዘዛሉ (ምሳ. 22፥6)።

መታዘዝን ከማስተማር ጋር ወላጆች ልጆቻቸውን የሚወዱና በገርነት የሚከታተሉ መሆን ይገባቸዋል። ልጆቻቸውን በእኩል ደረጃ የሚመለከቱም መሆን አለባቸው። ልጆቻቸውን በማስቆጣት ማስመረር የለባቸውም። ይህም ማለት ያለ በቂ ምክንያት መገሠጽ ወይም መቅጣት ወይም ተገቢ ያልሆነ የጭካኔ አድራጎት ማድረግ አይገባቸውም። ወላጆች ልጆቻቸውን ያለ ምክንያት ማስቆጣትም አይኖርባቸውም። አዎ! በእርግጥ ልጆቻችንን መቅጣት ይገባናል፤ ታዲያ ስንቀጣቸው የወደፊት ሕይወታቸው በጥሩ አቋም ላይ ሊገኝ እንደሚችል በማረጋገጥ መሆን ይገባዋል። ሁል ጊዜ ስንቀጣቸው በፍቅር መሆን አለበት፤ ፍቅርና ተግሣጽ ሁለቱ በእኩል ደረጃ አብረው መሄድ ይገባቸዋል። ልጆቻችንን ስንቀጣ በመጀመሪያ ጥፋታቸውን በማሳመንና ለምን እንደምንቀጣቸውም በማሳወቅ መሆን ይገባዋል። ቅጣታችንም እጅግ ከመጠን ያለፈ መሆን የለበትም። የልጆቻችን ልስልስ ልብ እንዳያዝን ወይም እንዳይጠነክር ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። ልጆቻችን፥ በምንቆጣበት ጊዜ ወይም ትዕግሥታችን ሲያልቅ መቅጣት አይኖርብንም፤ ልጆቻችን አንድ ክፉ ነገር ሲያደርጉ በጣም በምንቆጣበት ወይም ትዕግሥታችን በሚያልቅበት ጊዜ ቁጣችን እስኪበርድ ድረስ ከመቅጣት መቆጠብ አለብን (ቆላ. 3፥21)። እግዚአብሔር ለባሎች ሥልጣን የሰጠው ለሚስቶቻቸው ጥቅም እንዲያውሉት እንደሆነ ሁሉ፥ እንዲሁም ለወላጆችም ሥልጣን የሰጠው ለልጆቻቸው ጥቅም እንዲያውሉት ነው (ዘዳ. 6፥6–7፤ 2ቆሮ. 12፥14፤ 1ጢሞ. 3፥4፤ ቲቶ. 2፥4)።

ባርያዎችና ጌቶቻቸው (6፥5–9)

5 በአዲስ ኪዳን ዘመን ባርያ ማስተዳደር በመላው ሮም ግዛት ውስጥ ተሠራጭቶ ነበር። ባሪያ አሳዳሪዎች፥ ባሮችን የሚስተዳድሩት በጣም በክፉ ሁኔታ ሲሆን። ነፃነት ወይም መብት ስለአልነበራቸውም፤ ከእንስሳ ይቆጠሩ ነበር። ጌቶቻቸውን በማንኛውም ነገር መታዘዝ ነበረባቸው፤ ከክርስቶስ ወንጌል ሰላምና ተስፋ ስላገኙ ብዙ ባሮች ክርስቲያኖች ሆነዋል! ይህም ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቶስ ደኅንነትንና የዘላለም ሕይወትን ተስፋ ሰጥቷቸዋል።

ክርስቲያኖች ቢሆኑም፥ በባርነት የነበራቸው ይዞታ በጣም አሳዛኝ ነበር፤ ይሁን እንጂ ጳውሎስ «ባሮች ምን ጊዜም ቢሆን ለጌቶቻቸው መታዘዝ ይኖርባቸዋል» በማለት ያሳስባል። አሁን ባለንበት ዓለም ባሪያን የማስተዳደር ልምድ እየቀረ መጥቶአል። ይሁን እንጂ፥ በጳውሎስ ዘመን የነበረው ባሪያና ጌታን የማስተዳደሪያ ደንብ አሁን ባለንበት ጊዜም ቢሆን በሠራተኛና በአሠሪ መካከል ይሠራበታል። ክርስቲያን ሠራተኞች ለቀጣሪዎቻቸው ታዛዦች መሆን ይገባቸዋል። ልክ ለክርስቶስ እንደሚታዘዙ ሁሉ በሥራ ላይ ለአሠሪዎቻቸው መታዘዝ ይኖርባቸዋል (ቆላ. 3፥22–24)።

6 መልካም ሥራን የምንሠራው፥ ሰዎች እንዲያመሰግኑን መሆን የለበትም። ሥራችንን ሥንሠራ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ምስጋና ለማግኘትና ከልብ ቅንነት (ቁ. 5) መሆን ይገባዋል። በሌሎች ሰዎች ፊት መልካም ሆነን ለመታየት ሳይሆን፥ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ለማስደሰት መሆን አለበት።

7–8 የጌቶች ወይም የአሠሪዎች ሥልጣን የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው። በአገልጋይና በጌታ መካከል ምንም ልዩነት የለም፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ሁላችንም አንድ ነን (ገላ. 3፥28)። በእግዚአብሔር ፊት ክርስቲያን ሁሉ እኩል ነው። በምድር ላይ ባላቸው የኑሮ አቋም በመደብና በማዕረግ ይለያዩ ይሆናል፤ በመንግሥተ ሰማይ ግን ሁሉም በእኩል ደረጃ የአንድ ጌታ አገልጋዮች ይሆናሉ (ቁ. 9)። እግዚአብሔር ሰዎችን ለተለያየ ጥሪ ሾሞአል፤ አንዳንዶቹን አሠሪዎች ሌሎችንም ሠራተኞች[26] እንዲሆኑ ጠርቶአቸዋል። ስለሆነም፥ እግዚአብሔር በሾማቸው ባለሥልጣናት ላይ ማጉረምረም ወይም ክስ ማብዛት አይገባንም። ልክ ለክርስቶስ ሥልጣን እንደምንታዘዘው ሁሉ ከቅን ልቦናችን ለአሠሪያችን ወይም ለመንግሥት ወይም ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ሥልጣን መታዘዝ ይገባናል (ቲቶ 2፥9–10 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ለአሠሪዎቻችን ሥራችንን በሚገባ የምናከናውን ከሆንን፥ ሽልማትን እንደምንቀበል እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶናል (ማቴ. 16፥7፤ 2ቆሮ. 5፥10)።

9 የተቀጣሪ ሥራ መታዘዝ ብቻ ነው። እዚህ ላይ ጳውሎስ የሚነግረን ስለ አሠሪው ወይም ስለ ጌታው ሥራ ነው። የአሠሪው ተግባር በሥሩ ያሉትን ማስተዳደር የሚገባው በሰማይ ያለው ጌታ ክርስቶስ እርሱን እንዲያስተዳድረው በሚወደው ዐይነት መሆን አለበት። ይህም ማለት አሠሪው ሠራተኞችን በደግነትና በአክብሮት መያዝ ይገባዋል። ለሠራተኞቹም ትክክለኛ ዋጋ መስጠት ይኖርበታል እንጅ ሊበዘብዛቸው አይገባም። መልካም ሥራ ሊሰጣቸውና ሥራቸውንም በሚገባ ሁኔታ እንዲሠሩ ሊያደርግ ይገባዋል። አሠሪው ወይም ጌትየው ሠራተኞቹ ሥራቸውን የሚሠሩት የእርሱን ስግብግብና ራስ ወዳድ አላማ ለማስደሰት መሆን የለበትም። እግዚአብሔር ለእኛ ምሕረቱንና ፍቅሩን እንዲሁም ይቅርታውን ሰጥቶናል፤ አሠሪው ወይም ቀጣሪው ሠራተኞቹን በዚሁ ዐይነት ቸርነት መያዝ ይኖርበታል። ልክ አንድ ሠራተኛ ጌታውን በመታዘዝ ሥራውን በትክክል ሠርቶ ሲገኝ እንደሚሸልመው ሁሉ አሠሪውም ሠራተኞችን በደንብ በመያዙ፥ ሰማያዊ ሽልማት ማግኘት ይችላል። በምድር ላይ ያሉ ጌቶች ሁሉ በሰማይ ጌታ እንዳላቸው ሁል ጊዜ ማስታወስ ይኖርባቸዋል (ቆላ. 4፥1)። እኛ ሁላችን አብረን የምንሠራ የክርስቶስ ባሪያዎች ነን፤ እያንዳንዳችን ጌታም ሆነን አገልጋይ፥ አሠሪም ሆንን ሠራተኛ እዚህ ምድር ላይ ክርስቶስን በታዘዝን መጠን በሰማይ ሽልማት እንቀበላለን።

እያንዳንዱ ሰው ለሌላው ስላለበት ግዴታ ማሰብ ይኖርበታል፤ ከሌሎች ምን እንደምናገኝ ማሰብ የለብንም። ይልቁንም ለሌሎች ምን መስጠት እንዳለብን እናስብ። ሠራተኞች ስለ ደመወዛቸውና ስለሚያገኙት ጥቅም በመጀመሪያ ማሰብ አይገባቸውም፤ ይልቁንም ማሰብ የሚገባቸው ሥራቸውን በጥሩ ሁኔታ ሠርተው አሠሪያቸውን ለማስደሰት መሆን አለበት። አሠሪዎችም ቢሆኑ ሠራተኞቻቸው ምን ያህል ሥራ እንደሠሩ ማሰብ ሳይሆን፥ በመጀመሪያ ማሰብ የሚገባቸው ለሠራተኞቻቸው ተገቢውን ደመወዝ እንዲያገኙና የሥራ ሁኔታቸውም የተስተካከለ እንዲሆን ማድረግ ነው። እንግዲህ የክርስቲያን መንገድ ይህን የመሰለ ነው። ከሁለቱም ወገን ያሉ ሰዎች ዘወትር ለመብታቸው ብቻ ከማሰብ ይልቅ በየሥራቸው ላይ የሚያተኩሩ ከሆነ አቤቱታ፥ ያለ መስማማት፥ ሰላማዊ ሰልፍ፥ የሥራ ማቆም አድማ ሊኖር አይችልም። ኢየሱስ እኛን ሁላችንን ያስተማረን የእኛን ጥቅም ከማስቀደም ይልቅ የሌሎችን ጥቅም እንድናስቀድም ነው።

የእግዚአብሔር የጦር መሣሪያ (6፥10–24)

10 *በርቱ!* ይህ ትእዛዝ ነው። ታዲያ ይህን ትእዛዝ እንዴት ነው መፈጸም የምንችለው? ብርቱ ልንሆን የምንችለውስ እንዴት ነው? የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ በመልበስ ነው (ቁ. 11)።

11 ስለድካማችን ማሰብ ምንም አይጠቅመንም፤ በእርግጥም ደካሞች ነን! እግዚአብሔር የጦር መሣሪያውን የሚያለብሰንም ለዚህ ነው። በዚህ ዐይነት ብርቱዎች ሆነን በመዘጋጀት ጠላትን መቃወም እንችላለን። ስለዚህም ጳውሎስ «ይህንን የጦር ልብስ ልበሱ» ይለናል።

እግዚአብሔር የጦር ልብሱን ሰጥቶናል፤ የሰጠን መንፈሳዊ የጦር ልብስ ነው፤ ይህም የጦር ልብስ ከዋናው መንፈሳዊ ጠላት ከዲያብሎስ ወይም ከሰይጣን ይከላከልልናል።

---

[26] ለብዙ ክርስቲያኖች በሕይወት ዘመናቸው እግዚአብሔር የማደግን ዕድል ይሰጣቸዋል። ክርስቲያኖችም ይህን ዕድል በመጠቀም ኑሮአቸውን ቢያሻሽሉበት መልካም ይሆናል። ነገር ግን ዋናው ነገር ይህ ነው፤ ለሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቀበል ይኖርብናል፤ ይህም ፈቃድ በሕይወታችን ምን ሊያስከትል እንደሚችል ባናውቀውም እንኳን በእግዚአብሔር ላይ ጨርሰን ልናጉረመርም አይገባንም (1ቆር. 7፥17–24፤ 10፥10 ማብራሪያውንም ይመለከቷል)።

12 በዚህ ዓለም የምንኖረው የክርስትና ሕይወት ልክ እንደ ውጊያ ወይም እንደ ጦርነት የሚቆጠር ነው። በጦርነት ላይ ድል አድራጊዎች ሆነን ለመገኘት የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር የጦር መሣሪያን መልበስ ነው። ሁለተኛው አስፈላጊ ነገር ጠላት ምን ይህል ብርቱ እንደሆነ መረዳት ነው። «ሰይጣን ብርታት የለውም» ከሚል የስሕተት አስተሳሰብ ነፃ መውጣት ይኖርብናል፤ ሰይጣን በጣም ብርቱ ነው። ሰይጣን ብርቱ አይደለም ብለን የምናስብ ከሆነ እርሱ ባቋራጭ ድል ይነሣናል፤ እርሱ ከእኛ ይልቅ ብርቱ ነው። እኛ የጦር መሣሪያችንን የማንለብስ ከሆነ ሰይጣን በቀላሉ ያሸንፈናል።

ሰይጣን ብቻውን አይደለም፤ ከእርሱ ጋር የሚተባበሩ *ገዥዎች፥ ባለ ሥልጣኖች፥* በምድር ላይ ያሉ ኃይሎች፥ በሰማይ ያሉት *ርኩሳን መናፍስት ናቸው።* አሁን ክርስቶስ በሰማይ የሚገዛቸው ባለ ሥልጣናትና ኃይሎች እነዚሁ ናቸው (ኤፌ. 1፥20–21)። እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያኑ አማካይነት እጅግ በዙ የሆነውን ጥበቡን እንዲያውቁ የሚደረጉት ገዥዎችና ባለ ሥልጣናትም እነዚሁ ናቸው (ኤፌ. 3፥10)። ይሁን እንጂ፥ በዚህ በምድር ላይ የእነዚህ ሁሉ ገዥዎችና ባለሥልጣናት ኃይል በጣም ትልቅ ነው። ስለሆነም እነርሱን ለመቋቋም እንድንችል የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ መልበስ ያስፈልገናል።

እንግዲህ የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ ከለበስን በኋላ ስለዚህ እጅግ አስከፊ ስለሆነው ጠላታችንን ስለሰይጣን ማወቅ የሚገባን ምንድነው? በመጀመሪያ እርሱ የማይታይ መንፈስ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ከዚህ በፊት እንዳልነው በጣም ኃይለኛ ነው። በሦስተኛ ደረጃ እርሱ ጠማማና ክፉ *የክፋት መንፈሳውያን ኃይሎች መሪ* ነው። ከሰይጣን ምንም ዐይነት መልካም ነገር ወይም ምሕረት አይገኝም፤ የእርሱ ምኞትና ግብ ማጥፋት ብቻ ነው። የተቻለውን ሁሉ በማድረግ የእያንዳንዱን ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ማጥፋት ይፈልጋል። በአራተኛ ደረጃ ስለ ሰይጣን ማወቅ የሚገባን እርሱ ሎሌና ተንኮለኛ መሆኑን ነው፤ ጴጥሮስ *«ሰይጣን የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ በዙሪያችሁ ያደባል»* ብሎናል (1ጴጥ. 5፥8)፤ ይህም እውነት ነው። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ ሰይጣን አያገሣም፤ ተደብቆና ጸጥ ብሎ እኛ ባልጠበቅንበት ጊዜ በላያችን ላይ እንደ እባብ ይጠመጠማል፤ ወይም ራሱን በመለወጥ እኛ በማናውቀው ሁኔታ ይመጣብናል (2ቆሮ. 11፥14)። እርሱ የበግ ለምድ እንደሚለብስ ቀበሮ ነው፤ ይህን ቀበሮ በጎቹ ልክ እንደ እነርሱ ይቆጥሩታል፤ በመንጋውም ውስጥ እንዲሠማራ ይተውታል (ማቴ. 7፥15 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

ይህን ከመሰለ ክፉ ጠላት ጋር እንዴት መዋጋት እንችላለን?

13 ከሰይጣን ጋር ልንዋጋ የምንችለው በእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ኃይል ከሰይጣን ኃይል ይልቅ በጣም ብርቱ ነው (1ዮሐ. 4፥4 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ በመልበስና በቦታችን ጸንተን በመቆም ሰይጣን ጥሎን እንዲሸሽ ማድረግ እንችላለን (ያዕ. 4፥7 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። በቁ. 11 ላይ እንደገለጸው ጳውሎስ በድጋሚ «የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ ልበሱ» ይለናል። ከጦር መሣሪያዎቹ መካከል አንድ ትንሽ መሣሪያ እንኳ ብትቀር ሰይጣን ወዲያውኑ በዚያ ባልተጠበቀ ክፍል ያቆስለናል።

እዚህ ላይ ጳውሎስ *«ክፉ ቀን ሲገጥማችሁ፥ ሰይጣንን መቃወም እንድትችሉ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ»* ይለናል፤ ክፉ ቀን የፈተናና የስደት ቀን ነው። በተለይ ሰይጣን በተንኮሉ ሊያጠቃን የሚችልበት ማንኛውም ቀን ሊሆን ይችላል።

14 ከቁ. 14–17 ባለው ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ስለ ስድስት የእግዚአብሔር የጦር መሣሪያዎች ይነግረናል። እነርሱም *ዝናርና* ጥሩር (ቁ. 14)፥ የግር ጫማ (ቁ. 15)፥ ጋሻ (ቁ. 16)፥ የራስ ቁርና ሰይፍ (ቁ. 17) ናቸው። በጳውሎስ ዘመን የአንድ ወታደር የጦር መሣሪያ እነዚህን ስድስት ክፍሎች የያዘ ነበር። ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በሮም እስረኛ በነበረበት ጊዜ ነበር። ምናልባትም እርሱን የሚጠብቀው ወታደር ይህን የጦር መሣሪያ የለበሰ ሳይሆን አይቀርም፤ ስለዚህም ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ ሊዘረዝር የቻለውም እርሱን የሚጠብቀውን ዘበኛ የለበሰውን በማየት ሳይሆን አይቀርም።

እስቲ አሁን የጦር መሣሪያውን በመውሰድ እያንዳንዱን ክፍል እንመርምር። በመጀመሪያ ጳውሎስ *«እውነትን እንደ ዝናር ታጠቁ»* ይላል። ሰይጣን የውሸት አባት ነው (ዮሐ. 8፥44)። የእርሱን ውሸት ሊረታ የሚችለው እውነት ብቻ ነው፤ እውነት ስንል እምነት የሚጣልበት ማለታችንም ነው። ምክንያቱም ከሰይጣን ጋር በምናደርገው ጦርነት እርስበርሳችን ልንተማመን ይገባናል።

ሁለተኛው የጦር መሣሪያ፥ *ጽድቅን እንደ ደረት ጥሩር ለብሳችሁ»* ይለናል (ኢሳ. 59፥17)። እግዚአብሔር በክርስቶስ ያመኑትን አማኞች ሁሉ ጻድቃን እንደሆኑ ይቆጥራል። አዎ የክርስቶስን ጽድቅ ተቀብለናል፤ ክርስቶስ የእኛን ኃጢአት ቅጣት በራሱ ስለተቀበለ እኛ ጻድቃን እንድንሆን ተደርገናል። በክርስቶስ በማመናችን በደል የለብንም (ማር. 10፥45)። ስለሆነም የጽድቅን የደረት ጥሩር መልበስ ይገባናል። አለበለዚያ ግን ሰይጣን «ጻድቃን አይደላችሁም» በማለት ሊከሰን ይችላል። ያለ ጽድቅ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ልንቆም አንችልም። ሰይጣን ትልቅ ከሳሽ ነው፤ የወንድሞች ከሳሽ በመባልም ይታወቃል (ራዕ. 12፥10)። ሰይጣን እኛ በእውነት የዳንን መሆናችንን እንኳ እንድንጠራጠር ለማድረግ ይሞክራል። ከሰይጣን ዋና ዋና ተንኮሎች አንዱ፥ ብዙ ጥርጣሬዎችን ወደ አእምሮአችን እየከተተ በእምነታችን እንድንጠራጠር ማድረግ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር መቆማችንን እንድንጠራጠር ለማድረግ ይሞክራል፤ እግዚአብሔር በአጠገባችን እንዳለ እንኳ እንድንጠራጠር ያደርጋል። እኛንም «አንተ እኮ ኃጢአተኛ ነህ፥ ጽድቅ የለህም፥ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር በመቆም አይከራከርልህም» ይለናል። ሰይጣን እንደዚህ በሚለፈልፍበት ጊዜ ልናዳምጠው አይገባንም፤ ይልቁንም የጽድቅን የደረት ጥሩር ልንለብስ ይገባናል። በክርስቶስ የተነሳ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነን እንደተቆጠርን ያለንን እምነት አጠንክረን እንያዝ።

15 ከእግዚአብሔር የጦር መሣሪያዎች ሦስተኛው ክፍል በእግራችን የምንጫማው ነው። *«የሰላምን የምሥራች ቃል እንደ ጫማ በእግሮቻችሁ አጥልቃችሁ በመዘጋጀት ቁሙ»* ስለተባልን ጫማችንን ማጥለቅ ይገባናል። ይህም ማለት የክርስቶስን ወንጌል ለሌሎች ለማዳረስ ይዘን መሄድ ያስፈልገናል። ገበሬ ጫማ አያስፈልገውም፤ ወታደር ግን በእርግጥ ጫማ ያስፈልገዋል። ጫማ እንዳንደናቀፍና እንድንዘጋጅ ይረዳናል። ጫማችንን ካደረግን ወንጌል ይዘን ለመሄድ እንዘጋጃለን። በመንገዳችንም ላይ አንደናቀፍም፤ ጫማችን በሚሄድበት ቦታ ሁሉ የሰላም ወንጌልም አብሮን ይሄዳል። የክርስቶስ ወንጌልም አብሮት ይዘምታል። እዚህ ላይ ጳውሎስ ወንጌልን የሰላም ወንጌል ይለዋል፤ ምክንያቱም በወንጌል በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሰላም ይገኛል (ሮሜ 5፥1 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

16 አራተኛው የጦር መሣሪያ «የእምነት ጋሻ» ነው። እዚህ ላይ በእግዚአብሔር ያለን እምነት እንደ ጋሻ ተቆጥሮአል። ጋሻችንን ወደ ላይ በምናነሳበት ጊዜ በእግዚአብሔር ኃይል ፍጹም መተማመን ይኖረናል። በጳውሎስ ዘመን የአንድ ወታደር ጋሻ ቁመት አራት ተኩል ጫማ ሲሆን፥ ስፋቱ ሁለት ተኩል ጫማ ይሆናል፤ መላውን ሰውነት ለመከላከል በቂ ነበር። በዚሁ መልክ መንፈሳዊ ጋሻችንን በምናነሣበት ጊዜ ከሰይጣን ትንታጋዊ ፍላጻዎች ሙሉ በሙሉ እንጠበቃለን። የሰይጣን ትንታጋዊ ፍላጻዎች ፍርሃት፥ ተስፋ መቁረጥ፥ ሁከት ጥርጣሬና የመሳሰሉ ነገሮች ናቸው። የእምነት ጋሻችን ወደ ላይ በሚነሣበት ጊዜ እነዚህ ነገሮች እኛን ሊነኩን አይችሉም።

17 ከእግዚአብሔር የጦር መሣሪያዎች አምስተኛው ክፍል «የደኅንነት ራስ ቁር» ነው (ኢሳ. 59፥17)። ከብረት በተሠራው የራስ ቁር ወታደሩ ራሱን ይከላከልበታል። ጠላቱም ሊገድለው አይችልም። በዚሁ ዐይነት፣ የደኅንነት ራስ ቁር ሰይጣን መንፈሳዊ ህይወታችንን እንዳይገድል ይከላከልልናል። የራስ ቁር ለደኅንነታችን እንደ ዋስትና ነው፤ የዘላለም ሕይወት እንዳለን ማረጋገጫ ነው። እኛ የራስ

ቁራችንን ካደረግን ሰይጣን የዘላለም ሕይወታችንን ሊወስድብን አይችልም።

ከእግዚአብሔር የጦር መሣሪያዎች ስድስተኛው ክፍል «የመንፈስ ሰይፍ» ነው። እስከ አሁን ያየናቸው አምስቱ ክፍሎች የሚያገለግሉት ለመከላከያ እንደነበረ እናስታውስ፤ ይህ ስድስተኛው ክፍል ሰይፍ ግን ሰይጣንን የምንዋጋበት የማጥቂያ መሣሪያ ነው። ሰይፍ ካልያዝን ሰይጣንን ማሸነፍ አንችልም። ይህ ሰይፍ ምንድን ነው? ሰይፉ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

እግዚአብሔር በቃሉ ብቻ ምድርን በሙሉና በዓለም ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ፈጠረ። በቃሉም በቁ. 12 ላይ የተጠቀሱትን ገዥዎችን፥ ባለሥልጣናትን፥ ኃይሎችንም ሁሉ ፈጠረ። እነርሱም በመጨረሻቸው እግዚአብሔርን ተቃውመውታል። የእግዚአብሔር ቃል የሚሠራ ነው፤ ኃይልም አለው! በምድር ላይ ካለው ከማናቸውም ዐይነት ኃይል ይልቅ የሚበልጥ ኃይል አለው። የመንፈስን ሰይፍ በእጃችን በምንይዝበት ጊዜ ይህ ሁሉ ኃይል የእኛ ነው።

ያም ሰይፍ የመንፈስ ቅዱስ ሰይፍ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ያስታውሰናል (ዮሐ. 14፥26)። ቃሉን በመጠቀም ሰይጣንን ማሸነፍ እንድንችል የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው፤ የእግዚአብሔርን ቃል አንደ ሰይፍ በመጠቀም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን፤ ኢየሱስ በተፈተነ ጊዜ ለሰይጣን የሰጠው መልስ ነው (ማቴ. 4፥1–11)።

18 ሁሉንም የጦር መሣሪያዎቻችንን በጸሎት መልበስ ይኖርብናል። አንዳንድ ሰዎች ጸሎት ከጦር መሣሪያዎቻችን ሰባተኛው ክፍል እንደሆነ ይቆጥሩታል። ካልጸለይን የጦር መሣሪያችን ምንም ሊጠቅመን አይችልም። ታዲያ ጸሎታችን ለራሳችን ብቻ መሆን አይገባውም፤ ነገር ግን ለሌሎች ክርስቲያን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችንም መጸለይ ይኖርብናል። እንዲህ ከሆነም የሰይጣንን ተቃውሞ ለመቋቋምና እርሱንም ድል ለመንሣት ይችላሉ። ለእነርሱ መጸለይን የምንተው ከሆነ ግን እነርሱ ይሸነፋሉ፤ ስንጸልይም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥና . . . *ዘወትር. . .ለምዕመናንም ሁሉ ባለማቋረጥ መሆን ይኖርበታል*።

ጳውሎስ *በመንፈስ ጸልዩ* ይለናል፤ ይህም ማለት በመንፈስ ቅዱስ እውነትና ማስተዋል መጸለይ አለብን፤ መንፈስ ጸሎታችንን ያስተውላል፥ ስለምን መጸለይ እንደሚገባንም ያስተምረናል (ሮሜ 8፥26)።

19–20 ታላላቅ የሆኑ ክርስቲያን መሪዎችና ሰባኪዎችም ቢሆኑ፥ የእኛ ጸሎት ያስፈልጋቸዋል። ጳውሎስ ያደረገውን ታላላቅ ሥራ ሁሉ ለማድረግ ያበቃው ጓደኞቹ የሆኑ ክርስቲያኖች ይጸልዩለት ስለነበር ነው።

በቁ. 20 ላይ ጳውሎስ ራሱን *አምባሳደር* ብሎ ይጠራል (2ቆሮ. 5፥20)። የነገሥታት ንጉሥ አምባሳደር ቢሆንም አሁን በመጨረሻው በእግር ብረት ታሥሮ በሮም እስር ቤት ውስጥ ተጥሎአል።

21–22 ከጳውሎስ የሥራ ጓደኞች አንዱ የሆነው ቲኪቆስ በሮም እስር ቤት ሳለም አብሮት ነበር። ይህን መልእክት ለኤፌሶን ሰዎች ከማድረስ በተጨማሪ ቲኪቆስ የጳውሎስን መልእክት ለቆላስያስ ሰዎችም አድርሶአል (ቆላ. 4፥7–8)።

23–24 ጳውሎስ ይህን መልእክት ሲጀምር የኤፌሶን ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋና ሰላም እንዲያገኙ ምኞቱን ገልጦል (ኤፌ. 1–2)። አሁን ደግሞ ደብዳቤውን ሲጨርስ ለኤፌሶን ሰዎች *የሰላምና* (ቁ. 23) *የጸጋን* (ቁ. 24) ቡራኬ ይሰጣቸዋል። ከዚህም ስለ መልእክቱ ታላቅ ርዕስ እናስታውሳለን፤ እርሱም «በጸጋ በኩል ሰላምን ማግኘት» የሚል ነው (ኤፌ. 1፥2 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)። ምንም እንኳ እኛ የምንገኘው በታላቅ መንፈሳዊ ትግል ውስጥ ቢሆንም፥ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን፤ በቤተ ክርስቲያናችንም ውስጥ ሰላም አለን፤ እንዲሁም በየልባችን ውስጥ ሰላም አለን።

ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሚወዱ ሁሉ ጋር ጸጋ ይሁን! ጌታን የማይወዱ ሰዎች ስለ ፍቅርና ስለ ጸጋ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም። የእግዚአብሔርን ጸጋ የተቀበሉ ሁሉ ግን ልጁን ኢየሱስን ይወዳሉ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ እኛ ሊመጣ የቻለው በኢየሱስ በኩል ስለሆነ ነው። ስለሆነም ጌታችንን *በማያቋርጥ ፍቅር* እንውደደው፤ ኑሮአችንንም የእርሱ ጸጋና ክብር ሊመሰገን በሚችልበት ሁኔታ እንኖር!